## የሁለተኛ ደረጃ ተከሳሾች ፍርድ ቤት መቅረብ

እያንዳንዱ እሥረኛ መጀመሪያ ለፖሊስ ሌፍትናንት ኮሎኔሎችና ቀጥሎ ለኮሎኔሎች ቃል ሰጥቶ ነበር። ያ ቃል በሌፍትናንት ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ለሚመራ አጣሪ ኮሚቴ ተላልፎ ኮሚቴው የራሱን ድርሻ ከተወጣ በኋላ ፋይሉን ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማስተላለፉ ተሰማ። ይህ በእንዲህ እያለ መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም. ጧት አንድ ሰዓት ገደማ ከዚያ በፊት ባልተለመደና ባልተገለጸ ምክንያት የእሥር ቤቱ ኃላፊ ሌፍትናንት ኮሎኔል በቀለ ወርቄ ከአንድ ወጣት ሙሉ የመቶ አለቃ ጋር ወደ ቁጥር አራት እሥር ቤት መጡ። በሌሎች ቤቶች ውስጥ የነበሩት መኮንኖች በሁኔታው እንግዳነት የተነሳ "ምን ሊሆን ነው?" ብለው በማሰብ በየበሩ ብቅ እያሉ በቁጥር አራት ስቀላ ቤት የሚደረገውን ይከታተሉ ነበር። ከዚያ ስም እንጠራለን አድምጡ ተባለና አንደኛ አቶ ብርሃኑ አሥረስ፣ ሁለተኛ የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ፣ ሦስተኛ የሻለቃ መላኩ በቀለ፣ አራተኛ የሻለቃ ተፈራ በላይ፣ አምስተኛ የሻለቃ ኃይለማርያም ሌንጮ፣ ስድስተኛ የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ፣ ሰባተኛ የሻምበል አሥራት ደፈረሱ፣ ስምንተኛ የመቶ አለቃ በቀለ መንገሻ ተብሎ ተጠራና ወጥተን ከእሥር ቤቱ የሺቦ አጥር አጠገብ እንድንቆም ታዘን፣ እንደ ትዕዛዙ ፈፀምን።

ወዲያው መሣሪያ የታጠቁ በርካታ ወታደሮች ራቅ፣ ራቅ ብለው ዙሪያውን ከበቡን። ከዚህ በኋላ ኮሎኔል በቀለ ወርቄ አብሯቸው ለነበረው የመቶ አለቃ ትዕዛዝ በመስጠት ደግመው ስማችንን በመጥራት አጣርተውና ቆጥረው አስረክበው ሔዱ። እንደገና ሌላ አንድ ሻምበል መጣና በበኩሉ የስም ጥሪው በትክክል መካሄዱን ለማረጋገጥ አንድ ባንድ ስማችንን እያስጠራ ከተመለከተን በኋላ በወታደራዊ ደረቅ የትዕዛዝ ቃና «ለቁርስ ግማሽ ሰዓት እሰጣለሁ። ስለዚህ አሁን ወደ ክፍላችሁ ተመለሱና ቁርስ በልታችሁ ልክ በሰዓቱ እዚሁ እንድትገኙ» ብሎ አዘዘ። እኛም ትዕዛዙን ተቀብለን ወደ ስቀላ ቤታችን ገባን። ተጨንቆና ትንፋሹን ውጦ ሁኔታውን ይከታተል የነበረው እሥረኛ ሁሉ የተጠራንበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ግር ብሎ ወደኛ መጣ። ምክንያቱን ጠየቁን፣ እኛም የተነገረንን ገለጽን። ለጊዜው እሥረኛው በእኛ ላይ ክፉ ነገር እንደማይኖር ከሁኔታው ቢገምትም፣ እያንዳንዱ በበኩሉ አሁን ካየው ከዕለት ችግር ያለፈ የወደፊት እጣው ምን ሊሆን እንደሚችል ስለማያውቅ ከጭንቀት የተላቀቀ አልነበረም።


ለቁርስ የተሰጠን ግማሽ ሰዓት ደረሰና ሁለት ሰዓት ሆኖ ስምንታችንም ከነበርንበት ቤት ስንወጣ ጥቋቁር አፋቸውን ወደ አራቱ ቤቶች ከፍተው ከተጠመዱት መትረየሶች የከፋሎቹ አፍ ወደኛ ዞረ። «ለስለት የሰጡት ገላ አያምም» ቢባልም ሁኔታው የሚቀፍ በመሆኑ እንደደመመን፣ ሁለት ስሪ ኳርተር መኪኖች ወደ ቆምንበት ቦታ መጥተው ቆሙ። ከዚያም አራት አራት እየሆን ከሁለት ተከፍለን በሁለቱ መኪኖች ላይ እንድንሣፈር ተደረገ። በያንዳንዱ ስሪ ኳርተር መኪና ላይ ከአሥር ያላነሱ ወታደሮች ከእነ መሣሪያቸው ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ከኛው ጋር

ተሣፈሩ። ስሪ ኳርተሮቹ አናት ላይም ሁለት ቀላል መትረየሶች ፊታቸውን ወደእኛ ሳይሆን መኪኖቹ ወደሚሔዱበት አቅጣጫ ተደርገው ተጠመዱ። አንዳንድ ከባድ መትረየስ የተጠመደባቸው ሁለት ጅፖች ከፊትና ከኋላ አጀበውን ጉዞ ጀመርን። የጉዟችን አቅጣጫ ከአንደኛ ክፍለ ጦር በጋንዲ ሆስፒታልና በፖሊስ ጋራዥ (አሁን ሸራተን ሆቴል በተሠራበት ፊት ለፊት) አድርጐ በታላቁ ቤተ መንግሥት በኩል ወደ ስድስት ኪሎ መሆኑን እንዳወቅን ከባድ ሥጋት ተፈጠረብን። የደም ሥራችን ተገታትሮ ፊታችን ሁሉ ተለወጠ። ጠባቂዎቻችንም ተጨንቀው ነበር። የኛ ሥጋት ግልጽ ነበር። በቆየው ልማድ ወንጀለኛ የሚቀጣው ወንጀሉን በፈጸመበት ቦታ ነበር። የእኛም ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ አቅጣጫ መሄድ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በተካሔደበት ቦታ የሞት ቅጣቱ ሊፈፀም ነው በሚል ግምት ነበር። ይዘውን የሚሔዱት ወታደሮች ጭንቀት የመነጨው ደግሞ መፈንቅለ መንግሥቱን የሚደግፍ ኃይል መንገድ ላይ ቢጋረጥ እንዴት እንወጣዋለን የሚል እንደነበር በኋላ ተረዳን። የሆነ ሆኖ የተወሰድነው ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ሳይሆን እሱን አልፎ አል.ጋ ወራሽ ግቢ አጠገብ ከነበረው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ነበር። "የዋለ ያደረ ደም ገላጋይ አያጣም" እንዲሉ የመጀመሪያውን እፎይታ አገኘን።

ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደ ደረስን ካንደኛ ደረጃ ተከሳሾች ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ በዐመፅ አራማጅነት ተከሰን መምጣታችንን ዐወቅን። ከፍርድ ቤቱ ግቢ የደረስነው ሦስት ሰዓት ሲሆን ነበር። ዳኞች ወዲያ ወዲህ ይላሉ። እስከ አራት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ድረስ ችሎት አልተቀመጡም፤ ምን ችግር እንደተፈጠረም ማወቅ አልቻለንም። የሚጠብቀው ጦር በሁለት ዙርያ ጥምጥም ከቦናል። አንዱ ዙር የአጥሩን ካብ ተጠግቶ ጠመንጃውን ወደ ውጭ ወድሮ ለመከላከል ሲቆም፤ ሁለተኛው ዙር ደግሞ ፊቱን ወደኛ አድርጐ ለተኩስ በተዘጋጀ ሁኔታ ይጠብቅ ስለነበር የችሎቱን ቶሎ አለመጀመር ከኛ ይልቅ እነሱ ጠልተውት እንደነበር ከሁኔታቸው ይታይ ነበር። እኛን የሚጠብቀው ጦር "እሥረኞቹን የሚያስለቅቅ ኃይል ቢመጣስ" የሚለው ሥጋት ሲያስጨንቀው፤ በዳኞች በኩል ደግሞ "በቅርቡ የሆነውን እያወቅን ረመጥ ላይ መቆማችን እኮ ነው" በሚል ሐሳብ ውስጥ መግባታቸውን ገመትን። ባጭሩ በዚህ ቆይታ ጊዜ የፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ የነበረው ሁሉ በሦስት ወገን ጭንቀት ላይ የወደቀ ነበር። ተፈጥሮ የነበረው ሁኔታና አሳድሮ የነበረው ጭንቀት የችሎቱን መሰየም ማዘግየት እንጂ ማስቀረት አልቻለም። ስለዚህ ዳኞች በችሎት ተሰየሙና የፍርድ ሒደቱ ቀጠለ። ለዚህም ስምንታችንንም ከሁለት በመክፈል በሁለት ችሎት እንድንቀርብ ሲደረግ፤ እኔ ያለሁበት የመጀመሪያዎቹ አራት ተከሳሾች በአንደኛ ችሎት የተቀሩት አራቱ ሁለተኛ ችሎት ላይ ደለደሉን።

የእኔ ክስ የታየበት የወንጀል መዝገብ ቁጥር ፩፻፶፫/፶፫ ሲሆን፤ ዳኞቹ ቀኛዝማች ጣሰው አየለ፣ አቶ ከበደ ክልል እና አቶ ኃይሌ አማን ነበሩ። ዐቃቤ ሕጉ ደግሞ አቶ ቦጋለ ውቤ ይሰኙ ነበር። የእኔ ዕድሜም ፳፱ ዓመት፣ ኃላፊነቴ ያዋሳኝ አገሮች ጥናትና ምርምር ሹም እንደነበርኩ ከተመለከተ በኋላ ሠራ የተባለው

ወንጀልም




በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፹ የተደነገገውን በመተላለፍ የሃሰት ወሬ በማውራትና ሕዝቡን በማሳሳት መከሰሴንና የወንጀሉ ዝርዝርም በቻርጁ ላይ መመልከቱ ተገለጸ።

ክሱ ተሰጠኝና አንብቤ እንደጨረስኩ ለዚህ ወንጀል ጥፋተኛ ነህ ወይስ አይደለህም? የሚል ጥያቄ ቀርቦልኝ መልሴን ሰጠሁ። ይሄን ጊዜ ዐቃቤ ሕጉ ወደ ወህኒ ቤት እንድወርድ ለፍርድ ቤቱ አመለከተ። በዚህ የተጀመረውን ክርክር የመሀል ዳኛው እንዲህ በማለት ገልጸውታል።

ተከሳሹ እምነት ክህደት ቢጠየቅ ጥፋተኛ አይደለሁም የሠራሁት ሁሉ በአለቃዬ ታዝዤ ነው ብሏል። ዓቃቤ ሕጉ ተከሳሹ ከባድ ወንጀል የፈፀመ ስለሆነ አስተማማኝ ጥበቃ ወዳለበት ወደ ታላቁ ወህኒ ቤት እንዲወርድ ወህኒ ቤቱም እንዲቀበለው ማዘዣ ይጻፍልኝ። ለተካደውም ምስክር እንዳቀርብ ሲል አመልክቷል። ተከሳሹም ጠበቃዬን ይዤ እንድከራከር ይቀጠርልኝ ብሎ አመለከተ ሲሉ አተቱ።

ከዚህ በኋላ ዳኞቹም የሚከተለውን ትእዛዝ አስተላለፉ። ዓቃቤ ሕጉ ያመለከተውን ተቀብለን ተከሳሹ ወህኒ ቤት እንዲወርድ፤ ወህኒ ቤቱም እንዲቀበለው ደብዳቤ ይጻፍ። ካሉ በኋላ ለእኔም የሚከራከርልኝ ጠበቃ ይዤ እንድቀርብ፤ ቀጠሮ ለመጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ተባለ። በሁለተኛው ችሎት የቀረቡትም ለቀረበላቸው የዕምነት ክህደትና ስለ ዐድማው ቀድሞ ማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት መልስ ከኔው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነበር። ይኸውም "በወታደር ሥርዓት" አንድ የጦር ሰው ባለቃው ሲታዘዝ እሺ ብሎ ትዕዛዝ መፈጸም እንጂ ለምን ብሎ እንዳይጠይቅ የሚያግድ በ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. የታወጀ የንጉሡ መሪ ቃል ነበር።



ወታደራዊ ትዕዛዝን ያለጥያቄ መፈፀም እንዳለበት የሚገልጽ የንጉሠ ነገሥቱ መሪ ቃል

ይሁንና ከስምንታችን መካከል እኔ ሲቪል ስለነበርኩ የሰጠሁት ቃል ሐሳቡ ያው ሆኖ አነጋገሩ ግን ለወጥ ያለ ነበር። እርሱም የሠራሁት ካለቃዬ ታዝዤ እንጂ ከራሴ አመንጭቼ አይደለም። ስለመፈንቅለ መንግሥቱ መነሣሳትና ቅንብርም ቀደም ብሎ የማውቀው ነገር አልነበረም የሚል ነበር። ፍርድ ቤቱ ግን ለስምንታችንም አንድ ዓይነት ውሳኔ በማሳለፍ ወህኒ ቤት እንድንወርድ፣ ወህኒ ቤቱም እንዲቀበለን ደብዳቤ እንዲጻፍ፣ ቀጠሮችንም ለመጋቢት ፲፯/፶፫ እንዲሆን ተወሰነ። ደብዳቤው ተጽፎ መጀመሪያ ወደ ፍርድ ቤት ለወሰደን መኮንን ሰጠና ዕቃችንን ለማንሣት ወደ

ነበርንበት ወደአንደኛ ክፍለ ጦር ተወሰድን። ከዚያ ዕቃችንን አንሥተን ለቀረው እሥረኛ የዋልንበትን ነግረን ስንጨርስ ወደ ወህኒ ቤት ተወሰድን። ከወህኒ ቤቱ ደርሰን ዋናው በር ፊት ለፊት ደጅ ላይ እንዳለን የወሰደን የጠባቂ ጦር አዛዥ መኮንን ከፍርድ ቤት ያመጣውን ማዘዣ ለወህኒ ቤቱ የዘብ ኃላፊ ሰጠ። የዘብ ኃላፊው ማዘዣውን ወስዶ ለበላይ ኃላፊው ካሳየ በኋላ በሩ ላይ አንድ በአንድ እየተፈተሽን ወደ ውስጥ እንድንገባ ተደረገ።

## ቦንዳና ቶንዶዝ

ወህኒ ቤት ቅጥር ግቢ ከገባንበትና ትልቁ በር ከኋላችን ከተዘጋበት ደቂቃ ጀምሮ ነፃነት አልባ የሆነው አዲሶቹ እሥረኞች እንግዲህ የወጣትነት ዕድሜና ሕይወታችን በዚህ ወህኒ ቤት እንደሚያልፍ በመገመት ነገሮችን ወደኋላ መለስ ብለን በአዕምሮአችን ጓዳ የተቀመጠውን በዝምታ ተውጠን እየፈተሽንና እየመረመርን መገረም ጀመርን። በሌላ በኩል ደግሞ ለብዙ ዓመታት ታሥረው በዚያ የሚገኙ ብዙ እሥረኞች መጀመሪያ የተመለከቱን እንደነሱ ያለ ተፈጥሮ ያለን ሰዎችና እንደነሱ ችግር ገጥሞን የመጣን አድርገው ሳይሆን ብርቅ አውሬዎች እንደመጣን አድርገው ነበር። ይህ አስተሳሰባቸው ባንድ በኩል ሲታይ በርግጥም ትክክል ነበር፤ ሊያሰኝ ይችላል። እኛን ከነሱ ጋር ሲያስተያዩን ሰውነታችን አልተጐሳቆለም፤ ላኃያችን አልደረቀም፤ ጽዳታችንም የተጠበቀ ነበርና።

ነገሩ በዚህ ብቻ አላበቃም። በመገረም ከሚመለከቱን መካከል ሁለት ጠና ያሉ እሥረኞች ከፊታችን አምስት ሜትር ያህል ርቀት በሚገኙ ድንጋዮች ላይ ተቀምጠው አሮጌ የብረት ቦንዳ በድንጋይ ይቀጠቅጣሉ። ረጅሙን ቦንዳ ባጭር ባጭሩ እያደረጉ መቆራረጡን ተያያዙት። ከዚያም እያንዳንዱን ቁራጭ ቦንዳ ባንደኛው ጠፍጣፋ ጐኑ በኩል ስለት ሊወጣው እንዲችል መቀጥቀጣቸውን ቀጠሉ። እኛ ለምን እንደሚቀጠቅጡት ስላላወቅን ከነበረብን ብስጭት ጋር ድርጊቱ አስለቸን። እንደውም እኔ አላስችል ስላለኝ "እንዴ ምንድን ነው? እፊታችን እንዲህ የምታደርጉት"። ብዬ ጠየቅሁ። ከመካከላቸው አንዱ በግልምጫ ዓየን፤ በለስ እንደቀናው አዳኝ ደስ ብሎታል። የይቅርታ መልስ ስንጠብቅ ይባስ ብሎ "ለናንተ ራስ መላጫ ነው የሚዘጋጀው" አለን። ምላጭ ወህኒ ቤት ስለማይገባ ቀልድ መሰለን። ቀጥለንም እርስ በእርስ በመተያየት «እንዴት» የሚል ጥያቄ ሰነዘርን። እነሱም በበቀል ዓይን ዓዩንና "እሥረኛ ፀጉሩ ሳይላጭ እንኳን ዓለም በቃኝ ሌላ ክፍል አይገባም" የሚል መልስ ሰጡን። ዓይናችንን በማፍጠጥ "እንዴ! በዚህ ልንላጭ?" በማለት እንደገና ስንጠይቃቸው፤ ቦንዳዎቹን መቀጥቀጣቸውን በመቀጠል "አዎ! ሌላ መላጫ የለም? እናንተ ሳታዩት የኖራችሁት፣ ቤት ያፈራው መሣሪያ ይኸው ነው። መቼስ ምን ይደረግ?" በማለት ተሳለቁና «የናንተ ዕዳ ነው። የእናንተ አስተዳደር ውጤት ነው። እሥረኛው የኖረው በዚህ ዓይነት ነው። ዛሬ እናንተ ላይ ሲደርስ እንዴት ይገርማችኋል? "ደባ ራሱን ስለት ዱጉሱን» ይባል የለ" ብለው እኛን

ለነበረው የአስተዳደር በደል ተጠያቂ በማድረግ ስለት ለማውጣት ቅጥቀጣቸውን ቀጠሉ።

እራሳችንን ይዘን የሚቀጠቅጡትን ቦንዳ በመመልከት ላይ እንዳለን በወህኒ ቤቱ ክሊኒክ የሚሠራ፣ አቶ አበበ ወልደ ሥላሴ የሚባል የክብር ዘበኛ ሠራዊት ባልደረባ የነበረ፣ ኮርያ በዘመተ ጊዜ አዛዦቹ የነበሩ መኰንኖች ከመካከላችን ነበሩና ከእነሱ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ከላጮቹ ጋር የነበረውን ፍጥጫ በሚግባቡበት ቋንቋ ተነጋግሮ በቦንዳ መላጨታችን ቀርቶ በቶንዶስ የመላጨት ያህል እንዲቀርጡን ስምምነት ላይ ደረሰ። ለዚህ ውለታ እያንዳንዳችን አንዳንድ ብር እንድንከፍል ተጠየቅን። በክፍያው ብንስማማም ገንዘብ አልነበረንም። ስለዚህ ገንዘቡ ሌላ መሰናክል ሆኖ ተደነቀረ። ሆኖም በቆየው የወህኒ ቤት ልማድ ገንዘቡ እስቲከፈል ድረስ ልብስ ወይም ጫማ ማስያዝ ይቻል ስለነበር "ልብሳቸውን ያስይዙ" ተባልን። ግልግሉን የያዘው አቶ አበበ የልብሳችን በመያዣነት መጠየቅ ከበደውና "ውለው አድረው ከዘመድ ሲገናኙ ይከፍላሉ" ቢል «እንግዲያውስ አንተ ክፈልላቸው ወይ ዋስ ሁናቸው» አሉት። እኛም ቤተሰቦቻችን ሲመጡ ገንዘቡን ለእሱ ልንከፍል ተስማምተን አቶ አበበ ክፍያውን ፈጽሞ ድርድሩ ተሳካ። አቶ አበበን ባይጥልልን ኖሮ ተቀጥቅጦ በተሳለ አርጌ ቦንዳ ብንገረደፍ ሊያስከትል ይችል የነበረው የጤና ጠንቅ እንዳለ ሆኖ፤ እሁድ ከቤተሰብ ጋር ስንገናኝ የዘመድ አልቃሽ[10] መስለን ሲያዩን የእኛም የነሱም ሞራል ምን ያህል ይነካ እንደነበር አንባቢ መገመት ይችላል።

በቦንዳ መላጨቱ ቀርቶ እፎይ ብለን ወደ ዓለም በቃኝ ከመግባታችን በፊት ደግሞ ሌላ ችግር መጣ። ልብሳችን "ሺህ ገዳይ" ከሚባል የቀንና የሌሊት ልብስ መተኮሻ "አውቶ ክለብ" ውስጥ መግባት አለበት ተባልን። ይህ ሺህ ገዳይ /አውቶ ክለብ/ የሚሉት በዳቦ መጋገሪያ መልክ የተሰራ ሲሆን፤ በቀን ከሚገባ ከ፴ እስከ ፵ አንዳንድ ጊዜም እስከ ፷ ሰው ከሚደርስ እሥረኛ ጋር የመጣ የቀንም ሆነ የሌሊት ልብስ እዚያ ውስጥ ባንድ ላይ ይገባና ለአንድ ሰዓት ያህል በከፍተኛ ሙቀት ታፍኖ ቆይቶ ተባዩ ሲሞት የሚወጣ በመሆኑ የናንተም ልብስ እዚህ ውስጥ ይገባና ይተኮሳል አሉን። "ሺህ ገዳይ የተባለበት ምክንያትም ሺህ ቅማል ባንድ ጊዜ ስለሚገል ነው። የቦንዳውን ነገር ካየን ወዲያ አይደረግም የምንለው ነገር ስላልነበር አሁንም የአበበን ርዳታ በድጋሚ ጠየቅን። እሱም "የዚያ ሁሉ ሰው የተለያየ ወዝና ቆሻሻ አንድ ላይ ታፍኖ ቆይቶ ሲወጣ እንኳን ልትለብሱት ባጠገቡ ሊታልፉ አትችሉም። ክርፋቱ ሌላ ነው» አለን። «እንዴት? እኛ እኮ ፅዳታችንን የጠበቅን ነን! እንዴት እንደዚህ ይደረጋል? " ብለን ተቃውሞ አነሳን። የሺህ ገዳይ ኃላፊ "የወህኒ ቤቱ ደንብ ነው፤ የእሥረኛውን ጤንነት ለመጠበቅ ለጥንቃቄ ተብሎ እገሌ ከገሌ ሳይባል ልብሱ ተተኩሶና ገላውን ታጠቦ ይግባ፤ የሚል የበላይ ትዕዛዝ ከተሰጠን ቆይቷል። እናንተን ከዚህ ውጪ ሊያደርጋችሁ የሚችል ነገር የለም" አለን። እኛም ስለተጨነቅን አቶ አበበን "እባክህ መንገድ ፈልግና አድነን» አልነው። መቼም ሳይደግስ አይጣላም

[10] ከፊል ፀጉሩን ተላጭቶ ከፊል ፀጉሩ የቀረ

እንደሚባለው አቶ አበበ ከሺህ ገዳይ ክፍል ኃላፊ ጋር እንዳይጋጭ ተጠንቅቆ በመነጋገር «ይህን ትዕዛዝ መለወጥ የሚችለው ጠቅላይ ካቦው ነው።» በማለት እሱን ፈልጐ በማነጋገር ልክ ለላጮች እንደተደረገው አንዳንድ ብር ልንከፍል ተስማምተን ልብሳችን ሺህ ገዳይ ከመግባት ዳነ። እዚያም ከፍርድ ቤቱ በመጣው ዝርዝር መሠረት ስማችን እየተጠራ ስምንታችንም የእሥረኛ መታወቂያ ተሰጥቶን ዓለም በቃኝ ገባን።

## ዓለም በቃኝ

ዓለም በቃኝ በታላቁ ወህኒ ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኝ የወህኒ ወህኒ ሲሆን፣ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን መንግሥት ተጀምሮ በንጉሥ ኃጋለ ሥላሴ የተጠናቀቀ ስምንት ማዕዘን «ኦክታጐናል» ቅርጽ ያለው ባለ አንድ ፎቅ የወህኒ ቤቱ አንድ አካል ነው። ሃያ ሁለት የምድር ቤትና ሃያ ሁለት የፎቅ ክፍሎች አሉት። የፎቁ ጣራ ዘበኞች መትረየስ ጠምደው የሚጠብቁበት ሲሆን፣ ከበሩ በኩል ደግሞ አንድ በሁለተኛ ፎቅነት ተደርቦ የተሠራ ባውዛ ቤት የሚሉት ወህኒ ቤቱን እየዞረ የሚያሳይ ደማቅ ብርሃን የሚሰጥ መብራት ያለበት ፎቅ ነው።[11] ዓለም በቃኝ በነፍስ ግድያ፣ ይሙት በቃ፣ ዕድሜ ልክ፣ ፳፫ ዓመት እሥራትና ግርፋት የተፈረደባቸው፣ የልዩ ቅጣት እሥረኞች ከፍርደኛ ወይም ከቀጠሮ ቤት በጥፋት የተቀጡ የሚገቡበት ጥብቅ ቁጥጥር ያለበት ወህኒ ቤት ሲሆን፣ እኛን ለመጠበቅና ለመቆጣጠር እንዲያመች ተብሎ ለብቻችን አንድ ክፍል ተደለደልን። ከክፍላችን ልንገባ ከመስኩ ላይ ስንደርስ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስን አገኘናቸው። የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ በመድፈኛነት ስዊዝ ሠልጥነው የመጡ ከጠላት በፊትና በኋላ የክብር ዘበኛ አባል የነበሩ፣ ከነቢትወደድ ነጋሽ ጋር ተሞክሮ በነበረው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ተባባሪ የነበሩ ናቸው።

የመቶ አለቃ በቃለ አናሲሞስ ከሌሎች እሥረኞች ጋር በመሆን መጀመሪያ ከቀረቡንና እሥረኞች መካከል አንዱ ናቸው። እንደውም የክስ ወረቀታችንን አላዩን ብለው ጠይቀውን የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤና የሻለቃ ተፈራ በላይ የክስ አንቀፅ ደህና ነው ተቀባይነት ያለው ነው ብለውን የነገሩ ናቸው። ይህም ማለት ወደኑሱ ፍርድ የተጠጋ ዓለም በቃኝ አዝግጦ[12] የሚያስቀር አንቀፅ ነው ማለታቸው ነው። የኔንና የሻለቃ አዲስ ዓለም ፅጌን "የሌባ መክሰሻ አንቀፅ ነው" አሉና አጣጣሉት። በዚያን ጊዜ በዓለም በቃኝ ወህኒ ቤት ውስጥ የነበረው የከባድ ወንጀል እሥረኛ ሁሉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፆችንና ቅጣት ልካቸውንም ጥንቅቅ አድርጐ በቃሉ ያውቃቸው ነበር። እኑ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ሁኔታችንን ከተረዱ በኋላ ወሬውን ለጓደኞቻቸው ለማድረስ ሔዱ፤ እኛም ወደ ተመደበልን ክፍል ገባን። የክፍሏ መጠን ሁለት ሜትር ተኩል በሁለት ሜትር ስትሆን፣ ከፍታዋም ሁለት

[11] ዛሬ ይህ እሥር ቤት ፈርሶ ለአፍሪካ ሕብረት አገልግሎት የሚሰጡ ሕንፃዎች ታንፀውበት አካባቢው ፍፁም ተቀይሯል።

[12] አዝቅጦ ለማለት ነው።

ሜትር ነው። በሩ የወፍራም ቆርቆሮ ሆኖ ከቁመቱ አንድ አራተኛ የሚሆነው የላይኛው ክፍል በሩ ሲዘጋ ለነፋስ ማስገቢያና አንዳንድ ጊዜም በግቢው ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ መመልከቻ ለወሬና ለጥሪም መስሚያ እንዲሆን በብረት ፍርግርግ የተሠራ ነው። የተመደብኩበት ክፍል ጠባብ በመሆንዋ ፍራሾችን ደራርበን ተጠጋግተን ለመተኛት ወሰን። ይህን ፈፅመን ዙሪያችንን ስንቃኝ ከበሩ አጠገብ አንድ ጉርድ የብረት በርሜል ተቀምጦ ዓየን። ማታ ከአሥራ አንድ ሰዓት በኋላ የእለቱ ቆጠራ ተደርጐ የየክፍሉ በር ከተዘጋ በኋላ እስከ ጧት አንድ ሰዓት ድረስ ምንም ዓይነት ችግር ቢያጋጥም የክፍሉ በር ስለማይከፈት፤ ሆዱን ላመመው መፀዳጃ፣ ሽንት ለያዘው መከፈያና እጣቢ መድፊያ በመሆን እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው። ከተመደብንበት ክፍል የገባነው በምሽት ስለነበር እራታችንን ሳንመገብ ተኝተን አደርን።

በማግሥቱ ጧት ለመፀዳዳት እኛ ያለንበት ክፍል ከሌሎቹ እሥረኞች ክፍል በፊት ተከፈተ። በፎቁና በምድር ላለው እስከ አራት መቶ ለሚገመት እሥረኛ ያለው መፀዳጃ ሁለት ክፍሎች እያንዳንዳቸው መደዳውን የተቀመጡ አራት አራት ጉድጓዶች ያሏቸው ብቻ በመሆናቸው ተራ እየጠበቅን ተፀዳዳን። ከዚያም ከሜዳው መሀል እንደ ከብት ማጠጫ ገንዳ ሆኖ በተሰራው የውሃ መውረጃ እጃችንና ፊታችንን ታጥበን ስንገባ፤ በሩ ከውጭ ተዘጋብን። ቀጥሎ የፎቅ ክፍሎች በሮች ተከፍተው እሥረኛው እየወጣ በየተራ እየተፀዳዳ ወደየክፍሉ ተመለሰ። ከዚያም የምድር ቤቱ እሥረኛ ወጥቶ ከተፀዳዳ በኋላ ወደ ክፍሉ በመመለስ ፋንታ ከሁለት ሰዓት እስከ አራት ሰዓት ባለው ጊዜ በዚያች ዙሪያዋን በግንብ ተዘግታ ቀና ሲሉ አውድማ የምታክል ሰማይና ጉንበስ ሲሉ በፎቁ ዙሪያ ልክ ስፋት ያላት ምድር በሚታይባት አውድማ የምታክል መስክ ሰውነቱን ለማፍታታት በአውድማ እንደሚሔድ በሬ እንዞለሌ ሲዞር፤ በበሩ ፍርግርግ ላይ ተራ በተራ ፊታችንን እየለጠፍን ሁኔታውን ስንመለከት ቆየን። ሰዓቱ ሲደርስ የምድር ቤት እሥረኛ ተመልሶ በየክፍሉ ገባና ለግማሽ ሰዓት ያህል መስኩ እንዲፀዳ ተደረገ። የፎቁ እሥረኛ በተራው በዚያችው ሜዳ ለ፪ ሰዓት ያህል ሰውነቱን ማፍታታት ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ክፍላችን ውስጥ ተቀምጠን በሐሳብ ወደኋላ መለስ በማለት ያለፈውን ሁኔታ ሁሉ እያነሳን በኛ በኩል ሊደርስ ይችላል ተብሎ የማይገመት ውድቀት መድረሱ አልዋጥልን ብሎ እየገረመን እንጫወት ነበር። እንዲህ እያልን ውለን ፲፩ ሰዓት ሲሆን በሩ ሁሉ ተዘጋ።

በሁለተኛው ቀን እኛ የማናውቃቸው እና በቤተሰቦቻችን የተመረጡ ጠበቆቻችን ወደ ወህኒ ቤቱ ስለመጡ፤ ተራ በተራ እየተጠራን ወጥተን በወህኒ ቤቱ አስተዳደር ምክትል ሹም ቢሮ ተገናኝተን «እኔ ነኝ ላንተ የቆምኩ» እየተባልን ተዋወቅን። በዚያኑ ዕለት በታኅሣሥ ፲፱፻፶፫ቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ዐመፁን የሚደግፍ ልዩ ልዩ ሥራዎች ሠርታችኋል በመባል አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ገብተው የቆዩ እሥረኞች የሚከተሉት እንደሆኑ ሰማን። ቆይተንም አገኘናቸው። እነሱም አቶ አሰፋ ዱላ የህግ ጠበቃ ከአዲስ አበባ፣ አቶ ሺፈራው ደሳለኝ ከድሬዳዋ፣ አቶ ጌታቸው ጋረደው ከድሬዳዋ እና አቶ ዓለም ሰገድ ከድሬዳዋ ናቸው።

በተለይ በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ጊዜ የድጋፍ ንግግር አድርጋችኋል በማለት በመንግሥት ተይዘው ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ከተላኩት አንዱ ስለሆኑት ስለ አቶ ሺፈራው ደሣለኝ ጥቂት ማለት ይገባኛል። አቶ ሺፈራው ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ተልከው ለፖሊስ ቃላቸውን ሰጥተው ፍርድ ቤት ቀረቡ። የዕምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ዳኛው "ሠርተሃል ለተባለው ወንጀል ጥፋተኛ ነህ አይደለህም" ይላቸዋል። ‹‹የቱን ወንጀል›› ሲሉ አቶ ሺፈራው ዳኛውን ይጠይቃሉ። ዳኛው አቶ ሺፈራው፣ ሠርተዋል የተባለውን የወንጀል ቃል ሊናገሩት አልወደዱምም አልደፈሩምና አንተ የሠራኸውን ብለው ጠየቁ። አቶ ሺፈራው ‹‹እስቲ ወንጀል የተባለው ይነበብልኝ›› ብለው አጥብቀው ይጠይቃሉ። ይሄን ጊዜ ዳኛው ሳይወዱ "ይህን ጣሳ እግዚአብሔር ገላገለን፣ አወረደልን ማለትህን" ይሏቸውና "ለዚህ ጥፋተኛ ነህ አይደለህም" ይሏቸዋል። ‹‹የለም ተስተካክሎ ይጻፍልኝና ዕምነት ክህደቱን ልናገር›› ይላሉ። ‹‹የለም በዚሁ ላይ ጥፋተኛ ነኝ በል›› ይሏቸዋል። ‹‹ትክክለኛ ቃሌ ይጻፍና ነው እንጂ እንዲሁ ጥፋተኛ ነኝ፤ አይደለሁም፤ አልልም›› ብለው ይመልሳሉ። ‹‹እሽ ምን ተብሎ ይስተካከል ሲሏቸው፤ ይህን የበሰበሰ የተጠረማመሰ አሮጌ ጣሳ እግዚአብሔር ገላገለን ነው›› ያልኩት ሲሉ ዳኞች የተባለውን አልሰማንም ለማለት ራሳቸውን ጠርቤዛ ሥር አግብተው ተደበቁ። ጥቂት አቅማምተው ቆይተው በማመንታት ይኸ ሰውዬ እብድ ነው። አማኑኤል ከአእምሮ በሽተኞች ሆስፒታል ተልኮ ይታከም ብለው ላኩዋቸው። አማኑኤል ሆስፒታል እንዳሉ ቅዳሜና እሁድ የበሽተኞች ዘመዶች ለጥያቄ ሲመጡ የመንግሥቱ አስተዳደር ከፍተኛ የአሠራር ጉድለት እንዳለበት ዘርዝረው ለሕዝብ ይገልጡ ነበር። በዚህ ጊዜ እናታቸው ሊጠይቋቸው ሔደው ሲያዩ፤ ሺፈራው ደሣለኝ ከላይ የተገለጸውን ስበካ ሲያካሒዱ ሲያገኟቸው፤ ‹‹ምነው ልጄ እንዲህ ታደርገኛለህ? ታስለቅሰኛለህ›› በማለት ምርር ብለው አልቅሰው ይጠይቋቸዋል። አቶ ሺፈራውም "እናቴ፣ አንቺ ብቻ እኮ አይደለሽም የምታለቅሽው፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እናት እኮ ነው የሚያለቅሰው" ብለው መለሱላቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ደግሞ አቶ አዱኛ ቢተዋ ከጐንደር፣ አቶ ካሳሁን አሸኔ ከኢሊባቡር፣ አቶ መንግሥቱ ገዳሙ ከአዲስ አበባ ከባንክ፣ አቶ ሰይፉ አካለ ወልድ ከአዲስ አበባ ፍርድ ሚኒስቴር፣ ሻለቃ አበበ በላቸው ከሐረር /ጂጂጋ/ ፖሊስ፣ አቶ አያሌው ከአስኮ ጫማ ፋብሪካ አዲስ አበባ፣ አቶ መኮንን ዋሴ /ከአሜሪካን ኢምባሲ/ አቶ ጥበብ አወቀ እና አቶ ኃይለ እየሱስ ደስታ ከተባሉ ሁለት ወጣት ግብረ አበሮቹ ጋር፣ አቶ ለማ ፍሬሕይወት /የጄኔራል መንግሥቱ የቅርብ ዘመድ/ ከቡና ቦርድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ አቶ ብዙነህ ሺፈራው በተባባሪ ከቡና ቦርድ፣ አቶ ተስፋዬ ዘለለው ከአዲስ አበባ እና አቶ ደመላሽ ከአዲስ አበባ ደግሞ ከየቦታው ተይዘው መጥተው እሥር ቤት የገቡ ናቸው።

ከ፲፱፻፹፪ እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ከፈታውራሪ ኃይሉ ክብረት ጋር በፀረ መንግሥት ወንጀለኛነት ተጠርጥረው ተይዘው ወህኒ ቤት የገቡት ደግሞ ፊታውራሪ በየነ ይመር ከጐጃም፣ አቶ ጫኔ በላይ ከጐጃም፣ የመቶ አለቃ ሙሉጌታ አብርሃም ከሆለታ ጦር ት/ቤት፣ የሻምበል ታደሰ ተክሌ ከአየር ኃይል፣ አቶ ይስሐቅ ቀለመወርቅ ከንግድ ባንክ እና አቶ በቀለ ሥዩም ከአዲስ አበባ ሲሆኑ፤ ፊታውራሪ ደስታ ጦና (ከወላይታ ከነቢትወደድ ነጋሽ ጋር አድመው ምስጢር አውጥተው ምስጢረኞቻቸውን አስያዙ) እየተባለ ይወራባቸው የነበሩት የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ሲያሤሩ ተደረሰባቸው ተብለው ተይዘው ወህኒ የገቡና ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ (የፊጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥ የነበሩና በታኅሣሡ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መጀመሪያ ተባባሪ ሆነው በኋላ አቋማቸውን በመለወጥ ከዘውድ ጠባቂው ጋር በመወገን የመንግሥት ለውጡን ያከሸፉ፤ እንደገና በኋላ ደግሞ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ሲያሤሩ ተገኙ ተብለው ወህኒ የገቡ) ይገኙባቸዋል። ከዚህ ሌላም ድርጅት አቋቁመው በኮሎኔል እምሩ ወንዴ መሪነት የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ሲያሤሩ ተደርሶባቸዋል ተብለው ተይዘው ወህኒ የገቡት ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ፣ የሻምበል ደገፉ ማሩ /በኋላ ኮሎኔል/፣ የሻምበል ሺፈራው ከበደ፣ የሻምበል ነጋሽ፣ የሻምበል ዘውዴ ወልደ ቂርቆስ እና የሻምበል ጥላዬ ዳምጤ ነበሩ።

ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ስመለስ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በቀረብን በሦስተኛው ቀን ጥንድ ጥንዳችን በሰንሰለት ተቆራኝተን በሽፍን መኪና በድጋሚ ፍርድ ቤት ቀረብን። በዚህ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ተከሳሾችን ጉዳይ እንዲያይ የተሰየመው ችሎት እንደ አንደኛ ደረጃ ተከሳሾች ችሎት «በወታደራዊና ሲቪል ዳኞች ኮርት ማርሻል» በጣምራ በተሰየሙ ዳኞች እንዲታይ ስለተወሰነ፤ የዳኞች ለውጥ ተደረገ። በዚህ መሠረት መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. በዋለው ችሎት ዳኞቹ ቀኛዝማች ጣሰው አየለ፣ ኮሎኔል ይልማ ሺበሺና አቶ ከበደ ከልል ሲሆኑ፤ ዓቃቤ ሕግ አቶ ቦጋለ ውቤ ነበሩ። በሁለተኛው ችሎትም እንደዚሁ የዳኛ ለውጥ ተደርጐ ኮሎኔል ጥ–ጋሻው ፀምሩ ተደለደሉ።

ችሎቱ ሥራውን ሲጀምር ስለነበረው አጠቃላይ የፍርዱ ሒደት ማሳያ እንዲሆን የኔን ክርክር የመኸል ዳኛው በንባብ ያሰሙትን ክርክርና ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አቀርባለሁ።

> ...ተከሳሹ ባለፈው ችሎት የሚከራከርለትን ጠበቃ ይዞ እንዲቀርብ ታዞ ለነበረው አቶ ታደሰ ድልነሳሁን አድርጌአለሁ ብሏል። አቶ ታደሰ ድልነሳሁም ቀርበው እከራከርለታለሁ ሲሉ አመልክተዋል። ዐቃቤ ሕጉ ፬ ምስክሮች ቀርበውልኛልና ይሰማልኝ ሲሉ አመልክተዋል። የተከሳሽ ጠበቃ የክሱ አንቀፅ በተከሳሹ ላይ የተመለከተው ቁጥር ፪፻፶፪ ተከሳሹን እወህኒ የሚያሳሥረው ባለመሆኑ በዋስ እውጪ እንዲቆይ ይደረግልኝ ሲሉ አመልክተዋል። ዐቃቤ ሕግ በመጀመሪያው ጥቅስ የተመለከተው ቁጥር ፪፻፵፰ ቢሆንም፤ በዚሁ ዘርፍ ተከታይ ቁጥር ላይ

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለሚመራ ወንጀሉ እንደቀላል ታይቶ በዋስ ሊቆይ አይገባም እቃወማለሁ ብለዋል።

## ት ዕ ዛ ዝ

የተከሳሽ ጠበቃ ተከሳሹ በዋስ እውጪ ይቆይልኝ ያሉትን አልተቀበልናቸውም፤ የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች ለመስማት የተከሳሹ ጠበቃ ከተከሳሹ ጋር ሳይነጋገሩበት የማይቻል ስለሆነ በሚቀጥለው ቀጠሮ ምስክሮች እንዲሰሙ ለመጋቢት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ተቀጠረ።

በመጋቢት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. በዋለው ችሎት ደግሞ የዳኞች መሟላት፣ የዐቃቤ ሕጉ አለመለወጥና እኔና ጠበቃዬ መቅረባችን ከተረጋገጠ በኋላ የምስክሮች ቃል መደመጥ ተጀመረ።

አንደኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ አባተ ማህሉ ዕድሜ ፭፫ ዓመት ሥራ መሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪ መሆኑን ሲጠየቅ ከመለሰ በኋላ ምስክርነቱን እንዲህ ሲል ሰጠ። ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በመሐንዲስ ኮሌጅ ትምህርት ቤት ከጧቱ በ፫ ሰዓት ተከሳሹን ቆሞ አይቸዋለሁ። ልጆቹ ከበውት ነበር። ወዲያው "ሌሎቹ የኮሌጅ ተማሪዎች ሲሰሙ እናንተ እስካሁን ባለመስማታችሁ አዝናለሁ። እኔ ተልኬ የመጣሁት ስለ አዲሱ መንግሥት ልገልጽላችሁ ነው። በዚህ በአዲሱ መንግሥት ደንብ አንድ ሰው በከተማው ውስጥ ከሦስት ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ቦታ እንዳይኖረው ገደብ ይደረጋል። ነገሩን ግርማዊነታቸው አውቀውታል። አሽከሮቻቸውንና ወጥ ቤታቸውን ይዘው ሔደዋል። ሌሎች የኮሌጅ ተማሪዎች ነገሩን ሰምተው ተሰልፈው ሊሔዱ ነውና እናንተም ደም እንዳይፈስ የሚል ጽሑፍ ይዛችሁ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ብትሄዱ መልካም ነው" ብሎ ተናግሯል። ካለ በኋላ ተማሪዎች ይጠይቁት ነበር። ጥያቄውን ሁሉ ላስታውሰው አልችልም። ተከሳሹም መልስ ይሰጥ ነበር። ጫጫታ ስለበዛ የሰጠውን መልስ አላስታውሰውም። መልስ ሲሰጥ ግን ሰምቻለሁ። በመጨረሻ፣ ደም እንዳይፋሰስ የሚል ጽሑፍ ይዛችሁ ብትሔዱ ይሻላል ብሎ ተናገረና ሔደ" ሲል መሰከረ።

ዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ በቃኝ ካለ በኋላ ጠበቃዬ ለምስክሩ ጥያቄ አቅርቦ ምስክሩ የሚከተለውን መለሰ። ደም እንዳይፈስ የሚል ቃል ጽፈን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሚል አውቶብስ መጣና በአውቶቡስ ተሣፍረን ወደ ፒያሳ ከዚያም ወደ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ድረስ ሔድን። ተከሳሹ እኛ ዘንድ ከመምጣቱ በፊት አዋጁን በራዲዮ ሰምተናል ካለ በኋላ ለጠበቃዬ ጥያቄ ምስክሩ «ደም እንዳይፋሰስ የሚለውን ጽሑፍ እንዲነበብ በግልፅ ይዘን በአውቶቡስ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ከደረስን በኋላ ከአውቶቡስ ወርደን ከሌሎች ኮሌጅ ተማሪዎች ጋር ተደባልቀን በሰልፍ በከተማው ውስጥ ተዘዋውረናል» አለ።

ሁለተኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ዓለማየሁ ተፈራ ዕድሜ ፵፭ ዓመት ሥራ መሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪ መሆኑን ሲጠየቅ ከመለሰ በኋላ እኔን «ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. መሐንዲስ ኮሌጅ ትምህርት ቤት ከጧቱ በግምት ሁለት ሰዓት ተኩል

በሚሆንበት ጊዜ መጥቶ አይቼዋለሁ።» ካለ በኋላ እኔ ለተማሪዎቹ ንግግር ሳደርግ ንግግር ከጀመርኩ በኋላ መድረሱንና ተማሪዎች ይጠይቁኝ እንደነበር ገለጸ።

> እርሱም ይመልስላቸው ነበር። ዐላማው እኛ ሰላማዊ ሰልፍ እንድናደርግ ለመቀስቀስ ነው። ስለ ጃንሆይ መመለስ ልጆች ሲጠይቁት፣ አይመለሱም ብሏል። ልጆቹ የጠየቁት ጃንሆይ ይመለሳሉ ወይም አይመለሱም ብለው ነው። በአልጋ ወራሽ የተነገረውን የዐዋጅ ቃል በሬዲዮ ሰምተናል፡ የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ ነውና እናንተም ደም እንዳይፋሰስ የሚል ጽሑፍ ይዛችሁ ሒዱ አለ። በአዲሱ መንግሥት አንድ ሰው የከተማ ቦታ ከሦስት ሺህ ካሬ ሜትር የበለጠ ቦታ እንዳይዝ ገደብ ይደረጋል። እያንዳንዱ ሰው ከማልሚያ ጋር ሦስት ሦስት ጋሻ መሬት እንዲያገኝ ያደርጋል ሲል ተናግሯል። ትዝ የሚለኝ እስከዚህ ድረስ ነው። ስለ ግርማዊነታቸው እንድም የተናገረው መጥፎ ነገር የለም። ስለ አዲሱ መንግሥት አቋም በራዲዮ እንደተነገረው "ፕሬዚዳንቱ አልጋ ወራሽ ናቸው ግርማዊነታቸው አይመለሱም" ፲፮ ወጥ ቤቶቻቸውን ሳይቀር ይዘው ሔደዋል ብሎ ተናግሯል።

አለ።

ጠበቃዬ ለጠየቀው ጥያቄም «በከተማ ቦታ አዲሱ መንግሥት አንድ ሰው ከሦስት ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ በላይ እንዳይዝ ይደረጋል ሲል የተናገረው፣ ተማሪዎች አንድ ሰው ብዙ ቦታ የያዘ ሆኖ ሌላው ሰው አነስተኛ ቦታ ይዟል፣ ይህ እንደምን ይሆናል ብለው ስለጠየቁት ነው» አለ። ወደሰልፉ ሲሔዱ ስለማየቱ ለጠየቀው ደግሞ «ደም እንዳይፋሰስ የሚል ቃል ተማሪዎች ጽፈው መሔዳቸውን ዓላየሁም፣ እኔም አልሔድኩም።» ብሎ መለሰ።

ሦስተኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ሞላ ወልደ ሥላሴ ዕድሜ ፳፩ ዓመት ሥራ መሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪ ካለ በኋላ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ተከሳሹን መሐንዲስ ኮሌጅ ዓይቸዋለሁ ማለቱ ተገለጸ። በዚሁ መሠረት የምስክሩ ቃል እንደሚከተለው ተነበበ።

> እኔ ከመኝታ ቤት ወደ ምግብ ቤት ስሔድ ተከሳሹን አገኘሁትና ሌሎችንም ተማሪዎች ጭምር ጠራንና ወደ መጫወቻ ክፍል ሔድን። ተከሳሹ ወዲያው ንግግር ጀመረ። አሁን እኔ ተልኬ የመጣሁት አዲስ ሕዝባዊ መንግሥት በሚል ስም መቋቋሙን ልነግራችሁ ነው። እንደሌሎቹ ተማሪዎች እናንተም ሰላማዊ ሰልፍ እንድታደርጉ ነው አለ። ሐሣቡን እኛ ስላልደገፍነው ለሁሉም ነገር ሌሎቹ ተማሪዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ እናንተም ደም እንዳይፋሰስ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጉ አለን። እኛም በዚሁ መሠረት ደም እንዳይፋሰስ የሚል ጽሑፍ ይዘን ሰላማዊ ሰልፍ አደረግን። ዐዋጁ የአልጋ ወራሽ ቃል ነው ተብሎ የተነገረውን አልጋ ወራሽ የተናገሩት ተገደው ነው? ወይስ እንደ ምን ነው? ብለን ተከሳሹን ብንጠይቀው፣ አልተገደዱም ሲል መለሰልን። አልጋ ወራሽ በምን ማዕረግ እንደሆኑ በዐዋጅ የተነገረውን አላስታውስም

አለ።

> በተከሳሹ ጠበቃ ተከሳሹ ከኛ ዘንድ ከመምጣቱ በፊት በዐዋጅ የተነገረውን ቃል በሬዲዮ ሰምተናል፤ ልዑል አልጋ ወራሽ ሥልጣን የጨበጡ ለመሆናቸው በዐዋጁ ቃል ተረድተነዋል። ተከሳሹ የመጣሁት ተልኬ ነው ማለቱ እርግጥ ነው፤ የተላከው ከየት እንደሆነ ግን አልገለጠ ልንም

አለ። ተብሎ ከተነበበ በኋላ የችሎት ሰዓት ስላለፈ ቀሪው በይደር ተቀጠረ።

እንዲሁ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አስፈላጊዎቹ የፍርድ ቤት ደንቦች መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ፤ የዐቃቤ ሕጉ ምስክሮች ቃል ሪፖርት መቅረብ ጀመረ። አራተኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሻምበል ተፈራ ኪዳኔ፣ ዕድሜ ፵፱ ዓመት፣ ሥራ ቀድሞ የክብር ዘበኛ ባልደረባ አሁን ወደ ጦር ሠራዊት የተዛወረ፣ አድራሻ መሐንዲስ ኮሌጅ ትምህርት ቤት ተብሎ ከተነበበ በኋላ፤ «ተከሳሹን ታኅሣሥ ፮ ቀን ፶፫ ዓ.ም. መሐንዲስ ኮሌጅ ከሟቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ተማሪዎቹ በተሰበሰቡበት ንግግር ሲያደርግ ዓይቼዋለሁ፤ በንግግሩም «ተልኬ የመጣሁት አሁን ስለተቋቋመው ስለ አዲሱ መንግሥት ለሌሎቹ ተነግሮ ለናንተ ሳይነገር ስለቀረ ልነግራችሁ ነው፤ ይህ አዲስ የተቋቋመው መንግሥት ሕዝባዊ መንግሥት ይባላል» ብሎ ሲናገር ሰምቼአለሁ። ስለማለቱ ከተነበበ በኋላ ተማሪዎች አቀረቡለት ስለተባለው ጥያቄም «ትላንትና ልዑል አልጋ ወራሽ በዐዋጅ ሲናገሩ ሰምተናል፣ ይህ ንግግር የሳቸው ለመሆኑ እንደምን ለማወቅ እንችላለን ብለው ቢጠይቁት ተከሳሹ የተናገሩት ራሳቸው አልጋ ወራሽ ናቸው።» አለ ብሎ መሰከረ።

የዳኛው ንባብ ቀጥሎ

> እኔ ለናንተ እንድነግራችሁ የተላክሁት የአዲስ አበባና የሕንፃ ኮሌጆች ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ። እናንተም እንደነሱ ሰላማዊ ሰልፍ እንድታደርጉ ነው ሲል መለሰላቸው፣ ከዚህ በኋላ ካንድ አንድ ተማሪዎች በማናውቀው ነገር እንደምን ሰልፍ እናደርጋለን? በማለት ተናገሩ፣ ተከሳሹ ወዲያው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ አለባችሁ ከሌሎች መለየት የለባችሁም አለ፤ ተማሪዎችም ምን ይዘን ነው የምንሰለፈው? የምንሰለፈውስ የት ነው? ብለው ጠየቁት በዚህ ጊዜ ተከሳሹ የምትሰለፉት አንዳንድ ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ነው፣ ይኸውም ጽሑፍ የሚጠቅመው ሁለት ወንድማማቾች ደም ሊፋሰሱ ነውና ደም እንዳይፋሰሱ ነው። እናንተ ካልተጨመራችሁ ሰላም ሊሆን አይችልምና ተሰለፉ አላቸው። ወዲያው ተማሪዎቹ አንዳንድ ጥያቄ ሲያደርጉለት ጥያቄና መልስ አያስፈልግም እህል ከበላሁ ሁለተኛ ቀን ሆኖኛል። ይልቁንስ ቁርስ አብሉኝ አለ። እንደገና ተማሪዎች በማስገደድ ጥያቄ አደረጉለት ጥያቄውም ይህ ነገር የሆነው በምን ምክንያት ታስቦ ነው? በማለት ነበር ተከሳሹ ጉዳዩን ጌቶችም አውቀውታል የሔዱት ፈቅደው ነው አለ። አለወትሯቸው የቅርብ አጃቢዎቻቸውንና ፲፮ የሚሆኑ ቦዮቻቸውን ሳይቀር ይዘው ሔደዋል ሲል መለሰ። የማስታውሰው ይህንን ነው። ከዚህ በኋላ ተከሳሹ ከዚያው እንዳለ የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ አውቶቡሱ መጣና ተማሪዎቹ በሙሉ ሔዱ። እኔም በአውቶቡሱ ፒያሳ ኪንግ ጆርጅ ባር አጠገብ ወረድኩ። ሌሎች ተማሪዎች በአውቶቡሱ እንዳሉ ወደ አዲስ

ከተማ ሔዱ። ረቡዕ ዕለት ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. የአልጋ ወራሽ ቃል ነው ተብሎ የተነገረውን ዐዋጅ በሬዲዮ ሰምቻለሁ አለ።

ከዚህ በኋላ ጠበቃው ጥያቄ በቃኝ አለ። ዐቃቤ ሕጉ ያቀረበው የሰው ምስክር ስላአበቃ፤ «ተከሳሹ የሰጠውን የዕምነት ቃል አቅርቤያለሁ። ይመዝገብልኝ» ሲል ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. የተጻፈ አራት ገጽ የዕምነት ቃል አቅርቦ ፩ኛ የክሳሽ ማስረጃ ይመዝገብልኝ ሌላ የማቀርበው ማስረጃ የለኝም ነገሬን ዘግቼአለሁ» ስለማለቱ ዳኛው እንዳነበቡ ጠበቃዬ የጽሑፍ ማስረጃ ግልባጭ ይድረሰኝና ጽሑፉን ተመልክቼ መከላከያ የማቀርብ መሆን አለመሆኔን ወደፊት እመለከታለሁ አለ። ከዚህ በኋላ ዳኛው የሚከተለውን ትእዛዝ አነበቡ። ዐቃቤ ሕጉ ያቀረበውን የጽሑፍ ግልባጭ ለተከሳሽ ጠበቃ ይሰጥና የተከሳሹ ጠበቃ መከላከያ የሚያቀርብ መሆን አለመሆኑን ለመስማት ለመጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ተቀጠረ።

## ውደ ቀጠሮ ክፍል መዛወር

በዚህ አኳኋን ዕለት በዕለትና በማልስት ፍርድ ቤት እየተመላለስን አንድ ወር ያህል በዓለም በቃኝ ከቆየን በኋላ አደገኞች እንዳልሆንን ተገምቶ፤ ከዓለም በቃኝ ላላ ያለ ጥበቃና ቁጥጥር ባለበት በነፍስ ማጥፋትና በጦር መሣሪያ ዘረፋ ወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ገና ያልተፈረደባቸው እሥረኞች በሚቆዩበት ቁጥር ፩ ቀጠሮ ክፍል አዘዋወሩን። ቀጠሮ ቁጥር ፩ ቤት ከዓለም በቃኝ የሚለየው ጧት በሩ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ማታ እስቲዘጋ ድረስ እዚያው ግቢ ውስጥ እንደልብ መዘዋወር የሚቻልበት፣ የክፍሉ ሦስት ማዕዘን በእንጨት የተሠራ ለእሥረኞች መኝታ የሚያገለግል ቆጥ ያለው በመሆኑ ነው። እኛም በዚህ ክፍል ተደልድለን መኖር ጀመርን። በመጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. አስፈላጊው ደንብ ስለመሟላቱ ተረጋግጦ ችሎት ብንቀርብም የችሎት ሰዓት ስላለፈ ነገሩን ለመስማት አይቻልም በሚል በአዳሪ ለመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ተቀጠረ።

*መጋቢት ፴ ቀን በዋለው ችሎትም*

ዳኞች አልተለወጥንም ዐቃቤ ሕጉ የመቶ አለቃ ተሾመ ወልደ ሰማዕት ተከሳሹ መከላከያ ምስክር የሚያቀርብ ወይም የማያቀርብ መሆኑን ለዛሬ ቀጠሮ ስለነበረ የተከሳሹ ጠበቃ ተከሳሹ መከላከያ ሊያቀርብ አይገባም። ምክንያቱም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተከሳሹ የተከሰሰበት አንቀፅ የከለከለውን ነገር ለማድረጉ አልመሰከሩበትም። ፩ኛው ምስክር የመሰከረው ቃል ባጭሩ "ልጆች ከበውት ቆመው ነበር ጊዜውም ፫ ሰዓት ይመስለኛል ተልኬ ነው የመጣሁት አለ። ደም እንዳይፋሰስ የሚል ቃል ጽፋችሁ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሒዱ" አለ። ከተማሪዎች ብዙ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር ጫጫታው ስለበዛ ጥያቄውንና መልሱን አልሰማሁም ሲል እንደዚሁም ፪ተኛው ምስክር አቶ ዓለማየሁ ተፈራ ስለ ሰዓቱ ከ፩ኛው ምስክር በመለያየት ተከሳሹ ጠዋት በ፪ ሰዓት ንግግር ሲያደርግ ደረስኩ። ተከሳሹ በዚያን ጊዜ የመጣበት ዋና ዐላማ ሰላማዊ ሰልፍ እንድናደርግ ነበር። ይኸውም ቀደም ብሎ ከልዑል አልጋ ወራሽ በተነገረው መሠረት ሌሎቹ

> ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ ነው እናንተም «ደም እንዳይፋሰስ የሚል ጽሑፍ ያዙና ሰልፍ አድርጉ»

ማለቴን መሰከረ።

ሦስተኛውም ምስክር ሞላ ወልደ ሥላሴ አሁን ተልኬ የመጣሁት ደም እንዳይፋሰስ እንደሌሎቹ ተማሪዎች ሰልፍ እንድታደርጉ ብሎ አለን ሲል መስክሯል። ፬ተኛው ምስክር ሻምበል ተፈራ ኪዳኔ እኔ ተልኬ የመጣሁት ሁለቱ ኮሌጆች ሰላማዊ ሰልፍ ስለሚያደርጉ ሁለቱ ወንድማማቾች ደም እንዳይፋሰሱ እናንተም ሰላማዊ ሰልፍ እንድታደርጉ ነው ካለን በኋላ፣ ወዲያው ሲቪል የለበሰ ሰው መጥቶ ጥያቄና መልስ አያስፈልግም በቃ ብሎ ተቆጣው።» ሲል መመስከሩ ተነበበና የጠበቃዬ ክርክር ቀጠለ። በዚህ መሠረት ተልኬ የመጣሁ ለመሆኑ ከላይ በተዘረዘሩት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ማረጋገጣቸው፣ የተከሰስኩትም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፩፻፹ አንቀፅ የተከለከሉትን ወንጀሎች ለመፈፀም ሳይሆን፣ ይህ የተጠቀሰው አንቀፅ የሚፈቅደውን ለመፈፀም የተላኩ ለመሆኑና ይኸንኑ የፈፀምኩ ለመሆኑ ምስክሮቹ ማረጋገጣቸው፣ በዚህ አንቀፅ መሠረት እራሴ ያላመንኩ ለመሆኑ መረጋገጡ፣ በሕዝብ ላይ በሕጉ መሠረት ፀጥታ እንዲሆን ጥልና ፍጅት እንዳይሆን ለሰላም እንዲዘጋጁ የተናገርኩ ስለሆነና በአንቀፅ የተፈቀደውን የሰላም አኳኋን እንደፈጸምኩ እንጂ እንቀፁ የሚከለክለውን ግብር ባለማድረጌ ደም እንዳይፋሰስ ማለቴም ያብዛኛውን ሕዝብ ሕይወት ከጥቃት ለማዳን ስለሆን በዚህ አንቀፅ መሠረት ፍጅት ተብሎ የተጠቀሰ ስለሌለ ይህ አንቀፅ ደንበኛዬ ከሠራው ወንጀል ጋር የተቀራረበ ወይም ይመሳሰላል ብሎ ክስ ማቅረብ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፪ ንዑስ ቁጥር ፩ በዚህ ቁጥር በመጨረሻ አረፍተ ነገር ክልክል ስለሆነ፣ ደንበኛዬ መከላከያ ሊያቀርብ ስለማይገባ በነፃ ይለቀቅልኝ ሲል ማመልከቱ ተነበበ።

የዐቃቤ ሕጉን ጥያቄም አስመልክቶም ከአንድ እስከ አራት የቀረቡት ምስክሮች በተከሳሹ ላይ የመሰከሩበት በሚገባ ስለሆነ፣ ተከሳሹ መከላከያውን ሊያቀርብ ይገባል ሲል ስለማመልከታቸው ካነበቡ በኋላ የሚከተለውን የእኔ ጠበቃ ያመለከተውንና ዐቃቤ ሕጉ ያመለከተውን መዝገቡን መርምሮ መከላከያ ይሰማል ወይም አይሰማም ብሎ ትእዛዝ ለመስጠት ለሚያዚያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ተቀጠረ።

ቀጣዩ ቀጠሯችን ሚያዚያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. እንደመሆኑ በዕለቱ ችሎት ቀርበን አስፈላጊው ደንብ መሟላቱ ተረጋግጦ ፍርዱን ሲቀጥል፣ ‹‹...ባለፈው ችሎት የተከሳሽ ጠበቃ ተከሳሹ በተከሰሰበት አንቀፅ በተጠቀሰው በጥፋተኛነት ስላልተመሰከረበት መከላከያ ማቅረብ አይገባውም በነፃ ይለቀቃል ብሎ ያመለከተውን ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም።›› ይልና ትዕዛዙን ያስከትላል። ትዕዛዙም ‹‹ተከሳሹ መከላከያውን ያቅርብ ብለናል።›› የሚልና መከላከያዬን ለመስማት ለሚያዝያ ፴ ቀን ፺ ዓ.ም እንደተቀጠረ የሚያዝ ነበር። ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.ም በዕለቱ የመከላከያ ምስክር ሊሰማ ተቀጥሮ የነበረ ቢሆንም፣ ጠበቃዬ ይኸንን በመሰለ ለተከሰሱ ወንጀለኞች በ፪ተኛው የወንጀል ፍርድ ቤት በዛሬው ቀን ምስክር የሚሰማ በመሆኑ መከላከያዎችን ላቀርብ አልቻልኩም አመልክቷል በሚል ቀጠሮው አዳሪ

ሆኖ፣ መከላከያውን ለማሰማት የምስክሮቹን ስም ዝርዝር ተጠይቆ መጥሪያው ይጻፍ ተብሎ ለግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ተቀጠረ።

ስለዚህ ግንቦት ፩ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ስቀርብ «...ተከሳሽ ከጠበቃው ጋር ቀርቧል የመከላከያ ምስክሮችም ቀርበዋል። ተከሳሹ ሦስት ምርጫ ተሰጥቶት ምዬ እመሰክራለሁ ብሎ መርጧል።» በሚል ተነበበና ዝርዝሩ ቀጠለ። በዚህ መሠረት በሕግ እንድምል ተደርጎ የሰጠሁት የምስክርነት ቃል ተነበበ። ዝርዝሩም ከታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በፊት በግርማዊ ጃንሆይ ልዩ ካቢኔ መምሪያ እሠራ እንደነበር፣ አለቃዬ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እንደነበር፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በካቢኔ ሥራ ሚሊቴርንና ሲቪልን በማጣመር የበላይ ሹም እንደነበር፣ ታኅሣሥ ፬ እና ፭ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አብዛኛውን ትዕዛዝ የተቀበልኩት በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እንደነበር፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከሌሎቹ ሠራተኞች ጋር ከቀኑ በግምት ከ፲፩ ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ መሥሪያ ቤት ተሰብስበን ትእዛዝ እንድንጠባበቅ አዞን ስንጠባበቅ እንደነበር፣ ሁለት ሰዓት ሲሆን፣ እኛ የካቢኔ ክፍል ሠራተኞች ከምንሰበሰብበት ክፍል ውስጥ እንዳለን ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ መጥቶ እኔን አንደኛ ክፍለ ጦር ሔደህ ሁኔታውን ዓይተህ አትመጣም ወይ? ብሎ ሲያናግረኝ ጄኔራል መንግሥቱ መጡና አሁን ጊዜው መሽቷል፣ ሔዶም ቀርቶም የሚሰጠው ጥቅምና ጉዳት የለምና አይሒድ ይቅር ሲሉ በቁጣ ቃል መናገራቸውን፣ ትንሽ ቆይቶም ሾፌራቸው እዚያ ምን ታደርጋላችሁ ብሎ በጠመንጃ አፈሙዝ ከበረንዳው ወደ ቁጥር ፴፬ ክፍል አመልክቶ አስገብቶኝ ከብዙ የክብር ዘበኛና የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ መኮንኖች ጋር እዚያው እንዳደርኩ፣ ታኅሣሥ ፭ ቀን ማታ ጄኔራል መንግሥቱ ኮተቤ ላይ ስለ ታገደው ጦር ለሻለቃ ተፈራ በላይ ንግግርና ማስታወሻ መጻፍ እንዳበቃ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ ከሻለቃ መላኩ በቀለና ከሻለቃ ተፈራ በላይ ጋር ወደ ኮተቤ ሔዳችሁ ከደብረ ብርሃን የመጣውን ጦር አግባብታችሁ ወደመጣበት እንዲመለስ አድርጉ ተብለን ስለመታዘዛችን የሰጠሁት ቃል ነበር።

ከፎቁ ወርደን ከመኪና ልንገባ ስንል ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ ከፎቁ በመስኮት ብቅ ብለው ሁለቱ መኮንኖች ወደታዘዙበት እንዲሔዱ እኔ ወደፎቁ ተመልሼ እነሱን እንዳገኝ እንደጠሩኝ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የመሐንዲስና የሕንፃ ኮሌጅ እንዲሁም የማሠልጠኛ ተቋማት ተማሪዎች በአጠቃላይም ምሑራኑ እንቅስቃሴውን እንዲደግፉ ስለለውጡ መንፈስ በቂ ማብራሪያ መስጠት ስለሚያስፈልግ ረቡዕ ታኅሣሥ ፯ ቀን ማታ ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የማታ ተማሪ ከነበረው ከሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ፣ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ባልደረባ አቶ መስፍን ወልደ ሚካኤልና አቶ ኤፍሬም ፀሐይ ጋር ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እንደሔዱና ስለእንቅስቃሴው ለተማሪዎቹ እንደገለጹ፣ ተማሪዎቹ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቃል ሰጥተዋቸው ተመልሰው ይኸንኑ ሪፖርት ማድረጋቸውን ገልጸውልን፣ መሐንዲስና ሕንፃ ኮሌጅ እስካሁን የሄደ ሰው እንደሌለ

በመንገር እኔ ወደ ሸዋ ከምሔድ መሐንዲስና ሕንፃ ኮሌጅ ሔጄ ስለለውጡ ቅስቀሳ እንዲደርግ ከመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ /ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ፲ተኛ ተከሳሽ/ ጋር ወደ መሐንዲስ እና ሕንፃ ኮሌጅ እንድንሔድ ስለመታዘዛችን መመስከሬ ተነበበ።

ቀጥሎም መሐንዲስ ኮሌጅ ሔደን እኔ ንግግር ሳደርግ የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ውጪ እንዲቆይ ተነግሮት እንደ ነበር፣ እሱ እደጅ እንደቆየና እኔ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቼ አልፎ አልፎ በየጓደኞቻቸው ተሰባስበው ቆመው የነበሩትን ልጆች እተሰበሰቡበት ሄጄ የልዑል አልጋ ወራሽን ዐዋጅ እንዳነብላቸው መታዘዜን ነግሬ እንዲሰበስቡልኝ ማድረጌን፤ ተማሪዎቹም እሺ ብለው ወደ ማረፊያ ቦታቸው እንደወሰዱኝና የልዑል አልጋ ወራሽን ዐዋጅ ማንበብ ስጀምር፣ አንዱ ተማሪ አቋርጦ ዐዋጁን ስለመሰማታቸው ተናግሮ ሌላ የምትነግረን እንዳለ ንገረን እንደአለኝ፣ የታዘዝኩት ይኸንኑ ዐዋጅ እንዳስረዳቸውና የጦር ሠራዊት በመንግሥቱ ላይ በማመፁ ደም እንዳይፋሰስ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ እንዲገላግሉ እንዳሣስባቸው መሆኑን ተናገርሁ። ለሰላማዊ ሠልፉም በትምህርት ቤቱ የሚገኘውን ሰንደቅ ዐላማ ይዘው "ደም እንዳይፋሰስ ሰላም እንፈልጋለን የሚል ጉልህ ጽሑፍ ይዘው እንዲወጡ ማስረዳቴን፣ ከዚያም ብዙ ጫጫታና ጥያቄም በተማሪዎቹ በኩል እንደቀረበ፤ አንዱም ግርማዊ ጃንሆይን ምን የደረሰባቸው ይመስልሃል? የሚል ሲሆን፤ እኔም እንደናንተው የተፍታታ ነገር አላገኘሁም ብዬ እንደመለስሁ፤ ነገር ግን እኔም ጠቅላይ መምሪያ ስላደርኩ እንደደከመኝ፣ ፊቴን ያልታጠብኩ ቁርስም ያላደረኩ መሆኑን ገልጬ ይልቅስ ቁርስ አብሉኝ እንዳልኳቸውም የሰጠሁት ቃልም ተነበበ።

ከዚያም ወደ ውጭ ከመውጣቴ በፊት ዐዋጁን ማንበብ አቋርጬ ለምጠየቀው መልስ ከምሰጥበት ቦታ አንድ ጠይም ሰው ረዘም ያለ የሲቪል ልብስ የለበሰ አጭር ድግን መትረየስ የያዘ ከክፍሉ ገብቶ "ንግግርህን ቶሎ ጨርስ ወደ ሌላ ቦታ ትሔዳለህ" ስላለኝ፤ ቁርስ እንዳደርግ ልጆቹ ወደ ገበታ ቤት እንደወሰዱኝ፤ እዚያም ቁርስ በማደርግበት ጊዜ አንዱ ተማሪ ሕዝባዊ መንግሥት ማለት ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጉም ምን ማለት ነው ብሎ ቢጠይቀኝ «ሬፖፕሊክ» ወይም «ኰንስቲቲቱሽናል ሞናርኪ» ማለት ይቻላል ብዬ እንዳስረዳሁ፤ ከተማሪዎቹ አንዱም በመሬት በኩል በከተማ ውስጥ አንድ ሰው ብዙ ሺህ ካሬ ሜትርና ከዚያም በላይ ቦታ ሲኖረው አብዛኞቹ ኑዋሪዎች ምንም የሌላቸው በመሆኑ ባዲሱ መንግሥት እንዴት እንደሚሆን ቢጠይቀኝ ትንቢት እንዳልነግርህ ነቢይ አይደለሁም ብቻ ሁሉንም በሚያስማማ መንገድ ያካፍል ይሆናል ስል እንደመለስኩለት፤ በመንግሥት ሥራ ተቀጥሬ ሦስት ዓመት እንዳገለገልኩ በዚህም ጊዜ አንዳችም ጥፋት ወይም የተከሰስኩበት ነገር እንደሌለ መሰከርኩ። በታኅሣሥ ፭ እና ፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ካለቃዬ በመታዘዝ በሠራሁት ሥራ ምንም ያደረግሁት ጥፋት እንደሌለ፣ የሠራሁት ሥራ ወንጀል አለበት ብዬ ባስብ ኖሮ ተመልሼ ከሥራ ላይ የማልገኝና እጄን ከሰጠሁ በኋላም ለግርማዊ ጃንሆይ ሁለት ጊዜ በጻፍኩት ደበዳቤ ያላንዳች ጥፋት ታሥሬ

ቀለብ ተከልክያለሁ፤ ፍትህ አጥቻለሁ፤ ብዬ የማላመለክት እንደነበር የተናገርኩት ሁሉ ተነበበ።

ከዚህ በኋላ በዐቃቤ ሕጉ ለተነሳው ጥያቄ ለሥራ ስቀጠር ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታማኝት ለማገልገልና የመንግሥቱንም አቋም ለመጠበቅ ምያለሁ። እኔ ያልጋውን መገልበጥ አሁን ባቃቤ ሕጉ ጥያቄ ከመስማት በቀር አስቀድሞ እንዳላወቅሁ እና ለተማሪዎቹ አሰማ ተብዬ የታዘዝኩበት የጽሑፍ ዐዋጅ በልዑል አልጋ ወራሽ ስም የሆነው የመንግሥቱን ሥልጣን ይዣለሁ የሚለውን እንደሆነና ያዋጁን ቃል ለተማሪዎቹ ያነበብኩት አንድ ደቂቃ ያህል ብቻ እንደሆን ምክንያቱም ተማሪዎቹ ዐዋጁን ሰምተነዋል ብለው ስላቋረጡኝ እንደቀረ ተናገርኩ። ንባቡን የጀመርኩበትና ያቆምኩበት ከምን ጀምሮ እስከምን ድረስ እንደሆነ ባላስታውስም ዐዋጁንና ደም እንዳይፋሰስ ለተማሪዎቹ በተናገርኩበት ጊዜ መሣሪያ አለመያዜን፣ በታኅሣሥ ፮ ቀን የተቀበልኩት አንድ ካርበባይን ጠመንጃ ከ፲፬ ጥይት ጋር ለመሥሪያ ቤቱ ወዲያው መመለሴን፣ እኔ በታኅሣሥ ፯ ቀን ጠመንጃ የያዝኩበት ምክንያት የጦር ሠራዊት በመንግሥት ላይ ዐምፇል ስለተባለ ለሕይወታችን መከላከያ ያስፈልገናል ብለን ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን አስፈቅደን እንደነበር በኋላ ግን ዐምፇል የተባለው በቀድሞው መንግሥት ላይ እንጂ ባዲሱ መንግሥት አልተባለም ሲባል ተቀብዬ የነበረውን መሣሪያ በታኅሣሥ ፲ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ለመሥሪያ ቤቱ ግምጃ ቤት ኃላፊ መልሼ ማስረከቤን ተናገርኩ።

ይህን ተከትሎ የዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ ስለ አበቃ የእኔ ጠበቃ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የዘውዱ ወራሽ ልዑል አልጋ ወራሽ መሆናቸውን ይህም በሕገ መንግሥት የተደነገገ መሆኑን ማወቄን በመግለጽ፤ መሐላ በተቀበልኩበት ጊዜ ለግርማዊ ጃንሆይና ለወራሴ መንግሥት በታማኝነት ላገለግል መማሌን የማውቅ መሆኔን ጠቅሶ፤ ይገፎው በነበርኩት ካርባይን ጠመንጃ ምንም ወንጀል እንዳልሠራሁበትና አንድ ጥይት ሳትጉል መልሼ ማስረከቤን ተናግሮ ንግግሩን አቆመ።

ከዚያም ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ፩ኛ ኤግዚቢት የተባለው በምርመራ ለፖሊስ የሰጠሁት ቃል እኔ የፈረምኩበት እንደሆነ፤ ነገር ግን ይኸንን ቃል ስሰጥ ትክክለኛውን ቃል ሳመጣ ያቋርጡና በሌላ ሰው ጉዳይ እየገቡ ይጠይቁኝ እንደነበረ እንደገናም ወደ ሥር ጥያቄ እየተመለሱ ለማረሳሳት እንዲመቻቸው ለውጠው እኔ የተናገርኩትን ትተው እነሱ የሚፈልጉትን ይጽፉ እንደነበር ተናገርኩ። ጥያቄውን በማዘዋወር የተናገርኩትን አስቀርተው ጽፈውታል እንጂ በጽሑፍ የሠፈረው ቃሌ መሆኑን አመንኩ። በፖሊስ ምርመራ ከሰጠሁት ቃልና በፍርድ ቤት ከሰጠሁት ቃል እንዲፀናልኝ የምፈልገው በፍርድ ቤት የሰጠሁት ነው አልኩ። የገጠመኝ ችግር ስለመኖሩ ስጠይቅም ፖሊሶች ቃሌን ሲቀበሉ ከማዘዋወራቸው፣ የሚጠቅመኝን ከማስቀረታቸውና በጨለማ ለሦስት ቀን ዘግተው ከማስቀመጣቸው ሌላ የደረሰብኝ

ስቃይ የለም አልኩ። ስለ ከተማ ቦታም ተማሪዎቹ ከጠየቁኝ በቀር እኔ አንዱ ሰው ይኸንን ያህል ይይዛል ብዬ አልተናገርኩም። ለተማሪዎቹ መልስ ስሰጥ ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ለጠየቁኝ ሥልጣኑን ይዘዋል ያልኩት ግርማዊነታቸው ፈቅደው አልጋ ወራሽ አድርገዋቸዋል ለማለት እንጂ ይኸንን ነገር ግርማዊነታቸው ያውቁታል ለማለት አይደለም አልኩ። ግርማዊነታቸው በጉዞ ላይ በመሆናቸው ይመለሱ አይመለሱ አልታወቀም አልኩ እንጂ፣ እኔ ራሴ እንዳወቀ ሆኜ አይመለሱም አላልኩም። በተጨማሪም ከግርማዊ ጃንሆይ ጋር የሄዱት ፲፮ አጃቢዎችና ፲፮ ቦዮች[13] ናቸው። ከነሱም የተሰማ ነገር የለም ነው ያልኳቸው ብዬ አስረዳሁ። ብዙ ጫጫታ ስለነበር የመጡት ምስክሮች ምናልባት አጣርተው ባለመስማት ካልሆነ እኔ ሌላ አላልኩም ብዬ ገለጽሁ።

ስለ ሰልፉም ተማሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ ስነግራቸው የሚሄዱት ወደ ፬ኛ ክፍለ ጦርና ወደ ክቡር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ አካባቢ እንዲሁም ሕዝብ ተሰብስቦ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ መሆኑን መንገሬን፣ ትዕዛዙን ጄኔራል መንግሥቱና ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሲሰጡኝ ሌላም ሰው ባለበት መሆኑን፣ የመከላከያ ምስክሮች የማቀርባቸው ሦስቱ ካለቆቼ ለመታዘዜ የሚያውቁ መሆናቸውን፣ ሦስቱ ደግሞ ለመልካም ጠባዬ የሕይወት ታሪኬን የሚያውቁልኝ መሆናቸውን የልዑል አልጋ ወራሽ ዐዋጅ ነው ተብሎ የተሰጠኝ ጽሑፍ በእስቴንስል የተባዛ እንጂ ከላይ አርማና ያድራሻ ምልክት ከታች ስምና ፊርማ የሌለበት መሆኑን፣ በሬዲዮ የተነገረውን ዐዋጅ አለማዳመጤን፣ እኔ ሕጋዊ መንግሥት አድርጌ በሐሣብ የገመትኩት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትን መሆኑን፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ወደ አልጋ ወራሹ የሚተላለፍበትን የሥልጣን አወራረስ አስቀድሞ ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት ሳሉ አልጋ ወራሽ የተባሉት ከንጉሠ ነገሥቱ ሕይወት ማለፍ በኋላ የሚተኩ እንደሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወታቸው ሳሉ በፈቃዳቸው የሚተላለፍላቸው እንደሆነ በልማድ የማውቀውና በትምህርት ቤትም የተነገረኝ መሆኑን ተናግሬ ጥያቄ እና መልሱ አበቃ።

ሁለተኛ የመከላከያ ምስክሬን የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ለፍርድ ቤቱ የሰጠውን የምስክርነት ቃል ከፍርድ ቤቱ መዝገብ እንዳገኘሁት አስቀምጠዋለሁ።

> ... ኮሎኔል ወርቅነህ ከተከሳሹ ጋር ጠርተውን ወደ አንድ ክፍል ገባን። ብዙ ሰዎች ነበሩ። ወዲያው ኮሎኔል ይህን አዋጅ የመሐንዲስ ኮሌጅ ተማሪዎች አልሰሙም። ባለመግባባት የጦር ሠራዊት ድንገት ብጥብጥ አንስቶ ደም እንዳይፋሰስ ተማሪዎች ሰልፍ አድርገው ሒደው እንዲጠይቋቸው ሔደህ አስረዳ ብለው ተከሳሹን አዘዙት። እኔንም አብራችሁ ሒዱ አሉን። ጄኔራል መንግሥቱም ነበሩ የዐዋጁንም ወረቀት ኮሎኔል ወርቅነህ ለተከሣሹ ሰጡት የአዋጁን ወረቀት ተከሣሹ ከተቀበለ በኋላ ሁለታችንም አብረን ሔድን። ኮሎኔል ወርቅነህ ዐዋጁን ተማሪዎቹ አልሰሙም ሔደህ ንገራቸው ብለው በነገሩት ጊዜ የትኛውን ዐዋጅ ነው አልሰማሁም ብሎ ተከሣሹ ስለጠየቃቸው የዐዋጁን ጽሑፍ ሰጡት የዐዋጁን

[13] ወጥ ቤቶች (አሣላፊው፣ አጋፋሪው፣ መጠጥ ቀጂው ኬክ ሠሪውን ሁሉ የጨመረ ነው)

ወረቀት ከሎኔል ወርቅነህ ለተከሳሹ በሰጡት ጊዜ ግርማዊነታቸው ጉዟቸው ወደ ብራዚል ነበር። ሁኔታቸው ስላልተረጋገጠ ሥልጣኑን ልዑል አልጋ ወራሽ ይዘዋል። ይኸንኑ ለተማሪዎቹ ግለጥላቸው ብለው ነግረውታል። ተከሣሹ የለበሰው የሲቪል ልብስ ነበር ... ።

ከዚህ በኋላ የዐቃቤ ሕጉ ለምስክሬ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሰጠው መልስ በዳኛው እንደሚከተለው ተነበበ።

ለዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ የምስክሩ መልስ ወደ ኰሎኔል ወርቅነህ ዘንድ ስገባ ማን ቀድሞ እንደገባ አላስታውስም። ተከሣሹ የጦር መሣሪያ መያዙን አላየሁም፤ ተከሣሹ የሄደበት መኪና የማን እንደሆነ አላውቅም፤ ራሱ መዝጊያውን ከፍቶ ገብቷል። ታኅሣሥ ፭ ቀን ፶፫ ዓ.ም ተከሣሹን አላየሁትም፣ በመኪናው ውስጥ ያየሁት ነገር መኪናው ቮልስ ዋገን ነው ካለ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ በቃኝ አለ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ፣ ሦስተኛው የመከላከያ ምስክሬ አቶ ኤፍሬም ፀሐይ በዐቃቤ ሕጉ ተጠይቆ የሰጠው የመከላከያ ምስክርነት ቃል በዳኛው እንደሚከተለው ተነበበ።

... አሁን በእሥር ቤት የሚገኘው በደንቡ ምሎ ተከሳሹን ዐውቀዋለሁ። ዐብ ወይም ዝምድና የለንም። በታኅሣሥ ፮ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ከጧቱ በግምት ፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ቁጥር ፳፬ በሆነው ክፍል ተከሣሹና እኔ ሌሎችም የካቢኔው ሠራተኞች የክብር ዘበኛ መኰንኖች እንዳለን ሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ መጥተው ተከሣሹን ወደ መሐንዲስ ኮሌጅ ሔደህ ስለ ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ከበደ ገብሬ ማመፅ እንድትገልጥና ዐዋጁንም እንድታስረዳ ደም እንዳይፋሰስ ብለው ትእዛዝ ሰጡት። ወዲያው እኔ ከክፍሉ ወጥቼ ወደ ታዘዝኩበት ልሄድ ስል መኪና ከቆመበት አጠገብ እንደደረስኩ ተከሳሹ ከአንድ ከማላውቀው የክብር ዘበኛ መኰንን ጋር ሆነው በቮልስ ዋገን መኪና ሲሔዱ ዓይቻለሁ። መኰንኑ የጦር ልብስ ለብሶ የብረት ባርኔጣ አድርጐ ነበር። ተከሳሹ ትእዛዝ በተቀበለ ጊዜ ጄኔራል መንግሥቱም ነበሩ። ካለ በኋላ የተከሣሽ ጠበቃ ጥያቄ በቃኝ አለ። ዐቃቤ ሕጉ ሌላ ትእዛዝ ስለመታዘዙ ላነሳው ጥያቄ ምስክሩ ሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ለተከሣሹ ሌላ ትእዛዝ አልሰጡትም። ፪ተኛው ምስክር መኖር አለመኖሩን አላስታውስውም ብዙ መኰንኖች ነበሩ። ተከሣሹን ከታኅሣሥ ፩ እስከ ፮ ቀን አይቼዋለሁ። በዚህ ቀን የጦር መሣሪያ አልያዘም ኰሎኔል ወርቅነህ ለተከሳሹ ትእዛዝ የሰጡት በቃል ነው። ካለ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ በቃኝ አለ። ለተከሣሹ ጠበቃ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ ተከሣሹ በቃል የተቀበለውን ትእዛዝ አንድ ባንድ ላስታውሰው አልችልም። ካለ በኋላ ጠበቃው ጥያቄ በቃኝ አለ።

ከዚህ ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ ለምስክሬ ለአቶ ኤፍሬም ፀሐዩ ጥያቄ አቀረበለት። አቶ ኤፍሬም ፀሐዬም እንዲህ ሲል መለሰ። ‹‹ለተከሣሹ የጽሑፍ ትዕዛዝ ሲሰጠው ዓላየሁም። ከክፍሉ ውስጥ ከተከሣሹ አስቀድሜ የወጣሁት እኔ ነኝ፤ ከፎቅ ወርጄ ከመኪናዬ ልገባ ስል ከኋላ ወጥቶ መኪናው ሊገባ ሲል ዓየሁት። ተከሣሹ ከኔ ወደ ኋላ የቆየው የአንድ ደቂቃ ያህል ነው። ከክፍሉ ውስጥ ስገባ ማንኛችን ቀድመን

እንደገባን አላስታውስም። ቁጥር ፳፬ ክፍል ትእዛዝ መቀበያችን ነው።» ብሎ ምስክርነቱ ተቋጨ።

አራተኛው የመከላከያ ምስክር አቶ መስፍን ወልደ ሚካኤል ዕድሜያቸው ፴፪ ዓመት መሆኑ ሥራቸው በካቢኔ ልዩ መምሪያ ባልደረባ የነበሩና አሁን በአንደኛ ክፍለ ጦር በእሥር ቤት ያሉ መሆኑ ተገልጾ በደንቡ መሠረት መማላቸው ተረጋግጦ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል እንደሰጡ በዳኛው ተነበበ።

> ተከሳሹን ዐውቀዋለሁ፤ ፀብ ወይም ዝምድና የለኝም። ታኅሣሥ ፯ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ከተከሳሹ ጋር ከጧቱ አንድ ሰዓት ተሩብ ሲሆን ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ፳፬ ቁጥር ቢሮ ተገናኝተናል። እኔ ቁጥር ፳፬ ክፍልን ከፊት አድርጌ ስገባ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከብዙ ሰዎች ጋር ቆመው ነበር። ተከሳሹም ነበር። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ንግግር ሲያደርጉ ተከሣሹ ሊመልስላቸው ሲሞክር በቁጣ ቃል ዝም ብለህ አድምጠኝ ብለው ተናገሩት። ወዲያው ለተከሳሹ ወደ መሐንዲስ ኮሌጅ ሒደህ አንተ የምታስረዳው ሁለት ጄኔራሎች ዐምፀዋል ብለህ ነው። ሌሎች ተማሪዎች ዐውቀውታል ብለው ሲናገሩት እንደሰማሁ እኔ ሳልጠራ በመግባቴ ተመልሼ ከኰሪደሩ ላይ ጥቂት ቆየት አልኩና ወደ መኪናዬ ሔድኩ። ከዚህ ሌላ የሰማሁት ነገር የለም። እኔ ከወጣሁ በኋላ ከተከሳሹ ጋር አልተገናኘንም። የመሥሪያ ቤታችን ደንብ እንደ ወታደር ደንብ ነው። ሠራተኛ ሲያጠፋ በልዩ ፍርድ ቤት ይቀጣል ይላል። ስንቀጠርም እንደ ወታደር በመሐላ ነው። ቁጥር ፳፬ በሆነው ክፍል ሌላ ማን ባለሥልጣን እንደነበረ አላስታውስም። ስላልተጠራሁ ፈርቼ ወዲያው ተመለስኩ። ካለ በኋላ የተከሣሽ ጠበቃ ቢቃኝ አለ።
>
> ለዐቃቤ ሕጉ መስቀለኛ ጥያቄ የምስክሩ መልስ በ፳፬ ቁጥር ክፍል ውስጥ ፫ኛውን የመከላከያ ምስክር ዓይቼዋለሁ። ፪ተኛ ምስክር መኖሩን አለመኖሩን አላስታውስም። የክብር ዘበኛ መኮንኖች ነበሩ። ኮሪደሩ ላይ በቆምኩበት ጊዜ ፫ተኛውን የመከላከያ ምስክር አላየሁትም። ተከሳሹን ባየሁት ጊዜ የለበሰው የሲቪል ልብስ ነው። ታኅሣሥ ፯ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ድረስ አንደኛ ታኅሣሥ ፩ ቀን በ፲፩ ሰዓት ሁለተኛው ታኅሣሥ ፯ ጠዋት ከመገናኘታችን በቀር ሌላ ጊዜ አልተገናኘንም። ካለ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ ቢቃኝ አለ። ለተከሣሹ ጠበቃ ማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ከተከሣሹ ጋር የተገናኘነው ለሥራ ከመሥሪያ ቤታችን ገብተን ነው ካለ በኋላ ጠበቃው ጥያቄ ቢቃኝ አለ።

ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ላነሳው ጥያቄ ምስክሩ እንዲህ ሲሉ መለሱ። «የምንፈፅማቸው ትእዛዞች በውስጠ ደንብ ተዘርዝሯል እንደ ወታደር ደንብ ነው ያልኩት ስናጠፋ በልዩ ፍርድ ቤትና በማርሻል ኩርት የምንቀጣ መሆኑን ደንባችን ስለሚገልጥ ነው። ታኅሣሥ ፩ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በታዘዝኩት መሠረት በዚህ ቀን በ፲፩ ሰዓት ለተከሳሹና ለሌሎችም ሠራተኞች የሰጡሁት ትእዛዝ አለ። በዚሁም የተከሰስኩበት ስለሆነ ዝርዝሩን ለመናገር እኔን የሚነካኝ ነው›› የሚል ነበር። ፭ኛው መከላከያ ምስክር አቶ ዳኜው ወልደ ሥላሴ ዕድሜ ፴፫ ዓመት፣ ሥራ

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ፣ አድራሻ አዲስ አበባ ካለ በኋላ በደንቡ ምሎ ተከሳሹን ዐውቀዋለሁ ጠብና ዝምድና የለኝም ተማሪ ቤት ሳለን ከ፴፱ ዓ.ም. ጀምሮ ዐውቀዋለሁ። ከተከሳሹ ጋር ከተገናኘንበት ጀምሮ መጥፎ ነገር አላየሁበትም ሰላማዊ ሰው ነው በወንጀል መከሰሱን አላውቅም። ቀድሞ በአሜሪካን ኤምባሲ ሲሠራ እንደነበርና ኋላ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ገብቶ መሥራቱን ዐውቃለሁ። ትውውቃችን በቅርብ ነው። ከተማሪ ቤት ጀምሮም አልተለያየንም ማለቱን ዳኛው አነበቡ።

አቶ ዳኜው ወልደሥላሴ ለዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ የሰጠው መልስም ተነበበ። በዚህ መሠረት አሜሪካን ኤምባሲ ተከሳሹ በምሠራበት ጊዜ ደመወዜ ጥሩ እንደነበር። ለውጭ አገር ከማገልገል ለአገሬ ባገለግል ይሻለኛል ብዬ ኤምባሲውን ለቅቄ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደገባሁ ኤምባሲው ዘንድ የሠራሁት ስድስት ዓመት እንደሚመስለው እና መንግሥት ቤት ሥራ የገባሁትም ሁለት ዓመት አካባቢ እንደሚሆን እንደመሰከረ ተነበበ።

፫ኛው የመከላከያ ምስክር አቶ ወሰኔለህ ብጡልም ዕድሜው ፴፮ ዓመት፣ ሥራው ትምህርት ሚኒስቴር፣ አድራሻው አዲስ አበባ መሆኑና በደንብ ስለመማሉ ተገልጾ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል እንደሰጠ በዳኛው ተነበበ።

> ተከሳሹን አውቀዋለሁ ጠብ ወይም ዝምድና የለንም። የማውቀው ከ፴፱ ዓ.ም ጀምሮ ጐንደር አንድ ትምህርት ቤት ሳለን ነው። እኔ ከጎንደር ከመጣሁ ከሁለት ዓመት በኋላ ተከሳሹ አዲስ አበባ መጣ በምንተዋወቅበት ጊዜ የተከሳሹ ጠባይ መልካም ነው፤ በወንጀል መከሰሱን አላውቅም። አዲስ አበባ ከመጣን በኋላ አብረን ነው የምንኖረው፤ አልተለያየንም። ቀድሞ የሚሠራው አሜሪካን ኤምባሲ ነበር። እዚያ የሠራው አራት ዓመት ይመስለኛል። ከአሜሪካን ኤምባሲ የወጣው እሱ እንደነገረኝ መንግሥቴን ባገለግል ይሻላል በማለት ነው። ካለ በኋላ ጠ በቃው ጥያቄ በቃኝ አለ።

ለዐቃቤ ሕጉ ጥያቄ ተከሳሹን በመንግሥት መሥሪያ ቤት ማን እንደቀጠረው አላውቅም ሲል ምስክሩ እንደመለሰ፤ ዐቃቤ ሕጉም ጥያቄ በቃኝ አለ።

የመጨረሻው የመከላከያ ምስክሬ ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ ዕድሜው ፴ ዓመት፣ ሥራው የክብር ዘበኛ ባልደረባ የነበረና በወቅቱ በእሥር ቤት የሚገኝ መሆኑ ተጠቅሶ ተከሳሹን አውቀዋለሁ፤ ፀብ ወይም ዝምድና የለኝም ተከሳሹን የማውቀው በሕዝብ ፀጥታ መምሪያ ከተቀጠረበት ከ፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ ነው። በሥራ እንገናኛለን ተከሳሹ መልካም ጠባይ አለው። ታዛዥና ትጉህ ሠራተኛ ነው። በወንጀል መከሰሱን አላውቅም በማለት የሰጠው ምስክርነት ተነበበ። ከዚህ በኋላ ጠበቃዬ ጥያቄ በቃኝ አለ። ዐቃቤ ሕጉም አልጠይቅም ስለ አለ ጠበቃዬ ማስረጃ አበቃሁ፤ የፍርድ ሐሣብ አቀርባለሁ አለ። በዚህ መሠረት ፍርድ ቤቱ የተከሣሽ ጠበቃ የፍርድ ሐሣብ እንዲያቀርብ ለግንቦት ፲ ቀን ፺፫ ዓ.ም. ቀጠረ።

ግንቦት ፫ ቀን ፶፫ ዓ.ም. በቀጠለው ችሎትም ፍርድ ቤቱ ሒደቱን እንደሚከተለው ዘገበ፡፡

... ዐቃቤ ሕጉ ያመለከተው የመፋረጃ ቃል ተከሳሹ ስለ አዲሱ መንግሥት ዐዋጅ ተናግሯል ተብሎ በተከሰሰበት ወንጀል ዕምነት ክደት ቢጠየቅ ክዶ ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ አራት ምስክር አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የምስክሮችም አመሰካከር አንድ ዓይነት ነው፡፡ ተከሳሹ ይጠቅመኛል ብሎ ያቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች ወንጀለኞች ሆነው በመገኘት በወንጀል ተከሰዋል፡፡ አንደኛው ምስክር የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ፲ ዓመት የተፈረደበት ነው፡፡ ሁለቱም ለምስክር ያደሩ ናቸው፡፡ በወንጀለኞቹ ምስክርነት እንኳን ያልተደገፈ ሆኖ የተደገፈም ቢሆን ተከሳሹ በነፃ ሊወጣ አይገባውም፡፡ ይልቁንም ተከሳሹ ቃሉን በመሐላ ሲሰጥ ግርማዊ ጃንሆይ ወደ ብራዚል ስለመሔዳቸው ከኮሌጅ ተማሪዎች ጥያቄ ቢቀርብለት ግርማዊነታቸውና ፲፮ቱ አጃቢዎቻቸው የመመለሳቸውን ነገር አላውቅም ብዬአለሁ ሲል ቃሉን ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ከታኅሣሥ ፭ ቀን ጦርነት እስከቆመበት እስከ ታኅሣሥ ፰ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ድረስ የጦር መሣሪያ ይዞ እንደነበረ አስረድቷል፡፡ በምርመራ ጊዜ በሰጠው ቃል ሳይገደድ የወንጀሉን አደራረግ ጽፎ ፈርሞ ስላቀረበ ሁለተኛ ማስረጃ አድርጌ ለፍርድ ቤቱ አቅርቤአለሁ፡፡ በጠቅላላው በተከሳሹ ላይ የተመሰከረበት ስለሆነ የተጠቀሰው አንቀፅ ፩፻፳ በተከሳሹ ላይ የፀና ሆኖ የተስተካከለ ንፁህ ፍርድ እንዲታደለኝ እለምናለሁ አሉ፡፡

የተከሳሽ ጠበቃ ያመለከተው የመፋረጃ ቃል አስመልክቶም

በመጨረሻ ዐቃቤ ሕጉ ንፁሕ ፍርድ እንዲሰጥ ያሉትን እኔ እስማማበታለሁ፡፡ ዐቃቤ ሕጉ መጀመሪያ በሰጡት ቃል ተከሳሹ ለአዲሱ መንግሥት ዐዋጅ ተናግሯል ተብሎ ተከሷል ላሉት ዐዋጅ የተነገረው በከሳሹ ስላልሆነና እራሱም ምንጭ ያልሆነ ስለሆነ በተከሰሰበት አንቀፅ አይቀጣም፡፡ በተከሰሰ ጊዜ ክሱን ክዶአል ላሉት ጥፋተኛ አይደለሁም አለ እንጂ የክሕደት ቃል አልሰጠም፡፡ ወደ ትምህርት ቤትም አልሔድኩም አላለም፡፡ አራት ምስክሮች መስክረውበታል ላሉት አልመሰከሩበትም፡፡ እንዲያውም ፩፻፳ አንቀፅ የሚፈቅደውን ለማድረጉ መስክረውለታል፡፡ ሦስቱ የመከላከያ ምስክሮች ተቀጥተዋል፡፡ ሌሎቹ ተከሰዋል ምስክርነታቸው በቂ አይሆንም ላሉትም ስለ ፍርድ ቤቶቹ ሥራ አካሔድ በወጣው ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፪ ነጋሪት ጋዜጣ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ሁሉ ማስረጃ አቅርቦ ነፃ ይወጣል ይላል እንጂ በምስክሮቹ መከሰስና አለመከሰስ ምክንያት አይመሰክሩም አይልም፡፡ ምስክርነትም የግል የሃይማኖት ጉዳይ ብቻ መሆኑን የተከበረው ፍርድ ቤት ዐውቆ የሚሠራበት ነው፡፡ የተፈረደበትም ምስክር በይግባኝ ላይ ነው፡፡ ቢፈረድበትም እንኳ በሕይወቱ እያለ የሚያውቀውን ለመመስከር የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ ስለመከሰሳቸው ፍርድ ቤቱ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ በጠቅላላ ለምስክርነት በቀረቡ ጊዜ ዓቃቤ ሕጉ አይመሰክሩም ብለው አልተቃወሙም፡፡ ፍርድ ቤቱም ፈቅዶ ሲያስመሰክር ይግባኝ አልጠየቁበትም፡፡ ተከሳሽ ቃሉን በሰጠ ጊዜ በዮቻቸውን ብሎ መስክሯል ያሉት ቃል እውነት አለመሆኑን መዘገቡ

ያረጋግጣል። የተከሳሽ መልስ በኮሌጅ ተማሪዎች ጥያቄ ተንቀሳቅሶ የሰጠው ከአጃቢዎቻቸው የተሰማ ምንም የለም። ጉዞው በባሕር ስለሆነ እኔ አላውቅም ከማለት በስተቀር ሌላ አላለም። ተከሳሹ ይህን የዐዋጅ ነገር ሔዶ እንዲያሰማ የታዘዘው ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ለመሆኑ በሚገባ በመከላከያ አስረድቷል። በነገሩ ተደናግሮ አለቃውን አንዳንድ ጥያቄዎች ለመጠየቅ ቢሞክር በግሳጼ ዝም ብለህ ሒደህ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ ንገር ተብሎ ከበላይ የታዘዘ ለመሆኑ በመከላከያ ምስክር አስረድቷል። እንኳን መላክተኛ ሆኖ ይህን የመሰለ ወንጀል ያልሆነውን ነገር ይቅርና ወደ ወንጀል የሚያመራ ነገር ቢሆን እንኳን ታዞ እምቢ ቢል በውስጥ አስተዳደራቸው ከፍ ያለ ቅጣት የሚያደርስ መሆኑን በመከላከያ አስረድቷል።

ስለ ሕጉ ክርክር ተከሣሹ የተከሰሰው ሕግ ተላልፏል ተብሎ ነው የተከሰሰበትም አንቀፅ ቁጥር ፬፻፹ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ነው። በዚህ አንቀፅ መሠረት ለመቅጣት ተከሣሹ መፈፀም ይገባው የነበረው ወንጀል አንደኛ በሃይማኖት ሕዝብን ቢለያይ፣ ሁለተኛ በዘር፣ ሦስተኛ አጣልቶ በማፋጀት፣ አራተኛ ለብጥብጥ በመገፋፋት ወይም በመቀስቀስ ሕዝብን አደራጅቶ ቢሆን ኖሮ ምናልባት ኃላፊነት ይነካው ነበር። ነገር ግን ተከሳሹ ደም እንዳይፋሰስ ትልቅ ጥቅም ያደረገ ለመሆኑ የሕግ ምስክሮች እንኳን አረጋግጠውለታል። የክሱን አያያዝና አመሰካከራቸውን ተመልክተው የተከሰሰበትን አንቀፅ ዐቃቤ ሕጉ ለማሻሻል አልሞከሩም። በዘለፋ አንቀፅ አልከሰሱትም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ በቁጥር ፬፻፴ መሠረት የተገለጠውን መንፈስ ተቀብሎ የፈፀመ ያሽልመዋል እንጂ አያስቀጣውም። የተከበረው ፍርድ ቤት ከዚህ ሕግ ጋር ቁጥር ፭፫/ሀ- የሆነውን በማጣመር ተመልክቶ እስካሁን ታሥሮ በቆየበት ዐቃቤ ሕጉን በመውቀስ ተከሣሹን በነፃ እንዲለቅልኝ እለምናለሁ ካለ በኋላ በዚሁ ፍርድ እንዲሰጠው ጠይቋል። ፍርድ ቤቱም መዝገቡን መርምሮ አስፈላጊውን ፍርድ ለመስጠት ለግንቦት ፲፰ ቀን ፶፫ ዓ.ም. ተቀጠረ።

የሚል ነበር።

የእኔ ፍርድ ከመሰጠቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ፣ ኮሎኔል ይልማ ሺበሺ (በኋላ ሜ/ጄኔራል) ለሚዜዬ ለመቶ አለቃ ማሞ አየለ "እስቲ እነዚህን አንቀፆች ይመልከታቸው" ብለው አንቀፅ ፭፻፹፣፬፻፴፬/ሠ፣ ወይም ፭፫/ሀ ፴፬ትን ብመለከታቸው የታዩትን አንቀፆች እንደሚጠቁሙኝ ይነግሩታል። እርሱ ለባለቤቴ ለወ/ሮ መቅደስ ቁምላቸው ይነግራትና ወህኒ ቤት መጥታ ስትነግረኝ፤ «እንዴት ተደርጐ? እኔኮ በነዚህ አንቀፆች አልተከሰስኩም። የተከሰስኩት በአንቀፅ ፬፴ ነው። እነዚህ አንቀፆች እኔን የሚመለከቱ አይደሉም። ምናልባት እሳቸው ወታደር ስለሆኑ ሕጉን በሚገባ ባለመረዳት ሊሆን ይችላልና እንደገና ሒደህ አነጋግራቸው ብየው» ብዬ መልሼ ላኳት። ይሄንን ሔዳ ስትነግረው መልሶ ቢጠይቃቸው «ግድየለም ልብ ብለህ ተመልከተው። በዚህ ነው የሚሆነው» ብለህ ንገረው ብለው ይነግሩትና እሳቸው ያሉትን ያስረዳታል። እኔም ይሄንን ስረዳ፤ አብረውኝ ካሉት ጓደኞቼ ጋር

ተነጋገርንበት «እንዲህ ከሆነማ ትክክለኛ ፍርድ አይገኝም። የበቀል መወጫ ልንሆን ነው» የሚል ግምት ያዝን።

እውነትም ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ፍርድ ቤት ቀረብንና ዳኞች አልተለወጥንም ዐቃቤ ሕግ ቀርቧል። የተከሳሽ ጠበቃም አለ የሚለውን የተለመደ መግቢያ ካሰሙ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጡ።

ተከሳሽ ብርሃኑ አስረስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፪፻፶ ቀጥር የተጻፈውን ተላልፎ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መሐንዲስ ኮሌጅ ትምህርት ቤት ሔዶ ተማሪዎችን ሰብስቦ ግርማዊ ጃንሆይ አይመለሱም። ይሀንኑም የአዲሱን መንግሥት መቋቋም ግርማዊነታቸው ያውቁታል። አዲሱ መንግሥት የመጠሪያ ስሙ ሕዝባዊ መንግሥት ነው። ፕሬዚዳንቱም ልዑል አልጋ ወራሽ ናቸው። በማለት የሐሰት ወሬ በማውራቱ ክስ ቀርቦበት ተከሳሹ ወንጀሉን ለመሥራቱ ቢጠየቅ አላጠፋሁም ብሎ ተከራክሯል። ለወንጀሉ ማጣሪያ እንዲመች አራት የሕግ ምስክሮች ተሰምተዋል። የምስክሮቹም አነጋገር ባጭሩ ተከሳሹ መሐንዲስ ኮሌጅ መጥቶ ግርማዊነታቸው አሽከሮቻቸውንና ወጥ ቤቶቻቸውን ይዘው ሔደዋል። ነገሩንም ግርማዊነታቸው አውቀውታል። ስለ ጃንሆይ መመለስ ተማሪዎቹ ቢጠይቁት አይመለሱም ተማሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ ነውና ደም እንዳይፋሰስ እናንተም ሰልፍ ውጡ። አዲሱ መንግሥት የአንድ ሰው የከተማ ቦታ ከ፫ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ እንዳይዝ ገደብ ያደርጋል በማለት ተናግሯል ብለው መስክረውበታል። የቆጠራቸውም መከላከያ ምስክሮች እንደመሰከሩት ተከሳሹን እንዳልደገፉት ታይቷል። ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የሕግ ምስክሮቹን ቃልና መከላከያዎቹ የሰጡትን ድምጽ ሰምቶ በተከሰሰበት አንቀፅ ፪፻፶፡ ፪፻፷፱/ሠ ፫፻፫/ሀ እና ፭፻፷፩ትን ተመልክተን ተከሳሹ በሠራው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ በስምንት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ፈርደናል። በፍርዱ ያልተስማማ ይግባኝ ማለት ይችላል ብለን ፋይሉ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ አዘናል።

ብለው ዘጉት። እኔ የተከሰስኩበት አንቀፅ ፪፻፶ የሚያዘው ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እሥራት ወይም የገንዘብ መቀጮ ሲሆን፤ ኮሎኔል ይልማ «ተመልከተው» ብለው በላኩት መሠረት ፍርዱ በስምንት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ «ፈርደናል» ተብሎ ተወሰነ።

በእኔ ላይ የተላለፈው ፍርድ ግን ሕግ የጣሰ በመሆኑ የጠበቃዬን ይግባኝ ተከትሎ የሕዝቡን ቁጣ የሰሙት አዲስ የተሾሙት የፍርድ ሚኒስትር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ (በኋላ ዶክተር ደጃዝማች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ም/ጠ ሚኒስትር) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን ሚስተር ናታን ማሬንን (እሥራኤላዊ) እና ምክትላቸውን አቶ ንርአዮን እንዲሁም የጠበቆች ማኅበር ፕሬዝዳንቱን ይዘው ስብሰባ አድርገው የኔን ፋይል ከከፍተኛው ፍርድ ቤት አስመጥተው ካዩ በኋላ የተሰጠው የፍርድ ውሳኔ ያላግባብ ስለሆነ ለዚሁ ፍርድ ማቃኛ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ሹምና ለፍርድ ቤቱ በግልባጭ እንዲያሳውቅ ደብዳቤ እንዲጻፍ ውሳኔ ላይ ተደረሰ። ይህ እንግዲህ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የፍትሕ ታሪክ

የመጀመሪያው መሆኑ ነው። ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ "ወንጀል ሰርቷል በዚህ አንቀፅ ይቀጣልኝ" ብሎ ለከሰሰው አካል ፍትሕ ተጓሎበታል ይስተካከል ብሎ ተከሳሹን ደግፎ ይግባኝ ሲል በርግጥም የመጀመሪያ ነበር።

ደጅ ወጥቼ ፍርዱን ለመስማት ጓግተው ይጠባበቁ ለነበሩ እሥረኞች ጓደኞቼ እና ለጥበቃ ወታደሮች ነገርኳቸው። በዚህ ላይ እንዳለን ወህኒ ቤት የነበረ ቀደም ብለን ያላየነውና ያላወቅነው አቶ አያሌው የተባለ የአስኮ ጫማ ፋብሪካ ተራ ሠራተኛ በኛ መኸል ወደ ችሎት እንዲገባ ተደርጐ በለውጡ ጊዜ «ዘለፉ ተናግረሃል» በማለት ተከሶ በሦስት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ተፈረደበት። ይህ ሰው ይህንን ፍርድ ሰምቶ እንደወጣ ይበሳጭና በፍርድ ቤቱ አጥር ሥር በነበረው የጐርፍ መውረጃ ቱቦ በመግባት ራሱን ሊያጠፋ ሲል እሥረኞችን ይጠብቁ በነበሩ የወህኒ ቤቱ ወታደሮች ጥረትና ትግል ወደውጪ ጐትተው በማውጣት ከሞት አተረፉት። በእኔ ላይ የተሰጠው ከሕግ የወጣ ፍርድና የአቶ አያሌው ድርጊት በከተማው ሲሰማ የሕዝብ ቁጣና ንዴትን ፈጠረ። የኔ ጠበቃም በዚህ ባልጠበቀው ፍርድ አዝኖና ተናዶ በዚያኑ ዕለት (ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) ከዚህ የሚከተለውን አቤቱታ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቀረበ።

> ይህ ማመልከቻ የቀረበው በዛሬው ቀን ክቡር የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ዳኝነት ስለተበደለና የወንጀለኛ መቅጫውም ሕግ መንፈስ ባለመፈፀሙ ሕጉ ተከብሮ እንዲጠበቅ በይግባኝ መልክ ቢሆንም እርዳታ እንዲደረግልኝ ነው። አቶ ብርሃኑ አስረስ የተባለው ደምበኛዬ በዘንድሮው ሽብር ምክንያት የወንጀል ግብር ፈጽመሀል ተብሎ በቁጥር ፬፻፹ ተከሶ ነበር። ከጥፋቱም ዋና ሆኖ የተከሰሰበት ደም እንዳይፈስ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ አድርጉ ብለህ ንግግር አሰምተሃል የሚል ሲሆን፣ ይህ የተጠቀሰው አንቀፅ ሕግ የሚቀጣው ግን ደም ያፋሰሰ እንደሆነ አልቂትና ፍጅት እንዲፈፀም ያደረገን ሰው በመሆኑ በኔ አስተያየት ተከሳሹ ሽልማት እንጂ ቅጣት አይገባውም ነበር። ተከሳሹ የተከሰሰበት አንቀፅ የሚያስከትለው ቅጣት በገንዘብ መቀጮ ወይም በእሥራት ስለሆነ እና ተከሳሹ ነፃ በሚወጣበት ክስ ይቀጣ ቢባል እንኳን የእሥራቱ ቅጣት ከሦስት ዓመት መብለጥ አይችልም ነበር። ዳሩ ግን አሣዛኝ በሆነ ጭካኔ የተከበረው ፍርድ ቤት በስምንት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የፈረደው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፻፭ የተገፈውን በመደምሰስ እንዲሁም በሕግ የተቋቋመ ፍርድ ቤት የቅጣት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የተከሳሹን ቅጣት ማቅለል እንጂ ከተከሰሰበት አብልጦ መቅጣት የማይችል መሆኑን ባለመገንዘብ ስለሆነ፣ አሁን ክቡርነትዎን የምንለምነው በዚህ አፈፃፀም ልክ እንደኔ ተፀፅተውልኝ ስለ ሕግ መጓደል ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቤቱታዬን ደግፈው ጉዳዬን እንዲያሰሙልኝ አደራ ጭምር ነው።

የሚል ነበር።

በሁለቱም ችሎት ክሳቸው እየታዩ የነበሩት የሌሎች ተከሳሾችም ፍርድ በዚያው ዕለት ተሰጠ። ፍርዱም

የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ፲፭ ዓመት ፅኑ እሥራት፣

| | |
|---|---|
| የሻለቃ ተፈራ በላይ | ፲፩ ዓመት ፅኑ እሥራት፣ |
| ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ | ፲ ዓመት ፅኑ እሥራት፣ |
| አቶ ብርሃኑ አስረስ | ስምንት ዓመት ፅኑ እሥራት፣ |
| የሻለቃ መላኩ በቀለ | ሰባት ዓመት ፅኑ እሥራት፣ |
| የሻለቃ ኃይለማርያም ሌንጮ | አራት ዓመት ተኩል እሥራት፣ |
| የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ | ሦስት ዓመት እሥራትና[14] |
| የሻምበል እሥራት ደፈረሱ | ሰባት ዓመት ፅኑ እሥራት ነበር። |

ሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጠበቃዬ አቶ ታደሰ ድልነሳው መልስ ሰጪውን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን አድርጎ ለጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠየቀ። በመግቢያው ‹‹ይህ ይግባኝ የቀረበው ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. በተሰጠ ፍርድ ላይ ሲሆን በዚህ ነገር መልስ ሰጭ የሆነው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በፍርድ አሰጣጥ ሕግ የተበደለ በመሆኑ ለተከበረው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጽሑፍ ባቀረበው ሐሳብ ይግባኝ ባይን ስለደገፈልኝ ነገሩን ዓይቶ ፍርዱን በቶሎ መሻር ምንም አከራካሪ ነገር የለም›› በማለት የጀመረው የጠበቃዬ ማመልከቻ በእኔ ስም ይግባኝ የሚልበትን ዝርዝርም እንዲህ ሲል አስቀመጠ።

፩ኛ/ ይግባኝ ባይ የወንጀል ሥራ ሠርተዋልና ይቀጣሉ በማለት ክስ ቀርቦባቸው ስለነበር ወንጀል አልሠራሁምና ጥፋተኛ አይደለሁም ሲሉ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፪ የተጻፈውን ዐዋጅ መንፈስ በመከተል መልስ ሰጥተውበት ነበር፣

፪ኛ/ ይግባኝ ባይ ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ መንፈሱን ተከትለው ጥፋተኛ አይደለሁም ያሉት በእውነተኛ ፍርድ ዕምነት ስለነበራቸው ብቻ ሳይሆን የተከሰሱበት የወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፴፪ በመሆኑና በዚህም ሕግ መሠረት ፈፅመዋል የተባሉት ሥራ በአንቀጹ ከተገለጹት የወንጀል ሥራዎች ጋር የማይገናኝ እንዲያውም ይህ የተከሰሱበት አንቀጽ የሚከለክለውን ሳይሆን የሚፈቅደውን ሕጋዊ ድርጊቶች ፈፅመው መገኘታቸው የማያስቀጣ መሆኑን በማወቅ ነበር፡-

፫ኛ/ በቁጥር ፴፪ የተገለጸው ሕግ ጥፋት አድርጎ የደነገገው ድርጊት ባጭሩ ቀጥሎ ያለውን ነው።

[14] *ሻለቃ አዲስ ለለም ጽጌ የተከሰሰው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎችን ራሱ ተማሪ የነበረበት አብረው ከሄዱት የፀጥታ ሰዎች ጋር በመሆን በመቀስቀሱ የሐሰት ወሬ በማውራት ተብሎ ሲሆን፣ የተፈረደበትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የሦስት ዓመት እሥራት ነው። ይሔንንም ራሳቸው ኮሎኔል ቃለ ክርስቶስ በጻፉት ገጽ ፪፻፸፬-፪፻፹፩ ድረስ የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ ስም በግዞት ከሚቀጡት ውስጥ ያልተመደበ መሆኑ ቢታይም፣ በገጽ ፫፻፲፬ በናዝሬት ግዞት ላሉ ከሻለቃ አዲስ ዓለም ጋር ከታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፭ እስከ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፮ አብረው እንደነበር ተደርጎ መቅረቡ ስህተት ነው። ሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ በሁለተኛ ደረጃ ተከሳሽነት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት ቀርቦ በሦስት ዓመት እሥራት የተቀጣና የእሥራት ጊዜውንም በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት የጨረሰ እንጂ በአስተዳደራዊ ፍርድ ሦስት ዓመት ግዞት የተቀጣ መኮንን አይደለም። ሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ ሰሙንና ክብሩን የሚጠብቅ ስትር መኮንን ነበር።*

በፖለቲካ ጉዳይ፣ በዘር ወይም በሃይማኖት ነገር ለመለያየት ለጥል ለፍጅት ወይም ለብጥብጥ የሚገፋፋ ወይም የሚቀሰቅስ የሆነ እንደሆነ በገንዘብ ወይም በእሥራት ይቀጣል የሚል ነው።

፬ኛ/ ይግባኝ ባይ የተከሰሱበት ማመልከቻ እንደሚነበበው ዋናው አዲሱን መንግሥት ለመደገፍ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ አድርጓል፡-

፭ኛ/ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት የጠራቸው ምስክሮች ባንድ ቃል እንዳስረዱት በወንድማማች መካከል ደም እንዳይፋሰስ ሰላማዊ ሰልፍ እንድታደርጉ እንድነግራችሁ ተልኬ መጥቻለሁ ብሎ ተከሳሹ ሲናገር ሰምተናል፤ ከዚያ በኋላ ተከሳሹ አመንጭተው ሳይሆን በተማሪዎቹ ብዙ ልዩ ልዩ ጥያቄ እየተጠየቁ አንዳንድ መልስ ይሰጡ ነበር።

፮ኛ/ ተከሳሹ በመከላከያ ሰባት ምስክሮች ቆጥረው ያስረዱት፡-

ሀ/ ተማሪዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ እንዲነግሩዋቸው በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ መታዘዛቸውንና በፈቃዳቸው ያልተናገሩ መሆኑን፣

ለ/ አንድም ጊዜ በወንጀል ተከሰው የማያውቁና እስከ ተከሰሱበትም ጊዜ ድረስ በቅን መንግሥትን ያገለገሉ ሰላማዊ ነዋሪ መሆናቸውን ነበር።

፯ኛ/ የተከበረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተከሣሹ ላይ ቅጣት ሲወሰን፤ በዕሙን አጻጻፍ እንደገለጸው የተከሳሹን ቅጣት ሊያቃልላቸው ይገባል ሲል በመሠረቱ ተከሳሽን ደግፎ በቁጥር ፹፩ እና በንዑስ ክፍል ፩ ቅጣትን ስለማቅለልና ከቅጣት ነፃ ስለማድረግ ደንብ የታወጀውን ቁጥር ፻፹ን ጨምሮ ገልጾላቸዋል።

፰ኛ/ ዳሩ ግን እሥራቱን በሚወስንበት ጊዜ እርስ በርሱ ተቃራኒ የሆነ ፍርድ ከማስማቱም በላይ በሕግ ረገድ እጅግ ግዙፍ የሆነ ስህተት ፈጥሮ ፍርድ ቤቱ ፈራጅም ከሣሽም በመሆን ይግባኝ ባዩ የተከሰሱበት ቁጥር ፬፻፹፮ ከሚወስነው የእሥራት ጊዜ አምስት ዓመት ትርፍ በመጨመር ተከሣሹ በስምንት ዓመት ፅኑ እሥራት ይቀጣሉ ሲል አስቃቂ ፍርድ ፈርዷል።

፱ኛ/ በይግባኝ ባዩ ጠበቃ ሕጋዊ አስተያየት ይህ ስህተት ሊፈጠር የቻለው ምናልባት ፍርድ ቤቱ ከአዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መንፈስ ጋር ካለመግባባት የተነሳ ይሆናል በማለት ተገምቷል። ምክንያቱም ይግባኝ ባዩ የተከሰሱበት ቁጥር ፬፻፹፮ የሚያዘው ቅጣት እሥራት ወይም የገንዘብ መቀጮ ብቻ ነው፣ እንግዲህ የተከበረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንደገባው የቅጣቱ ምርጫ እሥራት ካለ እሥራት ማለት ደግሞ እስከ ዕድሜ ልክ ሊሆንም ይችላል በማለት ነው። ይህ የሕግ አቀራረብ ግዙፍ ስህተት እንዳለበት ግልጽ ነው። ምክንያቱም እሥራት ማለት ከአሥር ቀን አንሥቶ እስከ ሦስት ዓመት ብቻ እንደሆነ በዚሁ በአዲሱ ወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር ፻፮ ተገልጿል። ይህም ማለት ይግባኝ ባዩ ፈፅመዋል የተባሉት የወንጀል ግብር ባለመሆኑ አያስቀጣም እንጂ ያስቀጣል ቢባል እንኳን በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት መካከል ባለ ጊዜ ብቻ ከሦስት ዓመት ያልበለጠ የእሥራት ቅጣት መስጠት ይችላል፤ ወይም በአመክሮ ብቻ ሊያልፈው ይችላል ማለት ነው። ከዚህ ጊዜ

፳፬ ሰዓት እንኳን ይግባኝ ባዩን አስበልጦ በቅጣት ለመጨቆን አይገባም፤ አይቻልም። ምክንያቱም ይግባኝ ባዩ በጽኑ እሥራት እንዲቀጡ በሚል አንቀፅ ፈጽሞ ስላልተከሰሱ ነው። ፅኑ እሥራት ደግሞ ምን ማለት እንደ ሆነ በዚሁ ሕግ በቁጥር ፻፷ ተገልጿል። ተከሳሹ አልተከሰሱበትም። ከሁሉ የሚያስገርመው ፍርድ ቤቱ በቁጥር ፻፹፩ ስለተከሳሹ በፍርድ ውስጥ የጠቀሰላቸው መሆኑ የማይካድ ከሆነ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ተራ ቁጥር መሠረት ተከሳሹን በገንዘብ መቀጫ መልቀቅ እንዳለበት ሕጉን አልተመለከተላቸውም።

ክቡር ሆይ፣

፲ኛ/ ይህ እጅግ ዘመናዊ የሆነው አዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን በገናናው ንጉሠ ነገሥታችን መልካም ፈቃድ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ሲታደለን፤ በመንበረ ዳኝነት ላይ ሁኖ ይህን ፍትህ የሚፈትተው ዳኛ አስቀድሞ ያነበው ዘንድ እንዲህ የሚል ንጉሣዊ ቃል ይገኝበታል፣
በዓለም ላይ ሳይንስ እያደገ በመሔዱ መጠን ለዘመናዊው ኑሮ እያበረከታቸው የተወሳሰቡ ነገሮች በተስፋፉበትና የሕጐች ብዛት እያደገ በሔደበት በዛሬው ጊዜ ባንድ ወገን የሰውን ጠባይ በደንብ ለማስኬድ የሚወጡት ሕጐች በሚገባ እንዲፈጸሙ አስፈላጊ ሲሆን፤ በሁለተኛው ወገን ደግሞ የአፈፃፀሙ ነገር ርኅራኄንና እጅግ ሰፊ የሆነ አስተያየትን የያዘ እንዲሆን ይገባል የሚል ነው።
እንግዲህ የተከበረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህን ሁሉ አበጥሮና አተኩሮ ሳይመለከት የብዙ ሕፃናት አስተዳዳሪና የቤተሰብ ኃላፊ የሆኑትን ንፁሕ ሰው በተከሰሱበት አንቀጽ እንኳን ፈፅሞ ጥፋተኛ ሆነው ያልተገኙትን እንዲያውም እራሱ ከሳሽም ሆኖ የፈረደባቸው አሳዛኝ ስለሆነ የተከበረው የንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ተከሳሹን በነፃ እንዲያሰናብትልኝ ስለሕግ መጓደል ብቻ በዐቃቤ ሕግም ጭምር የተደገፈልኝን ቅሬታዬን በታላቅ ትህትና አቀርባለሁ።

በማለት አስቀምጧል። ለዚህ ይግባኝም ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ አቶ ቦጋለ ውቤ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል።

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ወንጀል መ/ቁ ፫፻፴፩/፶፫ ከጠቀሰ በኋላ መልሱን ሲዘረዝር

፩ኛ/ የክፍሉ ሕግ አስከባሪ ተከሳሹ በሠራው የወንጀል አደራረግ ተገቢውን የመጀመሪያውን የወንጀለኛ መቅጫ አንቀፅ ፩፻፹ ጠቅሶ መከራከሩና አስመስክሮ ሲረታ፤ የምስክሮቹን ቃል አነጋገርና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በማመዛዘን ተወራራሽ አንቀፆችን በመጨመር በስምንት ዓመት እሥራት ተከሳሹ እንዲቀጣ ፈርዷል፣

፪ኛ/ የተከሣሹ ጠበቃ ደምበኛዬ ባልተጠቀሰበት አንቀፅ ሊቀጣ አይገባም ሲሉ ለክቡር የፍርድ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ባመለከቱት መሠረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተከሣሹ ጠበቃ ያቀረቡትን የፍርድ መቃወም ደግፈው ለክፍልዎ ዐቃቤ ሕግ ለአቶ ሙሉጌታ ታደሰ በግንቦት ፳፪ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በቁጥር ሠ/፲፱፻፵፬/ጠ.ዓ/፯ ሲጽፉ ለክብርነትዎ ያደረጉት ግልባጭ ይገኛል። ምንም አድራሻው ለአቶ ሙሉጌታ ቢሆን ይህ ጉዳይ

እኔን የሚመለከት በመሆኑ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕጎች ሹም እኔ መልስ እንድሰጥ በነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በደብዳቤ በተሰጠኝ ትእዛዝ እዚህ ፍርድ ቤት ቀርቤ ስለነበረ በተለዋጩ ቀጠሮ መልስ እንድሰጥ አዞኛል፣

፫ኛ/ ለዚህ ጉዳይ የመብቱን ሥልጣን ድጋፍ በማድረግ ለዐቃቤ ሕጎች የበላይ የሆነው የሥራ መርሆአችን የፍርድ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በማክበድ ቅጣት ተከሣሹን የቀጣው ከሕግ ውጭ ነው ሊሻሻልለት ይገባል ሲሉ አትተውና ወቅሰው ጽፈዋል። እንግዲህ በዚህ አያያዝ የበታች የሆነው ዐቃቤ ሕግ የበላይን ትዕዛዝ ከመቀበል ሌላ ለመቃወም ስለማይችል ምንም ለማለት አላስፈለገም።

ዳሩ ግን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ አንድ ሳያስታውሰው የማያልፈው ነገር አጋጥሞታል። ይኸውም በተከሳሹ ላይ የሕግ ምስክር ተሰምቶ በሱም የመከላከያ ምስክር ተቆጥሮና ተሰምቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመሰለው ፈርዶ የወሰነውን እንደገና በተከሳሹ ላይ ያልተመሰከረበት ወይም ጠበቃ ሳይጨምር ተከራክሮ የተፈረደበት በማስመሰል ጉዳዩ በሌላ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አዲስ ሆኖ ይታይ ማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፈረደውን ሌላ ጓደኛው ይግባኝ ሰሚ ሆኖ ይየው እንደማለት ሲሆን፤ ይህ በመዘንጋት የተጻፈና የተላለፈ ነው ከማለት በስተቀር ሕግ ነው አላልኩም።

ጉዳዩ የቀረበለት ክቡር የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ በጅቷል አልበጀም ከማለት በስተቀር ወደዚያው ሊመለስ የማይታሰብ ስለመሰለኝ ሐተታውን በዚህ ላይ አቁሜ፣ ስለፍሬ ነገሩ ተከሳሹ በፍርድ ተበድሏል በማለት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አትተው ካሳሰቡ ኃላፊነቱ በአዛዡ ላይ ተጥሎ ክቡር የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፍርድ ቢወስን የማልቃወም መሆኔን በማክበር እገልጻለሁ።

ይላል።

በዚህ ደብዳቤ በቀኝ ጐን ላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ሹም ያለቦታውና ያለሥልጣኑ በዚህ ጉዳይ አቶ ቦጋለ ውቤ መልስ እንዲሰጡ ሲል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መጥቶ አዟል። በዚህ ትእዛዝ አቶ ቦጋለ ውቤ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርበው «እከራከራለሁ» ሲሉ፤ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ «የራሱ ዐቃቤ ሕግ እያለው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕግ አስከባሪ ተከትሎ መጥቶ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እከራከራለሁ የሚለው» እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ ሲሰማ፤ በጠበቃዬ አማካኝነት ወሬው ወደ ፍርድ ሚኒስቴር ተሰማና የፍርድ ሚኒስትሩ ከጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ከምክትሉ ጋር ተነጋግረው አቶ ቦጋለ ውቤ «የከፍተኛን ፍርድ ቤት ጉዳይ ተከታትለህ የጨረስክ ስለሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የራሱ የችሎት ዐቃቤ ሕግ ስላለው አንተ ወደዚያ መሔድ የለብህም» በማለት በደብዳቤ አገዷቸው። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ዐቃቤ ሕግ የነበሩትን አቶ ቦጋለ ውቤን የበላይ አካል የሆነው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት ተገኝተው እንዳይከራከሩ በደብዳቤ ሲያግዷቸው፤ ይህንኑ ለልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ሲነግሯቸው ልዑሉ

በበኩላቸው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥራና ሥልጣን ጣልቃ በመግባት ከጽሕፈት ሚኒስቴር ደብዳቤ በማጻፍ አቶ ቦጋለ ውቤ የአቶ ብርሃኑ አስረስ ጉዳይ እስኪያልቅ ድረስ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍርድ ምርመራ ችሎት ሁሉ እየተገኙ እንዲከራከሩ የሚል ትእዛዝ በማምጣታቸው ክርክሩን በሥርዓት ለማስኬድ አስቸገረ። በእርግጥ በጊዜው የነበረው የፍትህና የአስተዳደር ሥርዓት ይህንን ይመስል ነበር። የታኅሣሡ ግርግር የተከሰተው እንዲህ ያለውን የፍትህ መጓደልንና የአስተዳደር ችግርን ለማስወገድ በተደረገ ሙከራ ነበር።

የፍርድ ሚኒስቴር

ለጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ
በጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡ ስለአቶ ብርሃኑ አስረስ
የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መዝገብ ቁጥር፡ 30689/53

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

2.

ለለዚሁ ትምህርት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 480. [illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] —

22. 9. 53 ዓ.ም

ግልባጭ/.
[illegible]
23/9/53

ለዚሁ [illegible] መዝገብ [illegible] በመጠባበቅ [illegible]

[illegible]

9/10/53

## የወህኒ ቤት ቆይታዬና ትዝታዬ

በይግባኝ ክርክር ላይ እንዳለሁ ከነበርንበት ከቀጠሮ ክፍል ወደ ሦስት የፍርደኛ መኖሪያ ቤቶች ከፋፍለው አገቡን። የፍርደኛው ክፍል ከዓለም በቃኝና ከቀጠሮው ክፍል የተሻለ ነፃነት ያለበት ሲሆን፤ እሥረኛው ጉልበትና ጤና ካለው ሰውነቱ እንዲንቀሳቀስ በጓሮ አትክልት ሥራ ላይ ይመደባል። በኋላም በኢንዱስትሪ ክፍል ገብቶ ሙያ ይለምዳል። ለዚህ ሥራው ግማሽ ዳቦ ድርጐ ይሰጠዋል። ጤናውና ጉልበቱ ደህና ሆኖ የማምለጥ ሙከራ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ከተገመተ ሥራ ላይ አይመደብም። ግቢውም ሰፋ ያለ ስለሆነ ሙሉውን ቀን እንደልቡ በግቢው ውስጥ ሲንሸራሸር መዋል ይችላል። ወደ ትምህርት ቤት፣ ወደ ቤተክርስቲያንና ክሊኒክ ለመሔድም ከላይ ከጠቀስኳቸው ሁለት የእሥራት ክፍሎች ቀለል ያለ ቁጥጥርና ጥበቃ እየተደረገበት መንቀሳቀስ ይችላል። በመኝታ በኩልም እንደቀጠሮው ክፍል ቤቱ በሦስቱም ማዕዘን ለመኝታ የሚሆን ቆጥ የተሠራለት በመሆኑ ከላይም ከታችም በመኝታነት ይገለገሉበታል። ልዩነቱ መፀዳጃ ቤቱ ራሱን ችሎ እዚያው ክፍሉ ውስጥ መኖሩ ነው።

## ጉዞ ወደ ደብረ ብርሃን እሥር ቤት

በዚህ ሁኔታ እንደቆየን "ጢያቂ በዝቷል ወህኒ ቤቱን ያሠጋዋል" የሚል ምክንያት ተፈጠረና ከፍርደኛ ወጥተን የወህኒ ወህኒ ወደ ሆነው ዓለም በቃኝ መልሰው አገቡን። ከዚያም ብዙ ሳንቆይ አንድ ቀን ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት የዓለም በቃኝ መግቢያ መውጫው ድርብ በር ተከፍቶ ሻለቃ ተፈራ ወልደ ተንሳኤ፣ የሻምበል አስራት ደፈረሱ፣ አቶ ብርሃኑ አስረስ፣ ቀኛዝማች አባተ ኃይሉ፣ አቶ ብዙነህ ሺፈራው፣ አቶ መኮንን ዋሴ፣ አቶ በርሄ ተድላ ተብሎ ስማችን እየተጠራ ከየክፍላችን ወጥተን ከዓለም በቃኝ በር ከውስጥና ከውጭ መሐል ስንደርስ እጅ እጃችን በጥድፊያ በሰንሰለት እየታሠረ ከተዘጋጀው ዙሪያው ዝግ ከሆነው ከወህኒ ቤቱ እሥረኛ ማመላለሻ መኪና እንድንሳፈር ተደረገ። ፩ኛው፣ ፭ኛውና ፮ኛው የተጠቀሱት እሥረኞችም ከላይ ከፍርደኛና ከክሊኒክ ክፍሎች ተጠርተው መጡና ከኛ ጋር ተሣፈሩ። በዚህ ጊዜ ሁላችንም በድንጋጤ ተዋጥን። ምክንያቱም ለሊት በእንዲያ ያለ ሰዓት መኪና ወደ ዓለም በቃኝ መጥቶ እሥረኛ የሚጠራው ወይ ለግርፋት፣ አሊያም ወንጀል በሠራበት ቦታ ቅጣቱን ለማስፈፀም እንደነበር ቀደም ብሎ ከሰማነው ከወህኒ ቤቱ ታሪክ ስለተረዳን ነው።

ጥርጣሬያችን ይህ ቢሆንም የእያንዳንዳችን እጣ እንደሥጋታችን እንደማይሆን በየልቦናችን መተንበያችን አልቀረም። በኰሚኒስትነት የተጠረጠረው አቶ በርሄ ተድላ ግን በወህኒ ቤቱ የቆየና በዚያም አካባቢ ሲደረግ የነበረውን የተገነዘበ በመሆኑ ብርቱ ድንጋጤ ላይ ወድቆ ጤናው ታወከ። ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ሰውነቱ ተዝለፈለፈ። መኪና ላይም መሣፈር ስላቃተው በሰው ሸክም ነበር የተሣፈረው። በመኪናው አግዳሚ ወንበር ላይ ተደላድሎ መቀመጥ ባለመቻሉ ከመኪናው ግድግዳ የብረት

ማገር ጋር በብርድ ልብስ አሥረነው ጉዞው ቀጠለ። ሲነጋጋ ሲል አቅጣጫችን ወደ ደብረ ብርሃን መሆኑን ዐወቅን። በጠባቂነት አብረውን ለነበሩት ወታደሮች ወዴትና ለምን እንደሚወስዱን ለማወቅ በርካታ ጥያቄዎችን ብናቀርብም በሁኔታቸው ክፉ ነገር እንደሌለ ከማሳየት እና «ትደርሱበታላችሁ» ከምትለዋ ቃል በስተቀር ሌላ ፍንጭ ሳይሰጡን ደብረ ብርሃን ደረስን።

ከዚያ መኪናው ከተማውን ወደ ጋሽ ትቶ ወደ ምሥራቅ በመዞር ወደ ጉጡ ሲወስደን ግን የመጀመሪያውን ጥርጣሬያችንን እንዲታደስና እንዲጐላ ቢያደርገውም፣ ክፉ ነገር ከፊታችን ተደቅኖ የሚጠብቀን መሆኑን የሚያመላክት ሁኔታ ሳናገኝ ደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት ደረስን። ርክክብ ይደረግ በነበረበት ጊዜ አቶ በርሄ ተድላ መጀመሪያ ከዓለም በቃኝ ሲወጣ የመታው ድንጋጤ በጣም ኃይለኛ ስለነበር፣ ፊቱ ከቀይነት ወደ ነጭነት እየተለወጠ በመምጣቱ ይሞት ይሆን ወደሚል ሥጋት ከተተን። ሁኔታው ተባብሶ መናገርና መቀመጥ ተሳነው። ምግብ መብላት፣ ውሀ መጠጣት አልቻለም። ትውኪያና ተቅማጥ ስላጠቃው በሦስተኛው ቀን ወደ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት እንዲመለስ ተደረገ።

የደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት አሠራር ባለአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ነው። እዚያ የቆዩት እሥረኛ የክብር ዘበኛ መኰንኖች ከአገሬው እሥረኛ ጋር እንዳይገናኙና እንዳይነጋገሩ ታስቦ ግቢው መሐል ለመሐል ከሁለት ተከፍሎ በጠርብ እንጨት ታጥሮ ነበር። እኛ ወደ ደብረ ብርሃን ስንላክ ቦታውን ለኛ ለማስለቀቅ ክብር ዘበኞቹን ከአገሬው እሥረኛ ጋር ቀላቀሏቸው። እኛን እነሱ ከለቀቁት ክፍል አስገቡን። እነርሱን ግን ጥቂት አሰነበቷቸውና ወደ ሸዋሮቢት እሥር ቤት ወሰዷቸው። ደብረ ብርሃን አገሩ ቀዝቃዛ ስለሆነ ብርዱን መቋቋም አቃተን። በዚህ የተነሣ የገለባ ፍራሽ አስገዝተን ከታች እሱን ከላይ የጥጥ ፍራሽ በመደረብና ከመካከላችን አንድ ተረኛ በማቆም ቀሪዎቹ ዧ[15] ብለን በጀርባችን ተጠጋግተን ስንተኛ፣ ተረኛው አልባሽ በጐንና በጐን ክፍተት እንዳያመጣ ከጥጥ ፍራሹ ጋር ብርድ ልብሱን አጐናጥፎ እንደ ሞተ ሰው በመጠቅለል አስገብቶ ያሥረናል። ይህ ተግባር ተራ በተራ የሚደርሰን የየዕለት ያልባሽነት ሥራችን ነበር።

በደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት ኑሮአችን ብዙ የሚነሱ ፈተናዎች ነበሩ። ጥቂቶቹን ለማንሳት ከዓለም በቃኝ በመውጣት ወደ ደብረ ብርሃን ስንሔድ በአቶ በርሄ ተድላ ላይ የደረሰው የጤና ችግርና የኛ ቤተሰቦችም ከነበርንበት ወጥተን የሔድንበት ቦታም ሆነ መጨረሻችን ምን እንደሆነ ባለማወቃቸው የወረደባቸው ድንጋጤ፣ ጭንቀትና ለቅሶ ከባድ ነበር። ያለንበት ባለመታወቁ ዘመድ አዝማድ ለመጠየቅና ስንቅ ለማቀበል አልቻለም። በወህኒ ቤቱ ደግሞ ላንድ እሥረኛ በቀን የሚሰጠው ድርጐ ሁለት የገብስ እንጀራ ከሁለት ጭልፋ የሀል ወጥ ጋር ነበር። ሕይወትን ለማቆየትና በረሃብ ላለመሞት በሚደረግ ትግል ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ተቀብለን በላን። የገብስ

[15] በጀርባ ቀጥ ብሎ ተንጋሎ መተኛት

እንጀራን ለማያውቅ ለዚያውም ሙያ በጐደለው ሁኔታ በወህኒ ቤት ውስጥ የተዘጋጀ የገብስ እንጀራ መብላት አስቸጋሪ በመሆኑ በጤፍ እንጀራ እንዲለወጥልን ስንጠይቅ፤ ሁለቱ የገብስ እንጀራ ባንድ እንጉቻ በምታክል የጤፍ እንጀራ ተገምቶ፤ ካንድ ጭልፋ የህል ወጥ ጋር በቀን አንድ ጊዜ ለቁርስም፣ ለምሳም፣ ለራትም እንዲሆነን ይሰጠን ጀመር:: ይችን እፍ ቢሏት ደብረ ሲና የምታርፍ እንጀራ በሁለት ጉርሻ ጨርሰን ቁልጭ ማለት ጀመርን:: ከቀናት በኋላ ቦታቸውን ለኛ የለቀቁት እሥረኛ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ያጋጠመንን የምግብ እጥረት ሰምተው በየቀኑ ትንሽ ትንሽ የመደጉሚያ ምግብ እየላኩ ቤተሰቦቻችን እስኪደርሱልን ድጋፍ ሲያደርጉልን ቆዩ::

ካሥር ቀናት በኋላ ቤተሰቦቻችን በተለይ የኔ ባለቤት ወ/ሮ መቅደስ ቁምላቸውና የሻምበል አሥራት ደፈረሱ እጮኛ ወ/ሪት ብዙነሽ አየለ ብርቱና ሥልተኞች ስለነበሩና ሠፊ ማኅበራዊ ግንኙነት ስለነበራቸው፤ ጥረው ያለንበትን ዐውቀው መጥተው አገኙን:: ወ/ሪት ብዙነሽ አየለ በትውልዷ የሸዋ የከፍተኛው ማኅበረሰብ ተወላጅ ስለሆነች በዚያ በኩል የሚገኘውን መረጃ የምታገኝ ሲሆን፤ የኔ ባለቤት ወ/ሮ መቅደስ ደግሞ የመካከለኛ ኑሮ ነዋሪ ኅብረተሰብ (ሚድል ክላስ) የምትመደብ በመሆኗ በዚያ በኩል ባላት ሠፊ ማኅበረሰባዊ ግንኙነትና በፍርድ ቤቱ በኩል የምትጠይቀውን መረጃ ሁሉም ከልብ ሊረዳት ፈቃደኛ ሆኖ ይሰጣት የነበረ በመሆኑ ስለውጪ ሁኔታ ሁሉ በቂ ግንዛቤ ነበረን። ወደ ደብረ ብርሃን የተላክንበት ምክንያትም «ጠያቂያቸው በዝቷል፤ ለፀጥታው ያሠጋል» ተብሎ ነው አሉን::

የመጣልንን ስንቅና ገንዘብ ለመጠቀም የሚያስፈልገንን ነገር እያስገዛን እንደ አዲስ አበባው ወህኒ ቤት በጉልበት ሥራ የሚረዳ እስኩፒኒ[16] ልጅ ወህኒ ቤቱ መደበልን:: ይህ ልጅ ከወህኒ ቤቱ መውጣት መግባት የሚችል አንድ ገጠሬ እሥረኛ ሲሆን፤ በጠባዩ ጥሩ ታዛዥ ነው:: ለእኛ የሚጠቅም ሙያ ግን አልነበረውም:: በዚህ ምክንያት የሚሠራልንን ወጥ እኛ ቀምመን ለሱ እንሰጥ ነበር:: በዚህ ውስጥ የሌሉበት ታሣሪ ግን ከመካከላችን ነበሩ:: እርሳቸውም ቀኛዝማች አባተ ኃይሉ የሚባሉ የልዑል አልጋ ወራሽ የቅርብ ዘመድ ናቸው:: ቀኛዝማች አባተ ኃይሉ በመፈንቅለ መንግሥቱ ጊዜ ወልዲያ ላይ መትረየስ ጠምደው፣ አውራ መንገዱን ዘግተው፣ ያልጋ ወራሹን ሥልጣን መያዝ በመቃወም ወደ አዲስ አበባ የሚመጣውን ጦርም ሆነ ሌላ ተቃዋሚ ላለማሳለፍ በማመፃቸው ተከሰው በዚህ ድርጊት የሦስት ዓመት እሥራት ፍርደኛ ነበሩ:: ስለዚህ ከወልዲያ አውጥተው ከኛ ጋር ደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት አብረን ባንድ ክፍል ውስጥ ተደልድለው ነበር:: በዚህ ጊዜ ስድስታችንም ተራ ገብተን ለምግብ የሚሆነውን ነገር ሽንኩርቱን፣ በርበሬውን፣ ቅባቱን፣ ጨዉን፣ ሽሮውን፣ ፖስታውን ...ወዘተ. መጥነን ለእስኩፒኒው ሰጥተን እንዴት ማድረግ እንዳለበት የምንችለውን ያህል አስረድተን እንሰደዋለን:: በዚህ የምግብ አዘጋጅነትም ሆነ የቤት ፅዳት ተራም ቀኛዝማች አባተ ኃይሉ «በጭራሽ አልካፈልም አላደርገውም

[16] ከጣሊያንኛ ቋንቋ የተወሰደ በወህኒ ቤት የተለመደ ቃል ሲሆን፤ ትርጉሙ «ጠራጊ»፣ የጽዳት ሠራተኛ፣ ተላላኪ ማለት ነው::

እንዲያው በረሃብ እሞታለሁ እንጂ! ወጥ አልሠራም! ቤት አልጠርግም!» አሉ። እኛም የባሕል ተጽዕኖ እንደሆነ ተገንዝበን እሳቸውን ከዚህ የተራ ሥራ አወጣናቸው።

በእሥር ቤቱ ቆይታችን የሁሉም አያያዝ አንድ ዓይነት አልነበረም። ለምሳሌ የወህኒ ቤቱ የሃምሣ አለቃ የከፋ ነበር። የሻምበል ጌታነህ ደምሴ የሚባሉት የወህኒ ቤቱ ሹም ደግሞ የባህሪ ጌታ ናቸው። ፈሪሃ እግዚያብሔር ያደረባቸው፣ ለእኛም ጥሩ አመለከከት ያላቸው ነበሩ። "ቀን የማይጉድልበት ወንድ ልጅ የለም" ብለው የሚያምኑ ስለነበሩ ተንከባክበው ያዙን። የተያዝንበትን ምክንያት መሣሪያ አድርገው ሊጠቀሙበት እንደማይፈልጉም ደጋግመው ያነሱ ነበር። ቅን፣ ጨዋና አርቀው የሚያዩ በጣም ጥሩ ሰው ሆነው ነው ያገኘናቸው። የሃምሳ አለቃው ግን በእኛ ላይ የሚከፋ ብቻ ሳይሆን በሻምበሉ ላይ የሚያሳየው ንቀትና አለመታዘዝ ልክ የለውም። የዚህ ደግሞ ምክንያቱ ካውራጃው አስተዳዳሪ ከደጃዝማች ከፈለው ወልደ ጻድቅ ጋር ባምስቱ ያርበኝነት ዘመን አብሯቸዉ የነበረና አሁንም የቅርብ ወዳጅ መሆኑ ነበር።

የሻምበል ጌታነህ ለኛ ጥሩ ቢሆንም፣ የእርሱ መልካምነት ብቻ የእኛን የእሥር ቤት ኑሮ ጥሩ ስለማያደርገው አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብን አመን። በዚህም መሠረት ይህን አሽከርና ወዳጅ የሃምሣ አለቃ፣ አንድ ቀን እኛ ወዳለንበት ክፍል አስገብተን ጨዋና ጠንቃቃ ነህ በማለት ስናሞጋግሰው ነገሩን ለማወቅ ፈልጐ ጆሮውን ሰጥቶ ማዳመጥ ጀመረ። እየተግባባን መሄዱዳችንን ስንረዳ፣ ደጃዝማች ከፈለው ወልደ ጻድቅ አሉ ከሚባሉት ታላላቅ አርበኞች አንዱ መሆናቸው የታወቀ ሆኖ ሳለ፤ የሚገባቸውን ማዕረግና ሥልጣን አለማግኘታቸውን እና መፈንቅለ መንግሥቱ ተቃንቶ ቢሆን ኖሮ እርሳቸውን ለከፍተኛ ቦታ አጭተናቸው እንደነበር አነሳንለት። እውነት መስሎት ልቡ አበጠ። ነገሩንም እንደሆነ ቆጠረው። በሁኔታውም የመተማመን ምልክት አሳየን። ያርበኝነት ጊዜ ስሜትና ወኔውም ተቀሰቀሰና ቁጭት አደረበት። ቀጥሎም በኩራት መንፈስ «ባለውለታው ጌታዬ አልተጠቀመም፤ ተገፍቷል፤ ተጨቁኗል፤» በማለት ተነፈሰ። እኛም ቁጭቱን የሚያባብሱ ነገሮች ጨማመርንለት። በመጨረሻም ተደስቶና አመስግኖ «ስማችሁን በወረቀት ጻፍ አድርጋችሁ ስጡኝ፣ ወስጄ በጃቸው እሰጣቸዋለሁ» አለ።

በዚሁ መሠረት እሥራት፣ እኔ፣ ብዙነህና መኮንን ተማክረን ለአራት አንድ ደብዳቤ ጻፍንና የተቀሩትም በንባብ እንዲሰሙት አድርገን ሳንፈርም በስም ዝርዝር ብቻ ተዘጋጅቶ ተሰጠው። ደብዳቤው በተላከበት ሰሞን አንድ ዓመት በዓል እንደነበር ትዝ ይለኛል። ደጃዝማቹ አጋጣሚውን በመጠቀም አንድ በገፈጅ ድስት ወጥ፣ አንድ ሞሰብ እንጀራ ቀሚስ ለብሶ፣ በአንድ መንቀል ጠጅ፣ በአንድ መንቀል ጠላና በአንድ ጠርሙስ አረቄ ታጅቦ ዝክር ነው ተብሎ ተላከልን። ያን ያዩ ያገሬው እሥረኛ እንዳያማ ብዙ እንጀራና ወጥ ተላከለት። እኛም ለተደረገልን ሁሉ ምስጋናችን እንዲደርሳቸው በማድረጋችን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ተልኮልናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከኊናችን ያሉት እሥረኞች ንግግር አጥሩን አልፎ እነሱ የእኛን እኛም የእነሱን እንሰማ ነበር። እንዲያውም አንድ ትልቅ ባለውቃቢ (ቃልቻ)

ነው የተባለ እሥረኛ ሁልጊዜ የዛር ዘፈን እያወረደ ሲዘይር፣ እንሰማ ነበር። በተለይ «አርሂቡ ቡናው ሰከነ፣ አርሂቡ ቡናው ሰከነ፣ ሳላይሁ ልቤ ባዘነ፣ ሳላይሁ ልቤ ባዘነ...» የሚል ግጥም ደጋግሞ ይዘይራል፣ እንዲሁም ሕልም የማየትና የመፍታት ችሎታ እንዳለውም ይነገር ነበር። ባለውቃቢው ቡና የተጠጣበትን ፍንጃል ዓይቶ ይጠነቁላል ስለተባለ፤ ሻምበል አሥራት የሳይኮሎጂ ምሑር (ለማስተርሱ ይሠራ) ስለነበረ ለመመራመር ቡና ጠጥቶ ፍንጃሉን ሳከለት። ባለ ውቃቢውም ዓይቶ «አንተ ብዙ ጊዜ በእሥር ትቆያለህ፤ ቶሎ የምትፈታ መስሎህ እንዳትጓጓ» ብሎ መልሱን ላከለት። ይህ በዚህ እንዳለ ባለውቃቢው ከዕለታት አንድ ቀን ሌሊት ተነስቶ "ሕልም ዓየሁ" ብሎ ጧት አብረው ላሉ እሥረኞች ይነግራል። «ሕልሙ ምንድነው?» ሲባል፤ «አንድ ትልቅ ዋርካ ከሁለት ተሰንጥቆ አንድ ጕኑ ሲወድቅ ዓየሁ» ይላል። «ታዲያ ምንድነው?» ሲባል «ዋርካ ትልቅ ሰው ነው። ከትልልቆቹ አንድ የሚወድቅ ሰው አለ» ብሎ ይናገራል። ይህን በሰማንበት ጊዜ ለሕልሙም ለፍችውም ዋጋ አልሰጠነውም። ቁም ነገር ውስጥም አላገባነውም።

በማልስቱ ግን ጧት እዳሪ (ለሽንት) «አትወጡም» ተብለን ቤት ተዘግቶብን «ምንድነው?» እያልን ቆየን። ረፈድ ካለ በኋላም በሹክሹክታ አንድ ነገር ተሰማ። ይኸውም «አዲስ አበባ አንድ ችግር አለ ይባላል» አሉን። «ምንድነው ችግሩ?» ብለን አቆብቁበን ቆምን። «ዶሮ ብታልም ጥሬዋን» እንደተባለው መፈንቅለ መንግሥት ይሆናል ብለን ልባችንን ተንጠለጠለ። አምስት ሰዓት ሲሆን «ግርማዊት እቴጌ አረፉ ይባላል» የሚል ዜና ሰማን። ከዚያ እንደቀድሞው ሳይሆን እሥረኛው በጥቂት በጥቂቱ እየሆነ እዳሪ እንድንወጣ ተፈቅዶ ወጣን። በዚህ ጊዜ የሰውዬውን ሕልምና ፍች አደነቅን።

ይህ በዚህ እንዳለ በየሁለት ሳምንቱ ለሕግ ክርክር እኛን ከደብረ ብርሃን ወደ አዲስ አበባ ማመላለሱ ለወህኒ ቤቱ አስተዳደር የትራንስፖርትና ያጃቢ ወታደር እጥረት ችግር ፈጥሮበት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ቤተዘመዱም፣ ወዳጁም ወደ አዲስ አበባ እንድንመለስ የወህኒ ቤቶቹን አስተዳደር ረዳት ሚኒስትር አቶ ጫንያለው ተሾመን ያስቸግር ነበር። ወቅቱ የጥሎ ማለፍ ጨዋታ ጊዜ ቢሆንም፤ አቶ ጫንያለው የኛን መታሠር የመወጣጫ መሠላል ከማድረግ ይልቅ በተለያዩ መንገዶች በቅንነት ሊረዱን ይጥሩ ስለነበር፤ ከላይ በተጠቀሱት የወህኒ ቤቱን ችግሮች ምክንያት በማድረግ ከበላይ ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው ወደ አዲስ አበባ እንድንመለስ አስወሰኑ። ውሳኔው እኛንም ቤተሰቦቻችንንም ከብዙ ችግር ገላገለ።

አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ስንመለስ የእሥራት ጊዜያችንን ካንድ ዓመት በላይ አሳልፈናል። ሆኖም እንደ አዲስ እሥረኛ ወይም አደገኛ እሥረኛ ዓለም በቃኝ አስገቡን። ዓለም በቃኝ እንደገባን ወደ ማታ ዘጠኝ ተኩል ገደማ ሲሆን፤ ካቦው የየክፍሉን በር በውጭ ቀልፎ ከመዝጊያው ከፍ ብሎ በሚገኘው ክፍት የብረት ፍርግርግ ተጠግቶ በማየት እሥረኞች በትክክል በያንዳንዱ ክፍል መኖራቸውን ለማረጋገጥ ቆጠራ ያደርጋል። ድምሩንም ለተረኛው ኃላፊ ይሰጣል። ይህ እስከ አሥራ

አንድ ሰዓት ያላለቀ እንደሆን ግማሽ ሰዓት በመጨመር ቆጠራ ይካሔዳል። ምንም ቢሆን ምን ከአሥራ አንድ ሰዓት በኋላ ውጪ የሚቆይ እሥረኛ አይኖርም፤ በተለየ ምክንያትና የታመሙ እሥረኞች ካልሆኑ በቀር። ካቦው የክፍሉን እሥረኛ ቆጥሮ የሚያስረክበው ማታ ይሁን እንጂ በምሣ ጊዜም ከቁጥር የጐደለ እሥረኛ እንዳለ ቁጥጥር ያደርጋል። የጐደለ ካለ እከሌ የት ሔደ? የት ቀረ? ብሎ ያን ሰው ማግኘትና ማረጋገጥ አለበት። ፈልጐ ካላገኘ ተጠያቂ በመሆን ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ያጣልና።

ቁጥጥሩ በጣም ጥንቃቄ የሚበዛበት የቀጠሮ ክፍል ነው። የቀጠሮ እሥረኛ የጠፋ እንደሆን ፍርድ ቤቱ ወህኒ ቤቱን አጥብቆ ይጠይቀዋል፤ በቀላሉም አያልፈውም። "የሰደደው አውቆ ተመሳጥሮ በገንዘብ ተገዝቶ ነው" በሚል ጥርጣሬ ጭምር ሊከሰው ስለሚችል በዚያ ክፍል ያለ የእሥረኛ ቁጥጥር የጠበቀ ነው።

## የወህኒ ቤት ቆይታ ትዝብት፣ አርቆ[17] ማቃናት

በወህኒ ቤት ፅንሰ ሐሳብ ጥፋት የሠራ (የሕግ ጥሰት ድርጊት የፈፀመ) ሰው በሕግ ተይዞ ወህኒ ቤት መቆየቱ፤ ሰውየው ጥፋት በፈፀመበት ወቅት የነበረው ያውሬነት ጠባይ እንዲወገድለት፣ በወህኒ ቤት በሚቆይበት ጊዜ ጥፋቱን ተገንዝቦና ተፀፅቶ ተመልሶ ከኅብረተሰቡ ጋር ሲቀላቀል መልካም ሥነ ምግባር እንዲኖረው ለማብቃት አርቆ ማቃናት እንጂ ለመበቀል እንዳልሆነ ይነገራል። የወህኒ ቤቶች መቋቋም ፅንሰ ሐሳብና መንፈሥ እንዲህ አርቆ ማቃናት ሆኖ ሳለ፤ የኛ አገር ባለሥልጣኖች ግን እሥረኞችን ይዘው የሚያቆዩት ከዚህ በተቃራኒው ለመሆኑ ሩቅ ያሉትን ትተን ከመናገሻው ከተማ እምብርት አዲስ አበባ ወህኒ ቤት በቂ ምስክር ነው። እኛ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ገብተን ሥራ እስከ ተደለደልንበት እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ድረስ ፍርድን አግኝቶ በፀባዩም በወህኒ ቤቱ ኃላፊዎች የማምለጥ ጥንካሬ የለውም ወይም ሙከራ አያደርግም ተብሎ የታመነ፤ በጓሮ አትክልተኝነት ሥራ ይመደባል።

ፍርድ አግኝቶ ታማኝነቱ አጠራጣሪ የሆነ እሥረኛ ሊናፈስ ከወጣ ከላይ ሰማይ ከታች ኮረኮንች ድንጋይ በግራና ቀኝ የቆርቆሮ ቤት ተዋጊ የሽቦ አጥርና ግንብ ከስልሳ ሣንቲ ሜትር ያልበለጠ ስፋት ያላት ተጠቅልላ የተሰቀለች ምንጣፍና በብዙ መቶ ክሮች እርዳታ የተያዘች ድሪቶ ቆጥ ላይ ተሰቅሎ ከሥር የሻይና የቡና ወይም የውሃ መጠጫ ጣሳ፣ የወጥ መቀበያ ሳህን፣ ውሃ መያዣ ጣሳ አሊያም ኮዳ ወይም ማንቆርቆሪያ … ወዘተ. ሌላም ሌላም ቅራቅንቦ ከበው የያዙት እሥረኛ ነበር ያገኘነው።

በተራዘመ እሥረኛነት ቆይታ ያለምንም ተስፋ የዘለቀው እሥረኛ ወይ ይፈታል አሊያም ያብዳል። ከገፋም እዚያው እሥር ቤት ይሞታል። ሲፈታም አብዛኛው ባካልም በመንፈስም ጤነኛ ሆኖ አይደለም። ይህ ደግሞ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚነትን አያስገኝም። የተቋሙ ሕልውና ብቻ ደግሞ ኅብረተሰቡን ከወንጀለኛነት ነፃ አያደርግም። እሥረኛው በሚያጋጥመው የጤና ችግር የሚታከመው በወህኒ ቤቱ ክሊኒክ ነው። የወህኒ ቤቱ ክሊኒክ የማከም አቅሙ በጣም ውስን በመሆኑ ታካሚውን እሥረኛ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሁለት እጁን በበሽታው ላይ ታሥሮ ወይም ከሌላ በሽተኛ እሥረኛ ጋር ተቆራኝቶ፤ ወደ ፍርድ ቤት በሰንሰለት ታሥሮ እንደሚሔደው ዓይነት ነበር የሚላከው።

ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው የማይጠየቋቸው፣ ልብሳቸው በላያቸው ላይ አልቆ ዓለም በቃኝ ከ፲፮ እስከ ፳ ዓመት ቢታሠሩም፤ ገና ፍርድ ያላገኙ ወይም ተወስኖ ፍርድ ያልተፈፀመላቸው ብዙ ናቸው። በጣም ከሚያሳዝነውና ከሚዘገንነው አንዱ ሞት ተፈርዶባቸው ፍርዱ ሳይፈፀም ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመት በወህኒ ቤት የሚያሳልፉት ሰዎች ሕይወት ነው። ሰዎቹ ከፍርዱ ክብደት የተነሳ


---

[17] *የተጣመመ እንጨት እስኪዘረጋ ከባድ ነገር ተጭኖበት እንደሚቃና ሁሉ የሰውም ጉባጣ ባህርይ በእሥር ቅጣት ወደ መልካም ማኅበራዊ ኑሮ እንዲመለስ ባህሪው የሚገራበት ሁኔታ*

ቤተሰቦቻቸው ሁሉ ርቀዋቸው፣ የዓመት ልብሳቸውን የሚሰጣቸውና የሚጠይቃቸው ስለሌለ ስሚንቶ ላይ የሚተኙበት ጉናቸው በልዞ ቅጥራን[18] የተቀባ የሚመስል በብርድ ያረረ ገላቸው እስኪታይ ይደርሳል። ሁኔታው ዓለም በቃኝን ሰው ለሰው ልጅ የፈጠረው ምድራዊ ገሀነም አድርጎ ያሳያል። ሞቱን ፈልጎ ሞቱን ያጣ፣ ብዙ ነው። ሞት ርስት ነውና! ትሞታለህ ከተባለ በኋላ አሥርና አሥራ አምስት ዓመታት ታሥሮ በሥቃይ የሞት ቅጣት ሲፈፀምበት ማየት እጅግ ዘግናኝ ነው። ይህ የሞት ሞት ሁለት ቅጣት እንጂ አንድ ሞት አልነበረም። የሞት፣ የዕድሜ ልክ፣ የሃያ አምስት ዓመት እሥራትና የጅራፍ ቅጣት ተፈርዶባቸው በዓለም በቃኝ ወህኒ ቤት ከታሠሩት እሥረኞች መካከል የጥቂቶቹን ሕይወት እዚህ ጋር ማንሳት የችግሩን መጠን የበለጠ ግልጽ ያደርጋል።

## ደጃዝማች አበረ ይማም

ከ፲፱፻፶፮ እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በጉጃም ጠቅላይ ግዛት የአገው ምድር ሕዝብ "ግብርና አሥራት በዝቶብናል" ብሎ ለመንግስት አቤቱታ አቀረበ። ሰሚ ግን አላገኘም። ስለዚህ የአገሩ ሕዝብ ደጃዝማች አበረ ይማምን መሪ አድርጎ ዐመፀ። ይህን ተከትሎ የመንግሥት ጦር ተልኮበት በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ውጊያ ተካሒዶ በግራ ቀኙ ወገን ብዙ ሰው ሞተ፤ ንብረትም ጠፋ። በመጨረሻ ደጃዝማች አበረ ተይዘው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በፍርድ እንዲሞቱ ተወሰነባቸው። በዚህ የተነሳ የደጃዝማች አበረ ይማም እናት ከደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ ጋር ቅርብ ዘመድ ሲሆኑ፤ በአርበኛነቱም በእኩልነት የሚታይ ጀብድ የፈፀሙ ነበሩና ከንጉሡ ዘንድ ቀርበው ይሄን ሁሉ በማንሣት በልጃቸው በደጃዝማች አበረ ላይ የተጣለው የሞት ፍርድ ቅጣት እንዲነሳላቸው ምሕረት ይለምናሉ። ጃንሆይም ልመናውን ተቀብለው "በይ አንገልብሽም" የሚል ተስፋ እንደሰጧቸው ይነገር ነበር። ይሁን እንጂ የንጉሡን ምሕረት



*ደጃዝማች አበረ ይማም*

[18] ቆዳው በብርድ ተቃጥሎ ካትራሜ የተቀባ እስኪመስል የጠቆረ ገላ



ደጃዝማች አበረ ይማም

አስመልክቶ ለወህኒ ቤቱ በጽሑፍ የመጣ ነገር ስላልነበረ በወህኒ ቤቱ የሞት ፍርድ ሊፈፀም በየጊዜው ጥሩምባ ተነፍቶ እሥረኛው በየክፍሉ ክተት በተባለ ቁጥር፤ ደጃዝማች አበረ ይማም ዛሬ ይገድሉኝ ይሆናል በሚል ሥጋት ሁልጊዜ ለሞት ተዘጋጅተው የክት ልብሳቸውን ለብሰው ጥሪ ሲጠብቁ እንደሚኖሩ ዓይተናል።

## ባላምባራስ በከሬ

እንደ ደጃዝማች አበረ ይማም በየጊዜው ከሚሞቱት ጋር የሚሞቱ ሌላው ታሣሪ ባላምባራስ በከሬ ነበሩ። ራስ ደስታ ዳምጠውና ባላምባራስ በከሬ የጉራጌ ባላባቶች ሲሆኑ፤ በመካከላቸው የርስት ክርክር ነበራቸው ይባላል። በዚህ ቁርሾ ባላምባራስ በከሬ የጣሊያን ጦር ደጋፊና ተባባሪ በመሆን ጦራቸውን አዝምተውና ራስ ደስታ ዳምጠው ያሉበትን ቦታ ጠቁመው አሳይተው አስገድለዋል በሚል ተይዘው ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ጀምሮ ያለፍርድ ታሥረው የኖሩና እኛ ስንገባ እዚያ ያገኘናቸው የስማንያ ሦስት ዓመት አዛውንት ነበሩ። እኒህ ሰው ነጋ ጠባ ከዛሬ ነገ ይገሉኛል በማለት ነፍሳቸው እንደ ጨርቅ እየተቀደደች ዕድሜያቸውን ያሳለፉ ናቸው።

## ቀኛዝማች ንጉሤ[19]

በኦጋዴን የፊታውራሪ በኋላ ደጃዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማያት የጦር አዝማች የነበሩት የቀኛዝማች ንጉሤ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አልነበረም። ቀኛ ዝማች ንጉሤ እንደነገሩኝ ጣልያን በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኦጋዴን በወልወል በአቢሬ ወረዳ በቆራሔ በየጊዜው ትከፍተው በነበረው የጦር ትንኮሳ ፊታውራሪ (ከሞቱ በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ በነዚህ ቦታዎች ጠላትን ሲከላከሉ ቆራሔ ላይ በነበረው ጦርነት ከአውሮፕላን በተጣለ የቦምብ ፍንጣሪ ጭናቸው ላይ በከባድ ሁኔታ ቆሰሉ። አስፈላጊውን ሕክምና ባለማግኘታቸው እግራቸውን ተልቶ መንቃነቅ ቢያቅታቸውም፤ ጦሩ ይህን አውቆ እንዳይበተን ችግራቸውን ችግር አርገው ችለው ከምሽጋቸው ውስጥ ሆነው ሲከላከሉ ሞቱ።



*ፊታውራሪ (በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ ወልደ ሰማያት*

---

[19] *ስለፊታውራሪ (ከሞቱ በኋላ ደጃዝማች) አፈ ወርቅ ወልደ ሰማያት የመጨረሻ ሰዓት ሁኔታ የሰማሁት ከቀኛዝማች ንጉሤ ጋር አብረን አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ሳለን ነው።*



ፊታውራሪ (በኋላ ደጃዝማች) አፈወርቅ ወልደ
ሰማያት

በመካከል ቀኛዝማች ንጉሤ ኃላፊነቱን ከፊታውራሪ አፈወርቅ ተቀብለው በደጋሐቡር ቆራሔ በተባለው ቦታ ከፍተኛ የመከላከል ግዳጅ እየተወጡ ሳሉ፤ ፊታውራሪ አፈወርቅ ወልደ ሰማያት ከነሠራዊታቸው ለጣልያን ገብተዋል፣ የሚባል ወሬ በቤተ መንግሥት ተሰምቶ ኑሮ ይህን ሔዶ የሚያጣራና እውነት ሆኖ ከተገኘ ቢቻል እጃቸውን ይዞ የሚያመጣ፣ ባይቻል እዚያው ገድሎ የሚመለስ ፲፰ በመንግስት የተመረጠ ምርጥ ተኳሾችን የያዘ አንድ ቡድን ወደዚያ ይላካል። ቡድኑ እዚያ ሲደርስ ፊታውራሪ አፈወርቅ እንኳንስ ለጣሊያን ሊገቡ የደረሰባቸውን ከባድ ችግር ችለው ያገራቸውን ድንበር ላለማስደፈር በጀግንነት በመከላከል ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ከቡድኑ መሐል የመጡበትን ምስጢር ላገኙዋቸው አንዳንድ ሰዎች አውጥተው የነገሩ ኖሮ ከቀኛዝማች ንጉሤ ጆሮ ይደርሳል። በዚህ ጊዜ ቀኛዝማች ንጉሤ «እኔ ንጉሤ ነኝ በዚህ የተጠረጠርኩት? አገሬን ከድቼ ነው እንዲህ ያለ ሥራ የምሠራው?» በማለት ተናደው «ወላሂ! ከንግዲህ ወዲያ ለኃይለ ሥላሴ አልገዛም!» ብለው ክርስቲያኑ በእስላም ደንብ መሐላ ምለው፣ በሠራዊቱ መሐል እሩጠው ወደ ጣሊያን ጦር ገቡ። ቀኛዝማች ንጉሤ የተቀየሙዋቸውን ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ለመጉዳት ከጣሊያን ጦር ጋር ሁነው የኢትዮጵያን ጦር ወግተው ስለነበር፤ ነፃነት በዚህ ጥፋት ከ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ተይዘው ያለ ፍርድ ታሥረው የኖሩና እኔም ስፈታ እዚያው የነበሩ ናቸው። ጥፋተኛ ማነው? «ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ» እንደተባለው ዓይነት ባይሆን ኖሮ።

ቀኛዝማች ንጉሤ አንድ እግራቸው ተረከዝ ላይ በጥይት ተመተው ጅማታቸው ተበጥሶ ያነክሳሉ። አንዳንድ ጊዜ ሀዘኔታ የራቀው እሥረኛ ደህናውን እግራቸውን ከኋላ ሳያስቡት ወደፊት ሲገፋባቸው ሔደው በቂጣቸው ዘጭ ብለው ይወድቁና በንዴት በሽጉጥ አተኳከስ መልክ ጣታቸውን ወደ ገፋቸው ሰው አዙረው "ፑም! ፑም! ወይ ሽጉጥ! ወይኔ ንጉሤ!" እያሉ ሲናደዱ ያስቁም ያሳዝኑም ነበር። እኚያ ጀግና በዚህ ክብረ ቢስ ሕይወት ዕድሜያቸውን እስከመጨረሻው ሰዓት ሲገፉ ማየት በእጅጉ ያሳዝን ነበር።

## ማሞ ይንበርበሩ

በወህኒ ቤቱ ከነበሩት እሥረኞች ለየት ያሉና እኔም የማደንቃቸው እሥረኞች ነበሩ። ከእነዚህ አንዱ ማሞ ይንበርበሩ ናቸው። የአቶ ማሞ አባት አቶ ይንበርበሩ ከጠላት መምጣት በፊት በሥራ ወደ ኢሊባቦር ጎሬ ተመድበው ሳለ በማይጨው ጦርነት ዘምተው እዚያው የተሰው ናቸው። ማሞ ይንበርበሩ በወቅቱ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሲሆኑ እናታቸውም ሞተው ስለነበር ያለተንከባካቢ እዚያው ሳሉ ድል አድርገው ከገቡት የጣሊያን ጦር መኮንኖች አንዱ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ይዟቸው መጥቶ ሰይጣን ቤት አጠገብ የነበረው የመኮንኖቹ ማረፊያ አካባቢ ተጠግተው ምግባቸውን እያገኙ እንዲኖሩ ትቷቸው ሔደ። ንቁውና ትጉሁ ማሞ በአቅራቢያው የሚገኝ ሻይ ቤት ብርጭቆ በማጠብና በመላላክ በፈንታው ምግባቸውን እያገኙ መኖር ጀመሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአራት ኩቼኔታ የሚሽከረከር ሰው ማስቀመጫ ያላት መንሽራተቻ

በመሥራት ከሰይጣን ቤት (ቴዎድሮስ አደባባይ) እስከ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ድረስ ልጆችን ኩሼኔታው ላይ እየጫኑ ይዘው በመንተት ማንሸራሸር ጀመሩ። በእንዲህ ዓይነት ዘዴ ብዙ ገንዘብ ማግኘት ከቻሉ በኋላ ደግሞ ካቴናና ፔዳል የሌለው አሮጌ ብስክሌት ከመነዳሪያ ጎማውን በጠገራ ብር ልክ በመቁረጥ መሐሉን በስተው አደራርበው በማሠር ተሽከርካሪ አበጅተው ልጆችን በማስቀመጥ እየጐተቱ በማንንዝና በማዝናናት ገቢያቸውን አሣደጉ። በሠፈሩ ይህን የማሞን ብርታት ያየ ጣሊያን ጦር መኮንን ወደምፅዋ ይሄቸው ሔዶ ሃያ የሚሆኑ ባለጎማ ብስክሌቶች ገዝተው እንዲመጡ ስለረዳቸው ከዚያ በኋላ እያከራዩ ብዙ ገንዘብ አገኙ።

በዚህ መሐል የጣሊያን መንግሥት ወድቆ የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ጦሩ በርካታ የጣሊያን መኪኖችን ይሸጥ ስለነበር በ፻፷ ብር ፎርድ ጊካፕ ገዙ። በዚያ መኪና ከአዲስ አበባ ወደ ወሊሶና ወልቂጤ ማመላለስ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የሰላ የጥርጊያ መንገድ ስላልነበረ ጉዞው አመቺ ሆኖ በተገኘው መንገድና አቅጣጫ መንዝ ነበር። ክረምት ክረምት መሬቱ ረጥቦ ጭቃ እየሆነ ይይዝ ስለነበር ተሣፋሪው ዕቃውን አውርዶ ወደደረቁ ቦታ ተሸክሞ መሔድና መኪናውንም እደረቁ ቦታ ድረስ በግፊ መውሰድ ግድ ነበር። ከዚያ እንደገና ይጫንና ተመሣሣይ ችግር እስከሚያጋጥም በመኪናው ጉዞ ይደረጋል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ከመነሻው እስከመድረሻው ሁለት ሦስት ጊዜ ሊያጋጥም ይችል ነበር። አቶ ማሞም በዚህ መልኩ ቀጥለው ኋላ ትልቅ መኪና ገዝተው ከወሊሶ እስከ ጅማ መድረስ ቻሉ። ምንም ዓይነት ጥገና ባልተደረገለት በዚህ መንገድ ለመሔድ ይፈጅ የነበረውን ሦስት ቀንም እርሳቸው ባገኙት መንገድ በመስክ ጨምሮ በማቋረጥ በአንድ ቀን ተኩልና በሁለት ቀን ይገቡ ስለነበር፤ ማሞ ይንበርበሩ መታወቂያና መጠሪያቸው የሆነውን ማሞ ካቻ[20] የተባለውን ስማቸውን አገኙ። ይህ ስም እስከ መጨረሻው ድረስ የመኪናቸው ዓርማና የእሳቸው መታወቂያ ሆኖ ኖረ።

አቶ ማሞ በመጓጓዣው አገልግሎት እንዲህ እያደጉ በነበሩበት ወቅት በዘርፉ ታዋቂ ከነበሩ ሌሎች ሰዎች ቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ፣ ቀኛዝማች አሻግሬ፣ አቶ ንጋቱ ፈለቀና ቀኛዝማች አንዳርጌ ይታወቃሉ። ከነዚህ ሰዎች ውጪም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ንብረት የሆነው አንበሳ አውቶቡስ ድርጅትም ነበር። ይህ ድርጅት ሻል ሻል ያሉ መስመሮችን ይወስድ ስለነበረ፤ በተለይ አቶ ማሞ ሌሎቹም የመጓጓዣ አገልግሎት ሰጪዎች እንዲህ ዓይነቶቹ ቦታ ላይ የመመደብ እድል እንዲሰጣቸው ከመንትጎት አልፈው በየስማቸው ማህበር በማቋቋም አውቶቡሳቸውን ቁጥር ለመጨመርና በሁሉም መስመር የመሳተፍ ዕድላቸውን ለማሣደግ ጥረዋል።

---

[20] የጣሊያን ፈጣኑ መትረየስ ተኳሽ አውሮፕላን ካቻ ነው የሚባለው። አሁን ተዋጊ ጀት እንደምንለው ዓይነት መሆኑ ነው።

እነ አቶ ማሞ ለመደራጀት በውጥን ላይ ሳሉ አንድ ከእርሳቸው ጋር ቀደም ብሎ ጭቅጭቅ የነበራቸው ሰው ሞተው በመገኘታቸው አስተማማኝ ማስረጃ ባይኖርም ሊኖሩበት ይችላሉ በሚል በጥርጥር ተይዘው ፲፩ ዓመት እሥራት ተፈረደባቸው። በመጓጓዣው አገልግሎት ያላቸው አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ ስለገባ ግን በሣምንት ሁለት ቀን የድርጅታቸውን ሥራ እንዲያከናውኑ ተፈቅዶላቸው ድርጅታቸውን ይመሩ ነበር። እኛ ወህኒ ቤት ስንገባ አቶ ማሞ ካቻ አራት/አምስት ዓመት ሆኗቸው ነበር።

አቶ ማሞ ወደ እሥር ቤቱ ከመግባታቸው በፊት ምንም የቀለም ትምህርት ያልነበራቸው ቢሆንም እየንተጉቱን እንግሊዝኛና አማርኛን ንባብ ጠንቅቀው ከማወቃቸው ባሻገር መደበኛ ሒሳብም መሥራት ችለዋል። አቶ ማሞ በ፲፱፻፷ዎቹ መግቢያ ከወህኒ ቤት ወጥተዋል። ከእሥር ከወጡ[21] በኋላም አቶ ማሞ ድርጅታቸውን ለማሳደግ ጥረታቸውን የቀጠሉ ሲሆን በዚህ ጊዜ የሠሩት አስደናቂ ነገር አንበሣ አውቶቡስ ማኅበር ከጣሊያን ገዝቶ ካመጣቸው ፴ አውቶቡስ ጋር የተያያዘ ነው። አንበሣ አውቶቡስ ከጣሊያን ለመግዛት ከተስማማው ፴ አውቶቡሶች ገና ፲፰ቱ እንደገቡ ባልታወቀ ምክንያት ስድስት የሚደርሱት የፊት ጎማቸው እየፈነዳና እየተገለበጡ አስቸገሩ። በዚህ ጊዜ አቶ ማሞ ካቻ በራሳቸው ተነሳሽነት ምክንያቱን ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። ስለጉዳዩ እያሰቡበት የነበረው አቶ ማሞ አንድ ቀን ወደ ሻሸመኔ ሲሔዱ አንበሣ አውቶቡስ ጥሩንባ እየነፋ ከፊታቸው ወደ ባሌ ሲሔድ ያዩና ይከታተሉታል። በዚህ ወቅት ሻሸመኔን አልፎ ወደ ዶዶላ ከዚያም አልፎ ሲሔድ ቁልቁለት ላይ እንደደረሰ፤ ጎማው ፈንድቶ ከመንገድ ወጥቶ ከአለት ግድግዳ ጋር ይጋጫል። ይህንን የተመለከቱት አቶ ማሞ የችግሩን መንስኤ አሁን አገኘሁት አሉ። ከዚያም ወደጣሊያን ቶሪኖ በመሔድ ቀጠሮ ሳያስይዙ የፊያት ኩባንያን ፕሬዜዳንት ለማግኘት ጥያቄ ያቀርባሉ። ያለቀጠሮ መጥቶ ያውም አንድ ጥቁር ይህን ማለቱ ሲሰማ በአካባቢው ግርምትን ስለፈጠረ ስለሁኔታው ፕሬዝዳንቱ እንዲሰማ ተደረገና አቶ ማሞ ካቻ ተፈቅዶላቸው ፕሬዝዳንቱን ያገኛሉ።

ስለመጡበትም ሁኔታ ሲያስረዱ በኢትዮጵያ የአንበሣ አውቶቡስ ድርጅት ከኩባንያው ከገዛቸው አውቶቡሶች መካከል ኢትዮጵያ ከደረሱት ውስጥ አምስት/ስድስት የሚደርሱ የፊት ጎማቸው መፈንዳትና የመገልበጥ አደጋ እንደደረሰባቸው ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደሆነ እንዳወቁት እርሱም የቴክኒክ ስህተት እንደሆነ ነገሩት። በሁኔታው የተገረመው ፕሬዝዳንትም ኩባንያው ያሉትና በዕውቀትም በልምድም አገሪቱ ያፈራቻቸው ምርጥ መሐንዲሶች ያረጋገጡት ሥራ በመሆኑ ከምርት ጋር የተያያዘ ችግር እንደሌለበት ነገራቸው። እሳቸውም የለም ችግሩ ያለው ሲመረት ነው። ይኸውም የዕቃ ጭነቱና የመኪናው ሞተር ከፊት በመሆኑ፤ ሸክሙን

[21] ከተፈታን በኋላ በኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ውስጥ ለአባልነት አብረን ከመሥራታችን በተጨማሪ በግል ቅርብ ወዳጆች ነበርን።

አውቶቡሱ በመላ አካሉ ለማከፋፈል ስላዳገተው ክብደቱ ጫና በሚጠነክርበት በፊት ጎማው ላይ ጉዳት እያደረሰበት እንደሆነ ገለጹለት። ፕሬዝዳንቱም ነገሩ ከበድ ብሎ ስለታየው የማምረቻ ፋብሪካውን ዋና ዋና መሐንዲሶችን ጠርቶ የአቶ ማሞን ንግግር ሰምተው ማስታወሻ ከወሰዱ በኋላ አቶ ማሞ ከኩባንያው አዲስ አበባ ከመጡት አውቶብሶች እንዲሰጣቸው የጠየቁትን አንድ አውቶቡስ እንዲሰጣቸው ፈቀደላቸው። ስለዚህ የተሰጣቸውን አንድ አንበሣ አውቶቡስ አፍርሰው በቁመቱ ላይ አንድ ሜትር ከሃያ ጨምረው ዕቃ መጫኛውን ወደ መሀልና ወደ ኋላ በማድረግ አስተካክለው አስረከቡ። በዚህ ማስተካከያ የተጠገነው አውቶቡስ በተፈለገው ቦታ ሲሔድ ከተመሳሳይ አደጋ የራቀ ሆኖ ስለተገኘ፤ እርማቱ ትክክል መሆኑ ታዬ። ሁለተኛ አውቶቡስ ተሰጥቷቸው ስላስተካከሉት የአስተያየታቸውን ትክክለኛነት አረጋገጠ። የፊያት ኩባንያ የቀሩትንም በዚያው ዓይነት እንዲያስተካክሉ ለአቶ ማሞ ሊሰጡ ሲሉ የአንበሣ አውቶቡስ ማኀበር ራሳችን እናስተካክላለን ብለው ሥራውን ወሰዱ። አንበሣም እርሳቸው በሠሩት ዲዛይን አስተካከለ። የፊያት ኩባንያ ግን ለፈጠራቸው ወሮታ እንዲሆን ሞዴል ፪፻፩ መርሴዲስ ሸለማቸው።[22]

## ወርቁ ኃይለሥላሴ (በደልን የሚጠላ)

ወርቁ ቀይ፣ አጭርና ቀጭን የሰላሌ ሰው ነው። ወርቁ በተፈጥሮው ማንኛውንም ግፍና ኢፍትሐዊ የሆነ ሥራ የሚጠላና የሚቃወም ባህሪይ የነበረው ሰው ነው። እሱ አፍላ ዕድሜ በደረሰበት ጊዜ በአገሬው ሰው ላይ የሚሠራን ማንኛውንም ክፉ ሥራ አይወድ ስለነበረ፤ ክፉ አደረገ የተባለ አንድ ሰው በመግደል ሸፈተ። አሸፋፈቱ በራሱ ጉዳይ ሳይሆን ለሌላው መብት መጠበቅ በመሆኑ ጀግንነቱ ተወዶለት ብዙ ተከታይ አፈራ። እንደውም ሰው የገደለ፣ የበሬ ምላስ ቆረጠ፣ የበሬ ቋንጃ የቆረጠ፣ እህል ክምር ያቃጠለ፣ ቤት ቃጠለ፣ የሰው ሚስት አስገድዶ የወሰደ ሁሉ በአስቸኳይ ከተበዳዩ ወገን ጋር እንዲታረቅ፣ ችግሩን በዕርቅ ያልጨረሰ እንደሆነ ከየትም ቦታ አድኖ እንደሚይዘው አዋጅ አስነገረ። ይህንን ትእዛዝ ተቀብሎ ችግሩን ያልፈታ በጭፍሮቹ አሳዶ እያስያዘ በፍርድ እስከመስቀል ድረስ እየወሰነ ፳፩ ሰው በፍርድ ገሎ በመጨረሻ ተያዘ። ክሱን የተመለከቱት የከፍተኛ ፍርድ ቤትና ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሞት ፍርድ ሲበይኑበት፤ ቅጣቱ በንጉሡ ካልጸደቀ ስለማይፀና ዙፋን ችሎት ቀረበ።

---

[22] *እንዲህ ዓይነቱን ሳይማሩ የታደሉ ሰው ደርግ ወደሥልጣን ከወጣ በኋላ በጀመረው እንዲህ ያሉትን ዕድል ከፋች ሙያ ፈጣሪዎች አድሀሪዎች ናቸው በሚል ሠራተኞቹን በመቀስቀስ ካስነሳባቸው በኋላ ድርጅታቸውን ወርሶ በወዛደሩ ማኀበር እንዲተዳደር እርሳቸው በወር ፩ ሺህ ፩፻ ብር እየተከፈላቸው እንዲሠሩ ወሰነ። በዚህ ግዜ አቶ ማሞ «እኔ ከአያት ከቅድመ አያት የወረስሁትም ሆነ በሥልጣን በጉልበት ነጥቄ የወሰድኩት የለ፤ ሲሆን እኔ አንደኛውን እጄን በሌላኛው እጄ በመደገፍ እየቀጠቀጥኩ ሠርቼ ያፈራሁት ስለሆነ ለሌላው ጥሩ አርአያና ምሣሌ እንዲሆን ማቅረብ ሲገባ ምን ተብሎ ነው የምወረሰው? ከዚህስ ምን ትምህርት ይገኛል?» ሲሉ አጠንክረው የተከራከሩት። ያም ሆነ ይህ ድርጅቱን እንዲያስተዳድር የተሰጠው የሠራተኞች ማህበር ሥራውን በአግባቡ ማስኬድ ተስኖት ለሠራተኛው የሚከፍለው ደሞዝ እየጠፋ አራት አውቶቡስ እስከመሸጥ ደረሱ። ደርግ ሁኔታው ስላሳሰበው ድርጅቱን ለባለቤቱ ለአቶ ማሞ ካቻ መልሶ እስከ ሕልፈተ ሕይወታቸው ድረስ ሲስተዳድሩ ኖሩ።*

የተከሰሰበትን ግድያ የፈፀመበትን ምክንያት ሁሉ ዘርዝሮ ስላስረዳ የሞት ቅጣቱ ወደ ፳፭ ዓመት እሥራት ተለወጠለት። ከኃይሉ መግነን የተነሳ ከ፲፱፻፵፱ እስከ ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. አካባቢ በወርቁ አምላክ እተባለ ስሙ የሚጠራ ነበር። ቅጣቱን ሲጨርስ ተፈታ።

ወደ ቀደመ ነገራችን ስንመለስ ባጠቃላይ ወህኒ ቤቱ የእሥረኛን የዜግነት ስሜትን ግደታ የሚፈታተኑ ሁነቶች የሞሉበት ነበር ማለት ይቻላል። በመሆኑም እኛ እዛ ከደረስን በኋላ ነገሮችን ለመለወጥ ጥረት ማድረግ ጀመርን። የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስና እኔ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ትምህርት ቤት ለማቋቋም ተስማማን። ለዚህ ምክንያት የሆነን ብዙው ፍርደኛ ታሣሪ ቀን ቀን ያለምንም ሥራ ሲንገላወድ የሚውል መሆኑን በማየታችን ነበር። በወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ፲፬ በመቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንበብና መጻፍ አይችልም ብሎ የሰጠው አስተያየት ስላሳሰበው መንግሥትም ፊደል ሠራዊት የሚባል ድርጅት አቋቁሞ ትምህርትን ማበረታታት ጀምሮ ስለነበረ የእኛም ዕቅድ ይሄንኑ የሚደግፍ ሆኖ ተገኘ። በዚህ ምክንያት ዕቅዱን አውጥተን ማስታወሻ ያቀረብንላቸው የወህኒ ቤቱ አስተዳዳሪ ፈቃዳቸውን ሰጡን። ዕቅዳችንም ለትምህርት ቤት፣ ለቤተ መጻሕፍት አዳራሽና ለማንበቢያ የሚሆን ከፀሐይና ዝናብ መከለያ የሚሆኑ ሽፋን ያላቸው እያንዳንዳቸው አራት አራት ሰው የሚያስቀምጡ ስምንት ትንንሽ ሰቀላ ቤቶች (ጐጆዎች)ን አለፍ አለፍ እያልን ለመሥራት ነበር። ዕቅዳችንን ለወህኒ ቤቱ አስተዳዳሪ ለሻለቃ (በኋላ ሌ/ኮለኔል) ብርሃኔ ወልደየስ አቅረብን ስለተስማሙልን በወህኒ ቤቱ ግቢ ከነበሩ እርጎ ቤቶች ፍርስራሽ በተገኘ ቁሳቁስ የፊደል ማስተማሪያ የቤተ-መጻሕፍት አዳራሽና ማንበቢያ ኋላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን[23] ከተሠራበት ቦታ ላይ ሠርተን አገልግሎት መስጠት ጀመረን። ይህ ለወህኒ ቤቱ የመሻሻል ለውጥ የመጀመሪያ መሆኑ ነው።

በወህኒ ቤቱ ትምህርት ተጀመረ ማለት የለውጥ ብልጭታ ታዬ ማለት ነው። የትምህርት አሰጣጡ ጥሩ ችሎታ ባላቸው እሥረኞች ስለነበር፤ ለትምህርት የሚመጣው እሥረኛ ሁሉ ደስ ብሎት መምህራኑን አክብሮ ትምህርቱን ስለተከታተለ ብዙ እሥረኞች ባጭር ጊዜ ማንበብና መጻፍ እንዲሁም እስከ አራተኛ ክፍል የደረሰ ችሎታ አገኙ። ይህ የትምህርት ቤት ዕድገቱ እየቀጠለ ሔዶ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ካሉ ምስጉን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ እስከ መሆን ደረሰ። በአጋጣሚ ችግር፣ በልጅነት ዕድሜው ወህኒ የገባው የልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ ልጅ ልዑል በዕደማርያም የተማረውና የ፲ኛ ክፍልን መልቀቂያ ፈተና በከፍተኛ ውጤት ያለፈው በዚህ ትምህርት ቤት ነው። ይህ መልካም የለውጥ ጅምር የወህኒ ቤቱን አስተዳደርና እሥረኛውን ያስደሰተ መልካም ተግባር ነበር።

[23] አሁን የቻይና መንግሥት ለአፍሪካ ኅብረት ሠርቶ የሰጠው ሕንፃ የቆመበት ቦታ ላይ

ይህ በእንዲህ እያለ ዓመት ሳይሞላው ለቤተ - መጻሕፍት የሠራነውን አዳራሽ አሻሽለን ቤተ - ክርስቲያን እናድርገው ብለው የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ አማከሩኝ። በዚህ በመስማማት ይህንንም በማስታወሻ አዘጋጅቼ ለሌ/ኮሎኔል ብርሃኔ አቀረብን። እሳቸውም ለወህኒ ቤቶች አስተዳደር ረዳት ሚኒስትር ለአቶ ጫንያለው አስታወቁ። አቶ ጫንያለው ወህኒ ቤቱ ግቢ መጥተው የተመረጠውን ቦታ ዓይተውና ስለዕቅዱ አነጋግረውን ሐሳቡን ስለተቀበሉት ሥራው እንዲሠራ በመፍቀዳቸው ይህንንም በአካባቢው ከነበሩ አሮጌ ቤቶች በተገኘ ፍርስራሽ ቁሳቁስ ሠርተን ጨረስን። ጽላት አስመጥቶ አስባርኮ ለማስገባት ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተማርያም ወርቅነህን - (በካቢኔው የመፈንሣዊ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩትን፣ በኋላ አቡነ መልከጸዴቅን አሁን በስደት በአሜሪካ የሚኖሩ) ጠይቀን የቅዱስ ሚካኤልን ጽላት አምጥተው አስገብተው መንፈሳዊ ግልጋሎት መስጠት ተጀመረ።

በመቀጠልም የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስና እኔ እሥረኛ ለመጠየቅ ወደ ወህኒ ቤቱ የሚመጣውን ሕዝብ በፀሐይ ጊዜ ፀሐይ፣ በዝናብ ጊዜ ዝናብ ያስቸግር ስለነበር፤ መጠለያ የሚሆን ግባዛ (ስቀላ) መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ለወህኒ ቤቱ አስተዳዳሪ አስረዳን። አሁንም ተስማሙበት። በመሆኑም ከዚያው ከነበሩ አሮጌ ቆርቆሮ ቤቶች ቆርቆሮውን ወስደን ሠራን። ይህን ያልወደዱ አንዳንድ ለኃላፊዎች ቅርብ ነን የሚሉ እሥረኞች ግን በጠያቂውና በተጠያቂው መካከል ያለው ርቀት ቅርብ ነው። እጅ ለጅ መነካካት ይቻላልና ለወህኒ ቤቱ አደጋ ያመጣል ብለው እራሳቸው እሥረኞች ለኃላፊው ስላመለከቱ፤ አስተዳዳሪውና የጥበቃ ኃላፊው መጥተው ዓይተው "አራርቁት" አሉን። ለማራራቅ አፍርሶ መሥራት የሚያስፈልግና ለዚህ ደግሞ ምስማርና እንጨት ስለማይገኝ ባይሆን መደገፊያ ተብሎ ከተያዘው እንጨት ሰዎች ተጠግተው እንዳይቆሙ ራቅ አድርጐ የሚያቆም በሽልፍ ዓይነት በሠፊ ጣውላ እንዲራራቅ ብናደርግ ተብሎ እንደዚያ ተሠራና ጠያቂና እሥረኛ ተገለገለበት።

የመቶ አለቃ በቀለና እኔ በሠራነው ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ-ክርስቲያን ምክንያት ብዙ እንቀራረብና ብዙ ነገሮችን ያጫውቱኝ ነበር። የሚቀርቧቸው እሥረኞች ከእኔ ጋር ስላላቸው ቅርርብ ሲጠይቋቸው የሚመልሱላቸው "ብርሃኑ ልብ ይላል፣ ያስተውላል፣ ይታገሣል" ብለው ስለሚገምቱ እንደሆነ ይነግሩዋቸዋል። አሁንም ይህን የምንግረውን ዝም ብሎ ሰምቶ ይይዘዋል። አንድ ቀን ለሕዝብ እንደሚያወጣው ተስፋ አለኝ ይሉ ነበር። እውነትም ትንቢታቸው ደርሶ ይኸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ገብቶ ሕዝብ እንዲያውቀው ሆነ። በዚህ አጋጣሚ ስለመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ጥቂት ማለት ያስፈልጋል።


## የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ

የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ትውልዳቸው ከጉራጌ ሕብረተሰብ ሲሆን፤ ያደጉት በአቡነ ማቲዎስ ሊቀ-ጳጳስ ዘኢትዮጵያ ግቢ ነው። መቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ከጠላት መምጣት በፊት በነበረው የክብር ዘበኛ ጦር አባል የነበሩና ስዊዝና ቤልጂግ ሔደው በመድፈኝነት ሙያ ሠልጥነው የመጡ መኮንን ናቸው። የመቶ አለቃ በቀለ ሠልጥነው በመጡበት የመድፈኝነት ሙያ ዘመናዊውን የክብር ዘበኛን ሠራዊት አሠልጥነው የክብር ዘበኛ ሠራዊት እስከፈረሰበት እስከመጨረሻው ጊዜ እንደተጠቀመበት የሠራዊቱ መኮንኖች ይናገራሉ። የማይጨው ዘመቻ ሲታወጅ የመቶ አለቃ በቀለ ከክፍላቸው ሠራዊት ጋር አብረው ዘምተው ብዙ የጦር ጀብድ የሠሩ መኮንን ናቸው። የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ጥሩ ወታደራዊ ተክለ ሰውነትና ቁመና ያላቸው ብርቱ የአገርና የወገን ፍቅር የሚያቃጥላቸው፣ በምንም ዓይነት መንገድ ወለም ዘለም የማይሉ ቁርጠኛ አቋም የያዙ መኮንን ናቸው። በዚህ ላይ አስተዋይና የመፍጠር ችሎታ የታደሉ ሰው ናቸው። መቶ አለቃው በማይጨው ጦርነት ጣሊያን ከአውሮኘላን ከጣላቸው በንቦች ወድቀው ያልፈነዱትን ቶሎ ደርሰው ካኘስሉን (አቀጣጣዩን) በመንቀል ፈንድቶ በወገን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በሙያና በድፍረት ወገንን ከእልቂት የታደጉ ሰው ነበሩ።



መቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ

የመቶ አለቃ በቀለ በማይጨው ጦርነት ንጉሡ ከጦር ሜዳው ሳይወጡ እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ድረስ እንዲፋለሙ፣ ካልሆነም ዘማቹ ጦር ወደየአገሩ ተመልሶ በሽፍትነት ጠላትን እንዲዋጋ የሚለው አቋም ያብዛኛው ወገን ውስጥ እንደነበር ይናገራሉ። አያይዘውም ይህ የአብዛኛው አቋም ሆኖ እያለ፣ "የማይጨው ጦርነት ከባድና አስከፊ ስለሆነ ንጉሡ ወደ ውጭ ሔዶ የውጭ እርዳታ ይዞ ቢመጣ ይሻላል የሚሉትን በጉኑ የነበሩትን (የእነ ወልደ ጊዮርጊስን) ምክር ተቀብሎ፣ ከጦር



መቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ

ሜዳ ሸሽቶ ወደ ጅቡቲ መሔዱን ስንሰማ በታላቅ ቅሬታና ተቃውሞ ውስጥ ከገቡት ዘማቾች አንዱ እኔ ነበርኩ" ይላሉ። ጃንሆይ፣ ወይም ንጉሠ ነገሥቱ የሚል ቃል ከአንደበታቸው አይወጣም። ባብዛኛው ንጉሡ ወይም እሱ ነው የሚሉት። የማይጨው ዘመቻ ተፈቶ ዘማቹ ሁሉ ወደመሰለው ሲሄድ የመቶ አለቃ በቀለም አዲስ አበባ ገብተው (በጣሊያን አስተዳደር ጊዜ) በግል ሥራ የኖሩ ሰው ናቸው። ከጠላት መልቀቅ በኋላ በተቋቋመው የክብር ዘበኛ ጦር ተመልሰው በመግባት በዚያው በሠለጠኑበት ሙያ በማሠልጠን ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ አነሣሽነት ተጠንስሶ በነበረው የመፈንቅለ መንግሥት አድማ ተባባሪ ተብለው የታሠሩ ናቸው። ስለዚህ ሁኔታ ሲገልጹ

> ክልፌ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ቤት ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ፊታውራሪ ደስታ ጦና፣ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ፣ ዮሐንስ ረምሐ፣ ጉዋለ (እጉዋለ)፣ አለቃ ፈጠነ፣ የሁለቱ ሰዎች ስም ተዘንጉኝ/ ስንወያይ በወላይታው ንጉሥ "በካኦ ጦና" ልጅ በፊታውራሪ ደስታ ጦናና በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ምስጢሩ ለንጉሡ ደርሶ፤ በስብሰባ ላይ እንዳለን መንግሥቱ ንዋይ አስከብቦ አስያዘን። ተከሰን ጉዳያችን በመደበኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በልዩ ፍርድ ቤት ታይቶ ተፈረደብን። ዳኝነቱ የታየው በዝግ ችሎት በመሆኑ የተከሰስንበት የወንጀል ዝርዝርና የኛን መልስ ሕዝብ አላወቀውም። እንዲያውቅ አይፈለግም ነበርና ነው።

ብለዋል።

በዚህ ክስ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸው ነበር። በኋላ ግን የዕድሜ ልክ እሥራቱ ወደ ፳፫ ዓመት እሥራትና ፳፫ ጅራፍ ተለውጦ የተገረፉ ናቸው። የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራን ስላስነሱት ምክንያቶች ሲዘረዝሩም፤

- ፩ኛ የማይጨው ጦርነት ከባድ ቢሆንም እስከ መጨረሻዋ የደም ጠብታ ድረስ ንጉሡ እዛው መዋጋት፣ ካልሆነም ዘመቻ ላይ ያለው ጦር ወደየአገሩ ተመልሶ በሽፍትነት ጠላትን መውጋት የሚል የብዙዎች አቋም ሆኖ ተይዞ ሳለ፤ ንጉሡ በዘማቹ ጦር ሳይሆን በጐኑ በነበሩ ሰዎች ምክር ወደ ውጭ ሄዶ እርዳታ ይዞ ቢመጣ ይሻላል የሚሉትን (የነወ/ጊዮርጊስን) ሐሳብ ደግፎ ሸሽቶ በመሔዱ፤
- ፪ኛ ጦር ሜዳ ላይ ፊሦ ለነበረው ዘማች ሠራዊት መመሪያ ሣይሰጥ ሾልኮ ሔዶ፤ ሠራዊቱን ለእልቂት በመዳረጉ፤
- ፫ኛ. የተያዘ ስንቅ ለዘማቹ እንዳይሰጥ መቆጠቡና ዘማቹ በረሃብ በመጎዳቱ በኋላም ጠላት በአውሮፕላን እንዲያቃጥለው በማጋለጡ፤
- ፬ኛ.ከውጭ ተመልሶ ወደ አገሩ እንደገባ ደግሞ እነዚህ ወንጀሎቹ እንዳይነሱበት የንግግር፣ የጽሑፍ እና የመሰብሰብን ነፃነት በመንሳቱ፤
- ፭ኛ እሱ እንዳይከሰስ የፍትሑን አካል ደካማ ያደረገ ወንጀለኛ ስለሆነ፤ እሱን ከሥልጣን ለማውረድ በማስፈለጉ፤

ናቸው ይሉናል።

የመቶ አለቃ በቀለ የገለጹልኝን እነዚህ ቁም ነገሮች ቀደም ብሎ በሌላው ምዕራፍ ላይ እንደተገለፀው ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋሪያት አርበኞች ባሉበት ሁሉ ባሠራጩት መልእክት ‹‹ያፈረሰ ቂስ ተመልሶ አይቀድስ››፣ ‹‹የሸሸ ንጉሥ ተመልሶ አይነግሥ›› የሚለውን አቋም የደገፈና የያዘ ነበር፡፡ በዚህ መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት (አጭር መግለጫ) በሚለው ንዑስ ርእስ ውስጥ የተገለጸው የጀኔራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ ጃንሆይን ያስቆጣ አስተያየትም ከዚህ ጋራ ተያያዥነት አለው፡፡ እውነትም ይህ በ፲፱፻፳፰ - ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ተቀስቅሶ የነበረው ዐድማ ብዙ ጊዜ የአርበኞች ዐድማ ተብሎ ይነገር ነበር፡፡ እንዲህ የተባለበት ምክንያት የዐድማው መሪ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ የታወቁ አርበኛ ስለነበሩ ነው እንጂ፤ አብዛኛው አባላት ያወቁ እና የነቁ ምሑራንና ተቆርቋሪዎች እንጂ አርበኞች አልነበሩም፡፡ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ የወህኒ ቤት ቆይታ የሚጀምረው ከእዚሁ ዐድማ ጋር ተያይዞ ነው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ከመቶ አለቃ በቀለ ጋር የተገናኘነው በ፶፫ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተካፋይነት ተይዤ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ነው፡፡ በወህኒ ቤቱ በቆዩበት ጊዜ በወቅቱ ከነበረው የእሥረኛ ባህሪ ጋር ጨርሶ የማይገጥም፣ በንቃተ ኅሊና ልዩነት ምክንያት የተፈጠረ (አብዛኛው እሥረኛ ከገጠር በነፍስ ግድያና በዘረፋ ወንጀል) ስለነበረ እሳቸው ደግሞ የተማሩ፣ የነቁና ያስተዋሉ ሰው ስለነበሩ የአስተሳሰብ ልዩነት ነበራቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የመቶ ዓለቃ በቀለን እንደእብድ እንጂ እንደቁም ነገረኛ አድርጎ የሚያያቸው ወይም የሚሠሩትን ሥራ የሚያደንቅላቸው አልነበረም፡፡ የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያሸሟጥጥ ካልሆነ ሐሣባቸውን የሚጋራ አልነበረም፡፡ በ፲፱፻፶፫ቱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ምክንያት ተይዘን ወህኒ ከገባነው እሥረኞች መካከል እንኳን ብዙ የቀረባቸውና ያነጋገራቸው አልነበረም፡፡ እሳቸውም አልቀረቡም፤ አላነጋገሩምም፡፡ ከእኔ ጋር ያቀራረበንና ፅኑ ወዳጅ ያደረገን ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ለመስማት ይታገሣል፤ ልብ ብሎ ይሰማል የሚለው እምነታቸውና ሲናገርና ሲከራከርም የሚያነሣቸው ነጥቦች በቀላሉ የሚታለፉ አይደሉም የሚል አስተያየታቸው ነው፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ ከቤት ይዤው የመጣሁት ነቅቶ ተግቶ ልብ ብሎ የመስማትና የመታገስ ባህሪ ያደገብኝ ነው፡፡ እሳቸውንም ሆነ ማንንም የሚናገሩትን ጀምረው እስቲጨርሱ ሳላቋርጥ መስማትና ነገሮችን ከሥሩ ለመረዳት ጠበቅ አድርጌ መጠየቅ ልምዴ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ነው መጀመሪያ ትምህርት ቤት፣ የማንበቢያ ክፍል፣ ቀጥሎም ወደ ቤተክርስቲያን ሥራ ስንሔድ በሐሣብ የተስማማነው፡፡ በአንዳንድ ምክንያትም ትንሽ ቁጣም ሲኖር ስለምታገስና ስለምችላቸው ከኔ ጋር መሥራቱን ሳይወዱት አልቀሩም፡፡ እንደውም የሚያስቡትን ወይም የሚፈልጉትን ሁሉ በኔ አማካኝነት እንዲያልቅላቸው ያደርጋሉ፡፡

የመቶ አለቃ በቀለ በእሥር ቤት ውሏቸው የሚደነቁ አንዳንድ ነገሮች እናይባቸው ነበር፡፡ ከኛ በፊት የነበረው እሥረኛ ሁሉ የሚያውቀውና የሚያነሣው ነገር ይኸውም አዕምሮዋቸውን የሚይዝ ሥራ ከሌለ ሰላም ስለማይሆኑ ካኪ ሱሪያቸውን ወይም

ሽሚዛቸውን ተርትረው ሙልጭ አድርገው ክሩን ፈትተው እሳቸው በመስላቸው ቅርጽ እንደገና ቀደው የሚሰፉ መሆኑ ነው፤ ጊዜያቸውን በዚያ ለማሳለፍ።

የመቶ አለቃ በቀለ የፍርድ እሥረኛ ስለሆኑ ለፍርድ እሥረኛ በተከለለው ሥፍራ ከፍርደኛው እሥረኛ ጋር ተገናኝተው በሠፊው መስክ ላይ እንደልባቸው መዝናናት ሰውነታቸውን ማፍታታት ሲችሉ፤ በባህሪ አለመግጠም ምክንያት ከአንዳንድ ኃላፊዎችና እሥረኞች ጋር እየተጋጩ ግማሽ ያህሉን የእሥራት ጊዜያቸውን በቅጣት ዓለም በቃኝ ውስጥ ነው ያሣለፉት። መቶ አለቃ በቀለ እናሲሞስ ወደ ዓለም በቃኝ ሲገቡ በእግረ ሙቅና ሰንሰለት እጃቸውና እግራቸውን ይታሠራሉ። ስለዚህ ሱሪያቸው እንደማንኛውም በቀበቶ የታሠረና በፊት ለፊት በቁልፍ የሚከፈት ሣይሆን በጎንና ጎን ጭናቸው መዝጊያና መክፈቻ ቁልፍ የተተከለላት ቁምጣ ሱሪ ነበር የሚለብሱት። ይህም እጅና እግራቸው በሰንሰለት የታሠረ ስለሆነ ለመጸዳዳት ሲፈልጉ ሱሪያቸውን በቀላሉ ፈተው ለማውለቅ እንዲመቻቸው ነው። ግራ ቀኝ ካለው ጭናቸው ሱሪ ላይ የአፍሪካ ካርታን አዘውትረው ይሥሉና ኢትዮጵያን የሚያሣየውን ምስል በጥቁር ክር ይሰፉታል። ይህም "ኢትዮጵያ ከመከራና ከጭንቅ ያልወጣች ችግረኛ ሃገር ነች" የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ነበር። የሚያደርጉትም መለዮ የሚደንቅ ቅርጽ (የሆስቴሶችን ቆብ የሚመስል ትልቅ ቆብ) ያለው ሆኖ፤ ከጐንና ከጐኑ ላይ በጥቁር ክር የተቀረበ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነበረው። ከሱሪያቸው ላይም ግራ ቀኝ መቀመጫው በጥቁር ክር ጥልፍ የኢትዮጵያን ካርታ የሚያሳይ ሁለት የአፍሪካ ካርታ ያደርጉበት ነበር፤ ያው ችግር እና መከራዋ ያላለቀ በችግርና በጨለማ ውስጥ ያለች ነች የሚል ትርጉም ለመስጠት ነበር።

የወህኒ ቤቶች አስተዳደር ረዳት ሚኒስቴር አቶ ጫን ያለው ተሾመ የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ረጂም ጊዜ መታሠራቸውንና በጅራፍ መገረፋቸው ፊዕመዋል ለተባሉት ጥፋት በቂ ቅጣት እንደሆነ ይሰማቸው ስለነበር በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም ንጉሡ ዘንድ አቅርበው ምህረት ለማሰጠት ጥረት አደረጉ። ጥረቱም ጃንሆይ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ወህኒ ቤቱን ሲጎበኙ እሥረኛው ሁሉ በየክፍሉ ገብቶ ተዘግቶበት የመቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ብቻ እደጅ እንዲቆዩ እና ጃንሆይ ሲመጡ እጅ ነስተው ምህረት እንዲጠይቁ ግፊት ማድረግ ነበር። እንደታሰበውም ጃንሆይ ሲመጡ ወጥተው እንዲገናኙ ሲደረግ ግን፤ የመቶ አለቃ በቀለ ጃንሆይን ዝቅ ብለው እጅ ለመንሳት ስላላስደሰታቸው፤ አንገታቸውን ብቻ ትንሽ ቀለስ አድርገው መለሡት። ይህ አንድ ቅሬታን አሣየ። ጃንሆይ "እንዴት ነህ ያ! ጥጋብህ በርዷል" ብለው ሲጠይቋቸው፤ ደግሞ "ቀድሞም አልጠገብኩ፤ አሁንም አልተቸገርኩ" ሲሉ መለሱ። ጃንሆይ ይህንን መልስ ሲሰሙ "መልሠው!" ስላሉ የመቶ አለቃ በቀለ ወደክፍላቸው ተመለሱ። ስለዚህ የመቶ አለቃ በቀለ እሥራታቸውን ለመፈፀም በወህኒ ቤት እንዳሉ በመሐሉ በወታደራዊ መንግሥት መምጣት ምክንያት ከእሥራት ተፈቱ።[24]

[24] ከዚህ በኋላ ወደ ሲቪል ሕይወት ተመልሰው ሲኖሩ ከመታሠራቸው በፊት በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ከወለዱት ልጃቸው በተጨማሪ ተሹመ የሚበል አንድ ሌላ ልጅ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ወልደው ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. አርፈዋል።

## ማኅበራዊ ግልጋሎት በወኅኒ ቤት


አንዳንዱን የከባድ ፍርድ እሥረኛ ወይም በከባድ ወንጀል ተከሶ ገና ፍርዱን ያላገኘ የቀጠሮ እሥረኛን እየቀረብኩ ሳናግር ስለአገሪቱ የፍርድ ሒደት ያስገነዘበኝ ነገር ነበር። እሥረኛው በጣም የሚፈልገውና የሚያከብረው ጆሮውን ሰጥቶ ነገሩን የሚሰማው ዳኛ ነው። እሥረኛው እምነቱ ዳኛ በቅጡ ከሰማ ትክክለኛ ፍርድ ይሰጣል የሚል ነው። እሥረኛው እንደችግር የሚያነሳው ዳኞቹ የሰውን ጉዳዩ ለመስማት ትዕግሥት ያጡ ስለመሆናቸው ነው። ብዙዎቹ እሥረኞች ዳኞች ነገሬን በደንብ አልተረዱትም፣ አልሰሙትም በዚህም ምክንያት ነው እንዲህ ያለ ፍርድ የሰጡኝ የሚሉ ናቸው። እንዲህ ዓይነቶቹን ችግሮች ሙሉ መንፈሴን ለእሥረኞች ሰጥቼ ልብ ብዬ ስለምሰማቸውና እኔም የታየኝን እንዲረዱኝና እንዲገነዘቡኝ አድርጌ ስለማናግራቸው ከብዙ ችግረኛ እሥረኞች ጋር ለመቀራረብ ቻልኩ። ችግሩ እንዲፈታ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ የሚያጽፍ ጉዳይ ሲያጋጥምም፣ ጥሩ የእጅ ጽሑፍ በነበራቸው ተባባሪዎቼ የክብር ዘበኛ የሦስተኛ ክርስ መኮንንኖች የመቶ አለቃ ተስፋ ወልደ ትንሣኤ፣ የመቶ አለቃ ዘገየ በርሄና የመቶ አለቃ አበበ ገላግሌ (በኋላ ኰሎኔል) ጸሐፊነት የእሥረኛውን ችግር አፍታተን ጽፈን ለሚመለከተው ክፍል እንዲያቀርብ እየመከርን እንሰጥ ነበር። በተጨማሪ በወህኒ ቤቱ የሥራ መደቤ፣ በኢንዱስትሪና በቀለም የትምህርት ክፍል ኃላፊነት ስለነበረ ከብዙ እሥረኛ ጋር እንድገናኝ፣ ብዙ እሥረኛ እንዲቀርበኝ እና እንዲወደኝ አድርጎኛል። በአጠቃላይ የወህኒ ቤት ቆይታዬ በዕውቀት፣ በጉልበት፣ በሀብትና በወገን መመካት ዋጋ እንደሌለው የእንድገነዘብና "የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ" የሚለውን ኃይለ ቃል በሚገባ ተረድቼ "ፈሪሃ እግዚአብሔርን" እንድላበስ ረድቶኛል። ይህም ከላይ በተጠቀሱት የትምክህት ምግባሮች ከተጐዱ ብዙ እሥረኞች ጋር ተገናኝቼ ስህተቱን በመገንዘቤ ነው።

አብረውኝ ከሚኖሩት የክቡር ዘበኛ የማስታወቂያ ክፍል ኃላፊ የነበረው የሻምበል አሥራት ደፈረሱ የወህኒ ቤቱን ክሊኒክ ሀኪም ዶ/ር ቸዝ የተባሉትን ዩጉዝላቪያዊ ሐኪም ይረዳ ነበር። የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ ደግሞ የሻምበል አሥራትን ይረዳ የነበረ መኮንን ነው። የሻምበል አሥራት ደፈረሱ በአሜሪካ ከቦስተን ዩኒቨርስቲ በጆርናሊዝም የተመረቀና በዚያን ጊዜ ሁለተኛ ዲግሪውን በሳይኮሎጂ ለማግኘት ይሠራ ነበር። የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በኤክስቴንሽን ዲግሪውን ለማግኘት ትንሽ ብቻ የቀረው ነበር።

ወህኒ ቤት እኔ አብዛኛውን ጊዜዬን ከባድ ችግር ካለባቸው እሥረኞች ጋር እየተገናኘሁ በመነጋገር ብዙ ጊዜዬን ሳሳልፍ ሁለቱም ቅንና ብልህ ቢሆኑም፣ ከሥራ የተረፈ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በማንበብ ነበር። እንደውም እኔ ከእሥረኛ ጋር እየተገናኘሁ በማውራት የማጠፋው ጊዜ በጣም ያሣስባቸው ስለነበር፣ ይሔ እእምሮ በከንቱ ሊባክን የሚገባው አይደለም፣ አንተ ሰውዬ ተመለስ፣ ለራስህም አስብ፣ ማንበብ አለብህ


ብለው ይወተውቱኝ ነበር። እውነትም በወህኒ ቤቱ ተጠቀምኩ ከምልባቸው ነገሮች ዋንኛው በነዚህ ሁለት ወንድሞቼ ምክር ወደ ንባብ ገብቼ ለአምስት ዓመታት ብርቱ አንባቢ በመሆን የማንበብ ልምዱን በመገንባቴና ሠፊ ዕውቀት በመገብየቴ ነው።

በአጠቃላይ ወህኒ ቤት የመከራና የመቀጣጫ ቦታ ብቻ ሣይሆን፤ ራስን የማወቂያ፣ የመማርያና ምርምር ለማድረግ እንደ ጥልቅ ውቂያኖስ የራቀና የሠፋውን የሰው ባህሪ ለመረዳት የሚቻልበት ቦታ ነው። ከዚህ በገሀድ በዓይን እየታየ፣ በጆሮ እየተሰማ በአእምሮ የሚያዝበት የሰው ባሕርይ ቤተ ሙከራ (ለቦራቶሪ) ውስጥ ገብቶ ሁሉን ሰምቶና ተመራምሮ መውጣት የኋላ ኋላ ጠቃሚነቱ ዕጅግ ከፍተኛ ነው። በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት በአንዲት ትንሽ ቦታ ተኩኖ የመላዋን ኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ አስተዳደርና ፍትሕ ሁኔታ ለማወቅ ይቻላል እንደማለት ነው። በወህኒ ቤቱ ውስጥ ያሉት እሥረኞች ከሁሉም ጠቅላይ ግዛቶች በበቂ ቁጥር የመጡና ለናሙና የቀረቡ የሚያስመስል ነው። ወህኒ ቤቱን የየጐሣውን ባህል ባህሪይ ሁኔታውን እንዲሁም በየአገሩ የነበረውን የአስተዳደርና የፍትሕ ሁኔታን ሁሉ ለማወቅ ከፍተኛው የጥናትና የምርምር ላባራቶሪ (ቤተ ሙከራ) አድርጎ መውሰድ ስህተት አይሆንም። ወህኒ ቤት ለብዙ የጥናትና የምርምር ይጠቅማል። በተለይ በተለይ ለህግ ተማሪዎችና ለፖሊስ መኮንኖች ማሠልጠኛ ተቋሞች።



እሥር ቤት ውስጥ ሳለን በተሰጠን ልብስ ከእሥር ቤት በወጣሁ በሳምንቱ የተነሣሁት ፎቶ

እንግዲህ የወህኒ ቤቱ ኑሮ ይኸን ሲመስል የእሥረኛው ስለ ፖለቲካና ስለአስተዳደር የነበረው ንቃተ ኅሊና ደግሞ ምን ይመስል እንደነበር ለማየት አጋጣሚዎችን ማንሳቱ ያስፈልጋል። ግርማዊት እቴጌ እንደሞቱ ለፍትሀት (ነፍስ ይማር) ለማሰኘት የሚሆን ሽሚዝና ቁምጣ ሱሪ ለእሥረኛው በሙሉ እንዲታደል ተደርጐ ነበር። ይኸን ልብስ ጥቂቶቹ ታሣሪዎች ቢለብሱትም አብዛኛው ግን አልለበሰውም። ታሣሪው መልበስ ያልፈለገበት ምክንያት እጅግ ተራ የሆነ ቀለም ከመነከሩ በቀር መናኛ አቡጀዲ ጨርቅና ስፌቱም እዚህ ግባ የማይባል በመሆኑ ነበር። ስለዚህ በጣም ከተቸገረው እሥረኛ በቀር፣ ሌላው ንቆ ተወው። ይህ ሁኔታ በቤተ መንግሥቱ እንደተሰማ



እሥር ቤት ውስጥ ሳለን በተሰጠን ልብስ ከእሥር
ቤት በወጣሁ በሳምንቱ የተነሣሁት ፎቶ

የሚጠቁመው፤ ልዑል ሣህለ ሥላሴ ሲሞቱ ለጦሩ የሚሰጠውን ዓይነት ጥሩ የሆነ የአሜሪካ ሸሚዝና የሱፍ ሱሪ (ባትል ድሬስ) የሚባለው ልብስ ለእሥረኛው በሙሉ እንዲታደል መደረጉ ነው። ይህም የሚያመለክተው ለእቴጌ መነን ፍታት ተብሎ የተሰጠው አቡጀዴ ተንቆ ያስነወረ መሆኑን ነው። ልዑሉ ሲሞቱ ከልብሱ በተጨማሪ ለእሥረኛው አንዳንድ ትልቅ አራት መዓዘን ዳቦ (በዚያን ጊዜ ፳፩ ሣንቲም ይሸጥ የነበረ) ውስጡ ክትፎ ተሞልቶ ለእራቱ ታደለ። እሥረኛው ክትፎ የተሞላበትን ዳቦ ከበላ በኋላ አንድ እሥረኛ ያቀረበው ምርቃት ለእሥረኛው እርግማን ሆኖበታል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት አብዛኛው እሥረኛ ችግረኛ ነበር። እንደዚህ ያለ ምግብ እሥረኛው አግኝቶ ስለማያውቅ በእራቱ ተደሰተ። በዚህ ምክንያትም አንድ እሥረኛ ንጉሡን «ዕድሜህንና መንግሥትህን ያርዝመው» ብሎ ሲመርቅ፤ ጥቂት እሥረኞች አጨበጨቡ። ታዲያ ማሞ የሚባል በክብረ ነክ ወንጀል ክስ ታሥሮ ያለ ሰው ተነስቶ በመቆም፣ «አፈር ያብላህ! ሁል ጊዜ በሆድህ እየተገዛህ የምትኖር፣ ቂጥህን እየቆረጠ በአፍህ ሲያጉርስህ ዕድሜ ትለምንለታለህ! ፍትሕ አትጠይቅም?» ብሎ ተናገረው። ይህን የተናገረው ማሞም በማግሥቱ በካቦው ከሣሽነት ወደ ኃላፊዎቹ ቀርቦ እጁ ታሥሮ ዓለም በቃኝ እንዲገባ ተደረገ።

## የክብር ዘበኛ ሠራዊት መበተን

የክብር ዘበኛ ሠራዊት የአገሪቱን የሥልጣኔ ፈር በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት ተከትሎ የታነፀ በተዋጊነት በዓለም እስከመታወቅ የደረሰና ለአገር ዳር ድንበር ማስከበር ኢትዮጵያ ትመካበት የነበረ ሠራዊት ነበር። ሠራዊቱ በታጠቀው መሣሪያ ጥራትና ባለው ጥሩ የተዋጊነት ልምድ ሲመዘን የመፈንቅለ መንግሥቱን ንቅናቄ አውቆትና አምኖበት ቢሳተፍበት ኖሮ የተቃራኒው ኃይል ማጥቃት ቀርቶ ሊቋቋመው አይችል እንደነበር የሚያውቁት ሁሉ በልበ ሙሉነት ይናገራሉ።[25] ተደጋግሞ እንደተነገረው በመፈንቅለ መንግሥቱ ሒደት፣ በቁጥር አነስተኛ ከሆኑት የክብር ዘበኛ መኮንኖች በተቀር የተሰለፈው የክብር ዘበኛ ኃይል የጃንሆይን መንግሥት ከግልበጣ ለመከላከል የመሰለው እንደነበር የሚያከራክር አልነበረም። አንዴ ከተጀመረ በኋላ የሰው ኀሊና የማመዛዘንና ማገናዘብ ኃይል እያገኘ ስለሚሔድ፤ ሠራዊቱ ባየውና በሰማው ሁሉ አሰላለፉ የገባለትን ቃልኪዳን እየጣለ እንደሆነ መረዳቱ አልቀረም። ይህም ያጎረሰውን አረር እያፈናጠረ የውጊያ መስመሩን እንዲለቅ የሞራል ግዴታ ሆኖበታል። ይህ ስመጥር ሠራዊት የውጊያ መስመሩን ሲለቅ የሚያሰባስበውና አመራር የሚሰጥ አዛዥ በማጣቱ ተበታትኖ በየዛፍ ሥሩ ለሚጠብቅ ለደፈጣ ዘራፊም ተጋልጧል።

ይህ በእንደዚህ እያለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የብራዚል ጉብኝታቸውን አቋርጠው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ አንዳንድ ቀደምት የክብር ዘበኛ መኮንኖችን አነጋግረዋል። ከመኮንኖቹ መካከል አንዱ የነበሩት ኮሎኔል ሙላት አብጤ ለጃንሆይ ሲያስረዱ "የክብር ዘበኛ አልከዳዎትም። መንግሥቱ ንዋይ በነገረው ተሰልፎ ነበር። ሀሰት መሆኑን ሲረዳ ተመልሷል" እንዳሏቸው፤ ጃንሆይም ‹‹ሠራዊቱ እንዳልከዳን እናውቃለን። ሆኖም እጁን ከመስጠት ይልቅ ከከተማው ወጣ ብሎ እራሱን እየተከላከለ ለምን አልጠበቀንም›› ሲሉ መልሰውላቸዋል።[26] ይህ አባባል የክብር ዘበኛ ሠራዊት መሳሳቱን አውቆ የውጊያ መስመሩን እንደለቀቀ ቢቻል የአሳሳተውን ቡድን በቁጥጥር ሥር አውሎ ታማኝነቱን ማረጋገጥ፤ ሳይችል ሲቀር እጁን ለተቃራኒው ሳይሰጥ በኅብረት ተገልሎ ከከተማው ውጭ እራሱን እየተከላከለ ቆይቶ ለምን የእኛን መግባት አልጠበቀም? የሚል ነበር።

በእርግጥም ጃንሆይ ለክብር ዘበኛው የመራራት ሁኔታ ታይቶባቸዋል። የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው በታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ሆኖ ብዙዎቹ የክብር ዘበኛ መኮንኖችና ወታደሮች በቁጥጥር ሥር እያሉ በወሩ መጨረሻ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የልደት በዓል ላይ በማረፊያ ቤት የሚገኙትን የክብር ዘበኛ መኮንኖች ስም ዝርዝር ተጠናቅሮ ለያንዳንዱ መኮንን ቤተሰብ ብር ፲ ለበዓል መዋያ

---

[25] ጄኔራል መንግሥቱ በመጨረሻ ለፍርድ ቤት በሰጡት ቃልም ይህንኑ ያሉ ሲሆን፣ የሻለቃ መሳኩ በቀለ፣ የሻለቃ አዲስ አለም ጸጌ እና የሻለቃ ተፈራ ወ/ትንሣኤ ከጃንሆይ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ ይህንኑ በልበ ሙሉነት አረጋግጠው ሲናገሩ ጃንሆይም ወደ ጄኔራል መርዕድ ዞር በማለት ሰማህ ሲሉ ገርመም አድርገዋቸው እንዳለፉ የሻለቃ መሳኩ ገልጸልኛል።

[26] ኮሎኔል ሙላት አብጤ ፬ኛ ክፍለ ጦር አሥር ቤት ሳለን እንዳጫወቱኝ።

እንዲሰጣቸው የሚያዝ መልዕክት በጀኔራል ድረሴ ዱባለ አማካኝነት ለሻለቃ አንጋጋው ይሰጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት ከታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም. ጀምሮ የያንዳንዱን መኮንን አድራሻ ሻለቃ አንጋጋው በማቅረብ እንዲከፈላቸው ሆነ፡፡[27] እኔ የዚህ ታሪክ ጸሐፊም በዚሁ ትዕዛዝ መሠረት እስከተፈረደብኝ ግንቦት ወር ድረስ በወር ብር ፭፻ ለቤተሰቤ ሲከፈል ቆይቷል፡፡

እንደኮሎኔል አንጋጋው ኃይሌ አባባል ጃንሆይ ከዚህ አልፎም የተበተነው የክብር ዘበኛ ሠራዊት ተሰብስቦ በነበረበት መደብና ቀደም ብሎ በነበረው የታማኝነት መንፈስ እንዲቆም ፍላጎትም ነበራቸው፤ ጥረትም አድርገዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከግርግሩ መባቻ ጀምሮ የቴክኒክ ክፍል ባልደረቦች በሙሉ ተሰብስበው የነበሩበትን የሥራ ክፍል እንዲያጠናክሩም ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ተዋጊው ሠራዊት በግዞት ካምፕ ውስጥ ስለነበር ወዲያው እርምጃ መውሰድ አልተቻለም፡፡ የክብር ዘበኛ ሠራዊት እንደነበረው ተመልሶ እንዲቋቋም የግርማዊ ጃንሆይ ፍላጎት የበረታ በመምጣቱ ሁኔታውን ለማስተካከል እርምጃ መወሰድ ተጀመረ፡፡ በዚህ መሠረት ጃንሆይ መጀመሪያ ጄኔራል ድረሴ ዱባለን የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ አድርገው ሾሙ፡፡ ሁኔታውን በቅርታ የሚገልጹት ኮሎኔል አንጋጋው እንደሚሉት ግን ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ክብር ዘበኛን መልሶ ለማቋቋም ይረዳሉ በሚል አስተሳሰብ ቢሾሙም፤ ከተቃራኒው ኃይል አንደኛው ስለነበሩ ተዋጊ መኮንኖችንና ወታደሮችን ማራቅ ብቻ ሳይሆን የሲቪል አስተዳደር ሠራተኞችን ጭምር በየሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት እንዲደለደሉ የማዘዋወሪያ ዕቅድ በማውጣት ከማጠናከር ይልቅ የማዳከም ሥራን ነበር የመረጡት፡፡ የዝውውሩን ሐሳብም ለይሁንታ ለጃንሆይ አቅርበው ነበር፡፡ ዕቅዱ ግን ፈር ሳይዝ ጄኔራል ድረሴ ዱባለ የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሆነው ተዛወሩ፡፡

በጄኔራል ድረሴ ምትክ ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያምም የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ሆነው ተሾሙ፡፡ ሁለቱ ጄኔራሎች የሥልጣን ርክክብ ባደረጉበት ወቅት ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ስለ ክብር ዘበኛ አስተዳደር የነበራቸውን አቋም ለተተኪው ሲያስረዱ፤ አንድ ዝርዝር አውጥተው «እነዚህ በክብር ዘበኛ ውስጥ የነበሩ ሲቪል ሠራተኞች ወደየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እንዲደለደሉ ተወስኖ መሸኛ እየተዘጋጀላቸው ነው» ይላሉ፡፡ ጄኔራል ደበበም «ከኖሩበት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የሚዛወሩበት ምክንያት አይኖርም» አሉ፡፡ ይህን በቦታው ተገኝተው ለማዳመጥ የቻሉት ኮሎኔል አንጋጋው[28] ‹‹የጃንሆይን አቋም የሚደግፍ አዛዥ እንደተገኘ ገመትኩ›› ይላሉ፡፡ የንጉሡ ፍላጎት ለደሞዝም ሆነ ለሥራ ማስኬጃ የሚውለው የክብር ዘበኛ በጀት ሳይቀነስ እየተፈቀደ የሥራ እንቅስቃሴው እንዲቀጥል፣ የሠራዊቱ አቋቋም ግን እንዲጠና ነበር፡፡ ስለዚህ

---

*[27] ሻለቃ አንጋጋው በጄኔራል ድረሴ ዱባለ አማካኝነት አንድ አስቸኳይ ትእዛዝ ደረሰኝ ሲሉ የገለጹልኝ ነው፡፡*

*[28] የክብር ዘበኛውን የመልሶ ማቋቋም ጥረትና የተደረሰበትን መረጃ ያገኘሁት ከኮሎኔል አንጋጋው ነው፡፡*

ጃንሆይ የመፈንቅለ መንግሥት ሤራ ጠንሳሾች ከሆኑት መኮንኖች በስተቀር ሌላው የክብር ዘበኛ ሠራዊት በሙሉ በነበረበት መደብ ተመልሶ ሥራውን እንዲቀጥል ሙሉ ፍላጎት ነበራቸው። ይህንን ሐሳብ ግን የተቃራኒው ኃይል የማይቀበለው ሆኖ ተገኘና ንጉሡ ነገሥቱም እንደሚጥማቸው ለማድረግ ጣቱን ከጠመንጃው ቃታ ካላነሳው ኃይል ጋር የሚያናቁር ተከታይ አደጋን መጋበዝ እንደሆነ የተገነዘቡ ይመስላል ሐሳቡ በእዚሁ ይደመደማል።

ይህን ተከትሎ ሌላ አስታራቂ ሐሳብ ይመነጭና ተመራጭ ሆኖ ይገኛል። ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሤራ ነፃ የሆነው የክብር ዘበኛ መኮንንና ሠራዊት በሞላ ወደ ነበረበት መደብ መመለሱ ቀርቶ፤ አዲስ አበባ ውስጥ ኖሮ ለውጊያ የተሰለፈ ሁሉ የወንጀል ይዘቱ እየተጣራ ነፃ ሆኖ የተገኘው በጦር ሠራዊቱ ውስጥ እንዲደለደል ማድረግና በመፈንቅለ መንግሥቱ ወቅት ኮንጎ የነበረውን የክብር ዘበኛ ብርጌድና በልዩ ልዩ ምክንያት በየክፍለ አገሩ የነበሩና ለትምህርት በውጭ አገር የነበሩ መኮንኖች ብቻ ወደ ነበሩበት ክብር ዘበኛ መደብ እንዲመለሱ ማድረግ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ከጦር ሠራዊቱ ውስጥ አዛዦች የሚመርጧቸው ሁሉ ተሟልተው የክብር ዘበኛ ኃይል አንደኛ ክፍለ ጦር ክብር ዘበኛ በሚል ስም እንዲቋቋም ተወሰነ። ስለመቋቋሙ ያወዛገበው ሐሳብ አስታራቂ መፍትሔ አግኝቶ ሠራዊቱ አንደኛ ክፍለ ጦር ክብር ዘበኛ በሚል ስያሜ በስብጥር በተቋቋመ በማግሥቱ የኮንጎ ዘማች ብርጌድ አዛዥ የነበሩት የቀድሞው ክብር ዘበኛ አባል ኮሎኔል ወልደ ዮሐንስ ሽታ የብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ ተሹመው የስብጥሩ ክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ ሆነው ተሾሙ። ከዚህ በኋላ ለቤተመንግሥቱ እንደቀድሞው አንዱ ከሌላው እኔ እታመናለሁ በሚል የሁለት ተፎካካሪ ጥበቃ ክፍል ሥር መውደቁ የመጨረሻ መፍትሔ ባይገኝለትም መጠነኛ እርጋታን አገኘ። በስብጥር በተቋቋመው ክብር ዘበኛ ውስጥ ግን መተማመንና መግባባት ካለመገኘቱም ባሻገር፤ አንዱ ወገን ከሌላው በችሎታ እልቃለሁ ወይም ይልቀኛል በሚል የመናናቅ መንፈስ እርስ በርስ በሀሰት መረጃ መናቆር ተስፋፋ። አዛዦችም ይህን መናቆር የሚያባብስ ስውር መመሪያ ማውረድን ሥራዬ ብለው ስለያዙ፤ የሠራዊቱ ሞራል እየደከመ መጣ። የወታደራዊ መረጃው ጥንቅር ሳይበጠር በየፊናው ስለሚቀርብ፤ ለቤተ መንግሥቱ የጫማ ውስጥ ጠጠር እንደሆነ ይነገር ነበር። ምክንያቱም አንዱ ያቀረበው ሌላው ካቀረበው መረጃ ጋር እየተጣረሰ ለቁርጠኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ሆነ።